For many of us, the idea of having a wedding or getting married feels unattainable. As if it were a privilege reserved only for those who fit into the narrow mold of what society deems as “normal” - particularly, cishet individuals. Even for those who do fit into this category, the prospect of marriage can still be overwhelming, if not terrifying. The weight of societal expectations and traditional gender roles can create immense pressure on couples, who may feel as though they must conform to certain norms and expectations in order to have a “successful” marriage. This can be particularly challenging for queer couples, who face additional barriers and discrimination when it comes to legal recognition and cultural acceptance of their relationships.

Despite these challenges, the desire for love and companionship remains universal. We all deserve to find people who make us feel seen, heard, and valued, regardless of our baggage. And in a way, wewanted to share this moment with people who allowed us to feel seen the most. Our pseudo-wedding, however false it

might have been, created an opportunity for all of us to feel the love and devotion we all have for one another.

Taking and transforming such a patriarchal, cisgender, heteronormative institution into a subversive expression of queerness was a proclamation that we cannot be contained, categorized, or bordered. We affirm that our love is endless, that it can thrive even in the spaces that intend to break and suffocate us. In the relationships we form with one another, we are welcome as individuals and enough as queer bodies. On a day that represents love, we became it and continued to carry it into all the places that we've entered since. When we are together, we don't have to make ourselves less because we know that we are loved by more. We are so large that we are loved regardless, despite, and in spite of. Our love is outlawed, but it bears all things, believes all things, hopes all things, and endures all things. Our love never ends.

# ኧረ ፍቅር አለ!

## ቪክቶር ጌታ

አንተ/አንቺ

“ውይይይይ ዜጋ ጋር ፍቅር የለም”....”ውይይ ዜጋ ጋርማ መከባበር መተሳሰብ መተጋገዝ የለም”...ገና የዜጋውን ማህበረሰብ ስቀላቀል ሹክ ተብለው ከተነገሩኝ ነገሮች መሃል አንዱ ነው። ሰዉ ተፈራርቶ በአይነ ቁራኛ እየተያየ እውነተኛ ስሙን አድራሻውን እና የስራ ቦታውን እየደበቀ ግን አብረው ሲታዩ አብሮ አደግ ነብር ሚመስሉት። እፍፍፍፍ ክንፍ ብለው ብዙ አመት ተዋውቀው ለብዙ አመት የማይለያዩ ነው ሚመስሉት። ለዛም “ሁሉም fake ነው” ይላሉ።  ለእኔ ግን እንደዛ አላየውም። ወጣ ወጣ ማለት ስጀምር አዲስ ተቀጣሪ ስራተኛ ነበርኩና በገቢ አንፃር ብዙ ነገሮችን ማድረግ አልችልም ነበር። ዜጎች ጓደኞቼ ሳገናቸው ከኔ የተሻሉ ነበሩና ብዙ ጊዜ ያግዙኝ ነበር። ለሻይ ቡና ከመክፈል የታክሲ ከመክፈል እንዲሁም አንዳንዴ ሃምሳም መቶም ይሸጉጡልኝ ነበር። ምንም ኖሮን ኡይደለም። ከጓደኝነት ያለፈ ነገር የለንም ግን ያግዙኝ ነበር። ትምህርት እንድጨረስ ይመክሩኛል። በፍቅር ህይወት ላይ ባልታደልም ከጓደኞቼ ግን በቂ ፍቅርን አገኝ ነበር።

እኔም ወግ ደርሶኝ የተሻለ ደሞዝ ሲኖረኝ እነሱ እንዳረጉልኝ ዛሬም ድረስ አደርጋለሁ። ያሉኝን የተሻለ የሚያደርጉኝን ነገሮች ተጠቅሜ ሌሎች ዜጎችን ማገዝ እስለምደውኛል። አደረኩ ብዬም ትዝ የሚለኝ ወይም የምቆጥረው ነገር አይደለም። ትላንት የኔ የበላዮች አድርገውልኛል። እከሌ በዜግነቱ ምክንያት በቤተሰብ ከቤት ተባረረ ሰንባል ትዝ ይለኛል። ሰምንት ሳይሞላ ከዚህም ከዚያም ብር ተሰባስቦ አንስተኛ ቤት ተገኝቶ ኪራይ ተከፍሎ የቤት ቁሳቁስ ተገዝቶ ወድቆ እንዳይቀር ሁሉም ነገር ሽፍንፍ..... ስንተጋገዝም እንደዚህ ነን። አይታየንም እንጂ መልካም ነን።

ጥሉ ምኑ ምናምን ጎልቶ ይታየናል እንጂ ፍቅሩም አለን። የኔን ታላላቆች እየተደወለ ወሲብ ህይወት ስለሚኖሩ ጥያቄዎች ልምምድ ሲያካፍሉ ትዝ ይለኛል። ትዝ የሚለኝ ታሪክ ልጁ ያው ለብቻው እራሱን ሲያስደስት ግዑዝ አካል ከታች አስገብቶ ተወትፋ ቅርቅር። ይታያችሁ እንግዲህ የት ተብሎ ይኬዳል? ማን ዶ/ር ይጠየቃል? ጓደኞቹ ጋር ደወለ። “ቂጤ ውስጥ እንትን ገብቶ አልወጣም አለ”....በዚህ በለው በዛ በለው ቢሉት ወይ ፍንክች። የሚያውቁት በደንብ ልምድ ያለው ልጅ

ጋር ተደወለለት........”ሌብ ያለ ውሃ በመዘፍዘፊያ አድርጎ ይቀመጥ እና ትንሽ ቆይቶ ይግፋው” አለ፡፡...ውልቅ ብላ ወጣች፡፡

እነዚህ ምናልባትም ያሳፍራሉ ያስቃሉ ብለን የምናስባቸው ክስተቶች ናቸው፡፡ ግን ጤናን በተመለከተ ለሚገጥሙን ነገሮች የተዛቡም ቢሆኑ የምንቀያየራቸው መረጃዎች ትልቅ ቦታ አላቸው፡፡ ብዙዎቻችንን ታድገውናል፡፡ እንደሰው እንደዚህ አረገልኝ ከማለት እንደዚህ አረገብኝ ማለት ስለሚቀናን እንጂ ብዙ ማናያቸው ጥሩ ነገሮች አሉን፡፡

ዜጋው ጋ?.....ፍቅር የለም፡፡ የአማትህ ነዋ ፍቅር! እንፋቀር፡፡ ፍቅርን እና መዋደድን በወሲብ ሂሳብ ካየነው እሱ አያዋጣም፡፡ ፍቅርን በመተሳሰብ በመደጋገፍ እይታ ካየነው ሌላ ታሪክ ነው፡፡ በኔ ህብረተሰብ ብዙ ጭንቀቴች እንከኖች እንቅፋቶች ወይም በጊዜው አማርኛ “ተግዳሮቶች” እንዳሉብን አምናለሁ፡፡ የልጅነት  ግዜ ጠባሳዎቻችን የታዳጊነት ጊዜ ሰብራቶቻችን ዛሬ አድገን እንካሳ አድርገውናል፡፡ ከሰው ጋር አብሮ መኖር ይከብደናል፡፡ ስንዋሽ እራሳችንን ስንደብቅ ኖረን ዛሬ ልባችንን ለመክፈት ያመናል፡፡

‘ያ ልጅ ሲያምር’ ስል በልጅነቴ “ሂድ ከዚህ እንደዛ አይባልም” ተብዬ አድጌ ዛሬ ላይ ትላንት አትንካ የተባልኩትን ብነካም አያያዙን ግን አልችልበትም፡፡ እንደቀሽም ሞግዚት በጨቅላነቱ አንገቱን ነው ምቀጨው፡፡ አያድግም፡፡ እናም ፍቅር ሳይኖር ቀርቶ ሳይሆን ፍቅርን መንከባከብ ስላልተማርን ነው፡፡ ስላላየንም ነው፡፡ መተሳሰብ መተጋገዝ መረዳዳት ግን አለን፡፡ ጥሩ ጥሩ ጓደኞች አሉኝ፡፡ ወዳጆች፡፡ ቤተሰቤን ጓዳ ጎድጓዳዬን ሚሰጥር ቅሌቴን የሚያውቁ፡፡ ለእኔ የቤት እቃ ለመግዛት እቁብ ከመግባት አንዳችን ዜጋ ተብለን ከቤት ስንባረር ተረባርበን የቤት እቃ አሟልተን ቤት እስከመከራየት የምንተጋገዝ፡፡

ዛሬ ላይ ደህና ስራ ይዤ ያለሁበት ወቅት ላይ አይደለም፤ በፊት ገና ደሞዜ ወር ከወር የማታደርስ ጊዜ፡፡ አንድ ክፍል ቤት መሃል ከተማ ላይ 600 የነበረበት ጊዜ፡፡ ሃምሳ እና መቶ ነበር ያዋጣነው እና የተሰበሰበውም፡፡ ስም ዝርዝሩ ላይ 200 ያዋጣ አይቼ ‘ዋው ሃብታም’ ብዬ ‘ማነው? አጣብሱኝ’ ያልኩበት ጊዜ፡፡ ጓደኛችን ከቤት ከወጣ ስምንት ሳይሞላ ብሩ ተሰባሰቦ፣ ቤት ተገኝቶ፣ መርካቶ ሄደን የቤት እቃዎች ገዛዝተን ጨርሰን እሱ ማረፊያ አግኝቷል፡፡ መዋደድ እንዲህ ነው፡፡ ለቅሶ ሲባል ድፎ አሰደፍቼ ተሸክሜ ክፍለሃገር ድረስ ተሳፍሬ የሄድኩትን ሳስታውስ የሆነች እሮጊት ሴትዮማ ውስጥ አለች እላለሁ፡፡

who does that in his early twenties? ከአዲስ አበባ ድፎ ዳቦ......ጓድኛዬን ስለምወደው ነው።

ተራራ እንውጣ ተባብለን የየካን ተራራ ሽክ ብለን ተንጠላጥለን ወጥተን ፀሃይ ስትፀሃይ አይተናት...ደስ ሲል። ዜጋ ወይ ለብድ ወይ ለቂማ እና ቅምቀማ ብቻ የሚገናኝበት ጊዜ ላይ አስራ ምናምን ፋጤያም ወንድ ተሰብስቦ ተራራ መውጣት ደስ የሚል ስሜት ነበረው። ቧልቱ ቁምነገሩ ቡጨቃው......ከዛም ወርደን ምሳ ስንበላ ተማሪ ወይ ስራ የሌለው አይከፍልም ነበር። ከየት አባቱ ያመጣል? እንሸፋፈናለን። እንተጋገዛለን። “ፍቅር የለም” ስንል ውሃ አጣጭ የፍቅር አጋር ትዳር ከሆነ እሱ ሌላ ታሪክ ነው። መዋደድ መተጋገዝ ግን አለ።

# እንዴ አለመያዝ ነው

## ቻርም

እንተ/ እሱ

ሁሌም ፓርቲ ሲኖር ቀድሞ ወሬው በጓደኛ ጓደኛ ነው ሚሰማው። በተለይ የክፍያ ፓርቲ ከሆነ ሰው ሁሉ እንዲሰማ ሁለት ሶስት ሳምንት ቀደም ብሎ ነው ወሬው ሚናፈሰው። እኛም በሆነ የስራ ቀን አመሻሽ ላይ ስብሰብ ብለን ሻይ ስንጠጣ ከመሃላችን እንደዚህ አይነት ወሬ ማያመልጠው ጓደኛችን በመጪው ቅዳሜ ፓርቲ አለ ብሎ ሲነግረን..

የት ... ?

የማ .....? እያልን በጥያቄ አጣደፍነው። ከማሃላችን አንዱ ጓደኛችን "የዛች ብሰብስ ፓርቲ እንዳይሆን ብቻ! ባለፈው ምን በምታክል ቤት ውስጥ ደግሳ በሺሻ ጭስ አፍና ልትገለን ነበር" አለ።

ስለ ፓርቲ ወይም ስለ ማንኛውም የዜጋ ስብሰብ ሲወራ አንድ ኮምፕሌን የሚያደርግ ሰው አይጠፋም። እኛም ያንቺ አሉባልታ መጨረሻ የለውም በሚመስል እይታ አይተናት ተሳሳቅን። እንደዚህ አይነት ቅሬታ የሚያቀርቡት ናቸው ደሞ የዜጋ ፓርቲ አሽትተው ሚሄዱት። ታዲያ በማግስቱ ጠዋት በስልክ ያለው ቡጨቃ... ።

ወሬውን ያመጣው ጓደኛችን ባክሽ አንቺ የትም ቢሆን ትሄጃለሽ ብሎ አፏን አሲያዛት እና ተረጋጉ ገና እኔም ቦታውን አላወኩም ቅዳሜ አሳውቃችኋለው አለን። በዛው ከዚህ ቀደም ፓርቲዎች ላይ ስላጋጠሙን ጉዶች እያወራን ማሽካካታችንን ቀጠልን። ሁሌም ስላለፉ ፓርቲዎች ሲወራ ከዚህ ቀደም ያልሰማነው.. የተዘለለ ነገር ወይም አንዱ ሳይጨርስ አንዱ እያሰቆመው ከሰር መሰረቱ ያልሰማነው ወሬ ስለሚኖር ያለንበት አከባቢ እስኪረበሽ ድረስ ነው ምንስቀው። ደሞ እንዳንድ ሰዎች አሉ ተመሳሳይ ታሪክን እያደሱ.. ቅመም እየጨመሩ ሚያወሩ...።

ቅዳሜ ፥

ቅዳሜ እንደምንም ተንቀራፉ ደረሰች። ከስራ እንደወጣሁ በፍጥነት ወደ ቤት ሄጄ ለማታ ፓርቲ መዘገጃጀት ጀመርኩ። የዜጋ ፓርቲዎች በየጊዜው የሚገኙ ስላልሆኑ እንደዚህ አይነት አጋጣሚዎች ሲገኙ የማይሰረዝ

ፕላን የለም። የቤተሰብ ልደት፣ የቀጥ ጓደኛ ፕሮግራም ሁሉም ነገር ይሰረዛሉ። አንዴ እንደውም አንዱ ጓደኛዬ የአጎቱን ለቅሶ ቀርቶ ፓርቲ እንደመጣ አስታውሳለሁ። እንዴ ምነው? ስለው ባክሽ ነገ ደርሳለው ብሎ አስቆኛል። የዛን እለትም ቤት ምንም እንዳይሉኝ እየፀለይኩ ትንሽ እረፍት አድርጌ ሻወር ከወሰድኩና ትንሽ ከተቁላላሁ በኋላ ለጓደኞቼ ደውዬ እነሱ ወዳሉበት ካፌ አቀናሁ።

የተቀጣጠርንበት ካፌ ስደርስ ጓዳኞቼ ቀድመውኙ ስብስብ ብለው ያውካካሉ። የተለመደውን ሰላምታ ተለዋውጠን.... “ኡኡኡ ዛሬ ደሞ አምሮብሻል...” ተባብለን ወሬያችንን ቀጠልን። ከፓርቲ ደስ የሚለኝ ነገር ሁሉም ተሸረሟሙጦ መምጣቱ ነው።እውነት ለመናገር ከዚህ ቀደም ከምናደርገው የተለየ ነገር አናደርግም። ምናልባት ፀጉር ቤት መሄድ... ሻወር... ንፁህ መልበስ.. እና ሽቶ። ብዙ ሽቶ ብንቀባ ነው። ለነገሩ ከዚህ በላይ ምን ይደረጋል። ደሞ ስንዋጋገስስ አምሮብሻል፣ ዘንጠሻል.... ዛሬማ ብቻሽን አትገቢም ስንባባል ስናምር።

ፆታ የቀየርን ይመስል አንቺ አንቺ ስንባባል ለሰሚው ግራ ነው። በአጋጣሚ አዲስ ሰው ካለ ግር ይለዋል ግን እሱም ወዲያው ተላምዶ ራሱን አንቺታ ውስጥ ያገኘዋል። አስር ደቂቃ በማትሞላ ስአት ማይወራ ነገር የለም። ፋሽን፣ ፊልም፣ ስሞኑን ያገኘናቸው ሰዎች ፋይል... ሁላችንም አንድ ላይ እያወራን እንስማማለን። አንዳችን የጀመርነውን ወሬ አንዳችን እንጨርሰዋለን።

ብቻ ስብስብ ብለን እየቦጨቅን እያሽካካን እያለ በመሃል ስለ ፓርቲው ያወራልን ጓደኛችን ደውሎ የፓርቲውን ቦታ አሳወቀን። ሰዓትና ቦታውን ካወቅን በኋላ ለሌሎች ጓደኞቻችን ነግረን እነሱ እስኪመጡ ትንሽ እናሟሙቅ ተባብለን ቅርብ ወዳለ ባር ሄደን አንድ ሁለት እያልን ወሬአችንን ቀጠልን። ትንሽ ጋል ማለት ስንጀምር የቀሩት ጓደኞቻችን ደርሰው ተያይዘን ወደ ፓርቲው ሄድን።

በእርግጠኝነት ቦታው ትዝ ባይለኝም የሆነ ጭር ያለ አንድ ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ነበር የተዘጋው። የተነገረንን ምልክት ስናገኝ ያ ባለፈው ኮምፕሌን ሲያደርግ የነበረው ጓደኛችን ቀድሞ ደርሶ ስለነበር ደውለንለት ወጥቶ ተቀበለን። ከሱ ጋር ውስጥ ስላለው ድባብ፣ ማን ማን እንደመጣ፣ ምን እንዳመለጠን እየጠየቅን... ምን ሲያንጦሎጥል አስቸኩሎ አመጣሽ ብለን እየወቀስን ወደ ውስጥ ዘለቅን። ግቢው ውስጥ ስንገባ ሁለት ወጣቶች ሂሳብ እየተቀበሉ ነው “ለቦተም”

አይቀንስም ወይ እያልን ቀልደን ሂሳባችንን ከፈልን። እኛ እንደገባን ሌሎች ሁለት ልጆች ሲገቡ ፍተሻ አለ ብዬ ፍተሻ አይሉት ዳበሳ ነካክቼ አስገባኋቸው። በኔ ሁኔታ እና በልጆቹ የዋህነት ጓደኞቼ እየሳቁ ነበር። ትንሽ እልፍ እንዳልን አዘጋጇን አገኘናት። ከደቂቃ በፊት እንደዛ ስንቦጭቃት እንዳልነበር ልክ ሰናያት ቆንጆት ብለን ጥምጥም ብለን ሰላም አልናት። እሷም ጉንጭ ጉንጫችንን ስማ ከመሃል የማታውቀውን ደሞ እጇን እስማ አስገባችን።

እኛ ስንደርስ ከኛ ቀድመው የደረሱ ሰዎች ቦታ ቦታቸውን ይዘዋል። ግቢው ሰፊም ጠባብም አይባልም። ሰዎች እዚም እዛም አሉ። የመማሪያ ክፍሎቹ የዛን ለት “ሮላቸውን” ቀይረው ግማሹ የአዘጋጆቹ እቃ ማስቀመጫ፣ ግማሹ ሺሻ ቤት ግማሹ ዳንስ ፍሎር ሆነዋል።

ወደ ውስጥ ስንዘልቅ የሺሻ ክፍሉ እና የዳንስ ቤቱ በሰዎች ጢም ብሎ ሞልቷል። ቀሚስ የለበሱ፣ ዊግ ያደረጉ፣ በፒኪኒ ፓንትና በሂል የሚውረገረጉ… ደሞ ገና ጀማሪዎች ሂል ጫማ አድርገው የማያውቁ እየተወለጋገዱ የሚሄዱ ጀማሪ ልጆች… ጨበሬ ርካሽ ዊግ … ጥሩ ተደርጎ የተሰራ ዊግ… የተለደፈ ሜካፕ… የውበት ባለሞያን የሚያስንቅ ሜካፕ ሁሉም አይነት አለ። የሚጠጣ ነገር የያዙ ቆነጃጅት ምን እንዳስቸኮላቸው እንጃ ከግራ ወደ ቀኝ በፍጥነት ይራመዳሉ። ግማሹ ዳንስ መድረኩ ላይ ይውረገረጋሉ። ቀጭን፣ ወፍራም፣ አጭር፣ ረጅም ልጅ እግር፣ ሽማግሌ ሁሉም አለ። ሁሉም ከመሰሉ ጋር እየተዝናኑ ነው። በየመሃሉ አዘጋጆቹ እየመጡ አሉባልታ ይነግሩናል። ብቻ ግቢውም ሆነ ቤቱ በአጠቃላይ በሳቅ ጨዋታ ተሞልቷል። በዚህ መሃል እኔ አብሬ ከመጣኋቸው ጓደኞቼንና እዛ ካገኘኋቸው ጓደኞቼ ሹልክ ብዬ ጠፍቼ ውስጥ ውስጡን ማሰስ ጀመርኩ።

አሁን ሰአቱ እየገፋ የምንጠጣው መጠጥም ስራውን እየሰራ ነበር። ቤቶቹ ብርሃን አላቸው ለማለት በሚያሳቸግር ደብዛዛ አምፖሎች የተሞሉ ነበሩ። የሰውን ሙሉ ገፅታ ለመለየት ትንሽ አስቸጋሪ ናቸው። እኔ ቤት ውስጥ ገብቼ አሁን ላይ በቁጥር ከማላስታውሳቸው ሰዎች ጋር ዳንስ ፍሎር ላይ ስደንስና ስላላስ ነበር። ብቻ የሆነ ግዜ ላይ የሆነ ከንፈር ላይ ስደርስ እስታውሳለሁ። እስካሁን ከሳምኳቸው ከንፈሮች ይለያል። ከሱ ጋር መለያየት አልፈለኩም። ተጣብቄ መቅረት አማረኝ። ደብዛዛው ብርሃን ከመጠጥ ጋር ተደማምሮ ማንነቱን ባያሳየኝም ቁመናው ጥሩ ከሆነ ወጣት ጋር ነበር ስላላስ የነበረው። መሳሳማችንን አቁመን ትንሽ መወዛወዝ ስንጀምር ልጁ እኔ ጥሎ ከሆነ ነጭ ጋር

ተጣበቀ።

በዓይን ብጠራው ዓይኔ ቢንከራተት ልጁ ተመልሶ አልመጣ አለኝ። በዚህ መሃል ከዚህ በፊት ከማውቀው ልጅ ጋር ተገናኘን። ያኛውን ልጅ ለማስቀናት ከዚህኛው ልጅ ጋር መሳሳም ጀመርን። ልብ በሉ አሁን እኩለ ለሊት አልፏል። መጠጡ ሲጋራው እና ዊድ ስራቸውን እየሰሩ ነው። ከዚህኛው ልጅ ጋር የጠበቀ ነገር ባይኖረንም አልፎ አልፎ ስንገናኝ ግን እንሳሳማለን። ከዛ የዘለለ ነገር የለንም። ዛሬም ያንን እያደረግን ነው። ዳንስ ፎሎር ላይ የጀመርነውን መሳሳም ወደ መፀዳጃ ቤት ይዘነው ሄድን። አገር ሰላም ነው ብለን በሩን ከውስጥ ዘግተን መሳሳም አይሉት መላላሳችንን ቀጠልን።

በዚህ መሃል በር ላይ በአዘጋጆቹ እና የመግቢያ ክፍያ ሳንከፍል እንግባ በሚሉ ሰዎች መሃል ቅልጥ ያለ ፀብ ተፈጠረ። ውጪ ያሉት ሳንከፍል እንግባ ውስጥ ያሉበት በር ዘግተው አናስገባም። ይሄኔ ውጪ ያሉት ድንጋይ ወደግቢው መወርወር ጀመሩ። ግቢ ውስጥ እዚም እዛም የነበሩት እየተሯሯጡ ወደ ቤቶች ውስጥ ገቡ። ግማሹ ፈርቶ ፓርቲውን አቋርጦ ከግቢው ወጣ። ይሄ ሁሉ ሲፈጠር እኛ መፀዳጃ ቤት ውስጥ ሌላ አለም ላይ ነ።

ጣጣችንን ጨርሰን ለመውጣት በሩን ለመክፈት ስንሞክር የበሩ ቁልፍ አልከፈት አለን። አሁን ፀቡ ትንሽ ጋብ ስላለ በሩን ከውስጥ ስንደበድብ የፓርቲው ታዳሚ ከውስጥ ሌላ ነገር እያደረግን መስሎት በሩን ከመክፈት ይልቅ ቆሞ ያዳምጣል። ግቢው ውስጥ ያለው ሰው ባጠቃላይ ቀልቡን ወደ እኛ መልሷል። በስንት መከራ የፓርቲው አዘጋጅ ጉዳዩን ሰምታ መጣች። እሷ ከውጪ ልትከፍት ብትሞክር እምቢ አላት። ትንሽ ካረጋጋችን በኋላ ቢላ ፈላልጋ በሩን ፈልቅቃ አሰወጣችን። የመፀዳጃ ቤቱ ደጃፍ በሰው ተሞልቶ በሳቅ ተቀበሉን። ዋክ ኦፍ ሼም ማለት ይሄም አይደል?

ስንወጣ ተፈጥሮ የነበረውን ነገር ሰማን። ጓደኞቻችንን በዓይናችን ፈልገን ስናጣቸው ተያይዘን እነሱን ፍለጋ ወደ ውጪ ወጣን። ትንሽ እንደሄድን ግቢ ውስጥ የጀመርነውን መሳሳም ስወር ያለ ስፍራ ፈልገን ደገምነው። ከዛ ስንወጣ ላዳ ታክሲ ሲያልፍ አግኝቶ አብሮኝ የነበረው ልጅ ገባ። እኔም ቀበቶዬን አጠባብቄ መንገዱን ስሻገር ከታች ረብሻ ሰምተው የሚመጡ ፖሊሶች አስቁመው በጥያቄ ያጣድፉኝ ያዙ። ይሄኔ አብሮኝ የነበረው ልጅ ጎመን በጤና ብሎ ላዳውን አስነስቶ ሄደ።

እኔ ከፖሊሶቹ ጋር ስጨቃጨቅ ውስጥ ያጣናቸው ጓደኞቼ መደወል ጀመሩ። ስልኬን አላነሳም። ደጋግመው ሲደውሉ ውጪ ነኝ ስል አንዱ ጓደኛዬ መጣ። እሱንም እዛው ፖሊሶች ያዙት። እሱ ሲቆይ ሌላኛው ጓደኛችን ትንሽ ቆይቶ መጣ እሱንም ፖሊሶች ይዘው ወደ ፖሊስ ጣቢያ ወሰዱን። እዛ ትንሽ ምርመራ ከተደረገብን በኋላ የስራ መታወቂያችንን አሳይተን እኛ የጓደኛችንን ልደት ልናከብር መምጣታችንን ምለን ተገዝተን ተናግረን ለቀቁንና ወደ አንደኛው ጓደኛችን ቤት ለማደር ሄድን። ይሄኔ ስካራችን ለቆናል። ላዳ ውስጥ ሆነን ወደቤት እየሄድን የተፈጠረውን ነገር አንስተን ስንት ሰራ የስራ ጉሮሮአችን እስኪሰነጠቅ ሹፌሩ እስኪረበሽ እየሳቅን ቤት ደረስን። ተሰብሰበን ተኝተን ሃሳቤ ቀጣይ ፓርቲ ላይ ነበር.........።

እንዴ አለመያዝ ነው ማለት ይሄም አይደል?

# ሁሉ በእጄ

**መንደርደርያ፥**

ድሮ ድሮ ከአዳዲስ ሰዎች ጋር ለመተዋወቅ አጋጣሚዎች ቀላል አልነበሩም።በጓደኞቻችን አማካኝነት ወይም ከግዜ ጋር የሚቀያየሩ ምልክቶችን በመለዋወጥ ነበር ሰዎች አዳዲስ ጓደኝነቶችንና ግንኙነቶችን የሚመሰርቱት። እነዚህ ቅርርቦች ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ ይመጡ ስለነበር ነገሮች ወደ አልጋ ከመድረሳቸው በፊት ጥቂት የመተዋወቂያ እድልን ይሰጣሉ።

ዘመናዊነት ተስፋፍቶ ዓለም አንድ በሆነችበት በዚህ ዘመን ነገሮች ሁሉ መዳፋችን ላይ ባለው ስክሪን መከወን እንችላለን። ይህ ዘመናዊነት የስራና የማህበራዊ ህይወታችንን ብቻ ሳይሆን የወሲብ ህይወታችንንም በእጅጉ ቀይሮታል። በሻይ ቡና ተጀምሮ በእግር መንገድ ቀጥሎ የሚደረጉ ጅንጀናዎች አሁን አሁን ግዜያቸው አልፏል።

እኛም የዜጋ ባህል (ኩዊር ካልቸር) የሚል ርዕስ አንስተን በአብዛኞቻችን ተወዳጅ ስለሆኑትና በሰፋት ጥቅም ላይ ስለሚውሉት መተግበሪያዎች ሳናወራ ማለፍ አንችልም። እነዚህ መተግበሪያዎች የዜጋውን የዴቲንግና የወሲብ ቅርጽ በእጅጉ ለውጠውታል። በአብዛኛው ግዜያዊ የወሲብ ግለትን ለማብረድ ነው ምንጠቀምባቸው። እነዚህ መተግበሪያዎች ቀጣዩ የቁላ መዳረሻችንን በእጅጉ አቅርበው ሁሉም ነገር ከሁለትና ከሶስት ቃላት ባላለፈ ንግግር ልንከውን አስችለውናል። አልፎ አልፎም ቢሆን ጥሩ ጓደኝነትንና ወዳጅነትንም እንመሰርትባቸዋለን።

ህይወትን ያቀለሉት እነዚህ መተግበሪያዎች አንዳንዴ ህይወታችንን አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ድፍረት ይሰጡናል። ከዚህ በታች ያሉት ታሪኮችም ይህን በአጭሩ እንድንረዳው የሚያስችሉን ናቸው። ታሪኮቹ ከተለያዩ ሁለት ግለሰቦች ጋር ካደረኩት ቆይታና አንድ በድምፅ የተላከልንን ታሪክ ወደ ጽሑፍ ቀይረን ያዘጋጀናቸው ናቸው።

## ሳሚ

እንተ/እሱ

የ26 ዓመቱ መልከመልካም ሳሚ በአንድ ወቅት ያጋጠመውን ገጠመኝ እንዲህ ሲል ያስታውሰዋል። ክፍለሃገር ለስራ ቆይቼ መመለሴ ነው። ቤቴ ስደርስ አመሻሽ ሆኗል። ከተረጋጋሁ እና አንዳንድ የግል ነገሮችን ከከወንኩ በኋላ ስልኬን አንስቼ በብዛት የምጠቀመውን የሆካፕ መተግበሪያ ከፍቼ መጀናጀን ጀመርኩ። ሰፈሬ ከመሃል ከተማ ትንሽ ወጣ ስለሚል ይሁን ወይ በአጋጣሚ ለኔ ሰፈር ቅርብ የሚሆን ሰው ኦንላይን አልነበረም። ብቻ ከዚም ከዛም ጋር ስወዛገብ ሰዓቱ እኩለ-ለሊት ደረሰ። ከዛ የሆነ ልጅን እያወራሁ የሚልክልኝ ፎቶዎች ስሜቴን ከምለው በላይ ያግሉት ጀመር። ቆይቼ የመጣሁበት ክፍለ ሃገር ሰው አግኝቼ አለማወቁ ተደራርበው ስሜቴ ጣራ ነካ። ትንሽ እንዳወራን አድራሻውን ልኮልኝ ና አለኝ። ለሊት ከእንቅልፉ የነቃ ቅንዝራም ነው .... እኔስ ማን ነኝ?

እሱ የሚኖርበት ሰፈር ሩቅ መሆኑን ብረዳም እንቢ ማለት አልፈለኩምና ተነስቼ ለመሄድ መዘገጃጀት ጀመርኩ። በጊዜ ከብልቴ ውጪ ሌላ አካሌ ስራ ያቆመ ይመስል ማሰብ አልቻልኩም። ራይድ ጠርቼ መንገድ ስጀምር ነው ትንሽ ድንጋጤ ይሰማኝ የጀመረው። በምልክት የጠቆመኝ ሰፍራ ስደርስ ስልኬን አብርቼ እንደተቃረብኩ ቴክስት አደረኩለትና ወርጄ ጠበኩት።

አሁን የምር ደንግጬአለሁ። ከሰፈሬ በጣም ሩቅ መንገድ ነው የመጣሁት። መሃል ከተማ እና ዋና መንገድ ላይ መሆኔ እያሰብኩ ትንሽ ተፅናናው።

በምልክት የነገረኝን ልብስ የለበሰ ሰው ሲመጣ አየሁት። እውነት ለመናገር ከሱ እና ውር ውር ከሚለት ባለቤት አልባ ውሾች በቀር መንገድ ላይ ምንም የለም። ሰአቴን አየሁ ለሊት 7:45። ሰውዬው አጠገቤ ደርሶ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ልብ ብዬ በቅርበት ሳየው ከላከልኝ ፎቶዎች ጋር መሰረታዊ ባይሆንም የተወሰነ ልዩነት እንዳለው ገባኝ። በደንብ የተወለወሉ ፎቶዎች ነበር የላከልኝ። ብቻ ይሁን። በእሱ መሪነት ወደ ቤቱ መሄድ ጀመርን።

የተገናኘነው ካዛንቺስ ቶታል ጋር ሲሆን፤ የፊት ለፊት መንገዳችንን ይዘን፤ በእንደራሴ ወደ መገናኛ የሚይዘውን መንገድ ይዘን ትንሽ

እንደተራመድን ወደ ውስጥ የሚያስገባ መንገድ ውስጥ ገባን። አሁን ልቤ ፈራ። መንገዱ እጅግ በጣም ጠባብ ነው። በአንድ ጊዜ ከአንድ ሰው በላይ የማያሳልፍ አይነት ጠባብ በዛ ላይ ምንም አይነት መብራት የለም። የመንገዱ ቅጥነት በዛ ላይ ጠመዝማዛነት በዛ ላይ ኮረኮንች አይሉት ንጣፍ ድንጋይ ለመሄድ አይመች። ልቤ በአፌ ልትወጣ ሆነ። ቅንዝሬን ረገምኩት። ለኔ አንድ ስአት በእውኑ ለ 5 ደቂቃ ከሄድን በኋላ አልደረስንም አልኩት ትንሽ ይቀረናል አለኝ። ሁለቴ ሶስቴ ተመሳሳይ ጥያቄ ጠይቄ ቆይ ትንሽ ተብዬ ራሴን የሆነ ካርታና ፕላን የሌለው በደሳሳ ቤቶች የተሞላ ሰፈር ውስጥ አገኘሁት። አሁን ልመለስ ማለትም አልችልም። ለሱም ረፍዷል።

ብቻ ከሆኑ ብዙ ደቂቃዎች በኋላ ቤቱ ደረስን። ከውጪ የተቆለፈውን የላሜራ በር ከፍቶ ሲገፋው ከውስጥ ተቀርቅሯል። የበር ድምፅ የሰሙ ውሾች ከውስጥ ጩኸት አሰሙ ይሄኔ ሰፈር ውስጥ የነበሩት ውሾች እየተቀባበሉ ሰፈሩን በጩኸት አናጉት። የባለቤትየው ልጅ መሰለችኝ መታ በሩን ከውስጥ ከፍታ አስገባችን። አካኋኗ ከእንቅልፏ በመቀስቀሷ በፍፁም ደስተኛ እንዳልሆነች ያሳብቃል።

ወደ ውስጥ ገብተን በማይመች መንገድ መሄድ ቀጠልን። ጊቢው ጠባብ ቢሆንም ሁሉንም አይነት የመሬት አቀማመጥ ይዟል። ተራራ አለው ሸለቆም አለው። ከዋናው ቤት በስተግራ ከተደረደሩት ከሶስት በላይ ሰርቪስ ቤቶች መሃል ላይ ያለውን ከፍቶ ገባን። እፍን ያለ እምክ እምክ የሚል ሽታ ተቀበለን። በጣም ጠባብ ቤት ነው። በግራና በቀኝ ካሉት ቤቶች ጋር በችፑድ ነው የተከፈለው። በፍፁም ድምፅ ላያስተላልፍ አይችልም ብዬ እያሰብኩ እያለ ከአንደኛው ክፍል የማንኮራፋት ድምፅ ሰማሁ። ብዙ ጊዜ ሳናባክን ቲቪውን ድምጽ ከፍ አድርጎ ከፈተው እና ወደ ጉዳያችን ገባን። ምንም አይነት ድምፅ ላለማሰማት እየጣርን በምልክት እየተነጋገርን ጣጣችንን ጨረስን።

አሁን ወደ ቀልቤ ስመለስ እዚህ ቤት ማደር እንደማልችል ገባኝ። መታጠቢያ የለም። ጭክ ብሎ ማስነጠስ ራሱ አይቻልም። ስአቴን ሳይ ለሊት 8:24። ወደ ቤቴ ልሂድ አልኩት። አይ እደር ብሎ ትንሽ አንገራገረ። እንደ ወሰንኩ ሲረዳ እሺ ግን እኔ አልሸኝህም አለኝ። በር ድጋሚ ማንኳኳት አልፈልግም ነው ምክንያቱ እሺ ብዬ ራይድ ጠርቼ ግባ ብለው እምቢ አለኝ። ለመሄድ ደሞ ልቤ አንዴ ተነሳስቷል። ሁለት ሶስቴ ራይድ ብጠራም ሁሉም ወደ ውስጥ አንገባም ሲሉኝ በቃ ዋናው መንገድ ላይ ልውጣ ብዬ ወጣሁ። እሱ እስከ ዋናው በር አደረሰኝ።

የመጣሁበትን መንገድ ብቻዬን ሩጫ አይሉት እርምጃ ሄጄ ዋናው መንገድ ደረስኩ።

ራይድ ውስጥ ገብቼ ወደ ቤቴ መንገድ ስጀምር ብዙ ሃሳቦች ወደ አይምሮዬ ውስጥ መጡ። እርፌ ቤቴ ባድርስ? ነገ በብርሃን ሰው ባገኝስ? ከመጣሁ እዛው ባድርስ? ክፉ ነገር በመንገዴ ቢገጥመኝስ እያልኩ ቤቴ ደረስኩ።

እንዲህ አይነት የለሊት ጉዞዎች አብዛኞቻችን አድርገናል። ከቤታችን ወይም ከምንዝናናበት ቦታ በአጭር የጽሑፍ ልውውጥ በቀጥታ ወደ እንግዳ ሰዎች ቤት ወይም የመኝታ ክፍል እቅንተን እናውቃለን። ከረጅም አመታት በፊት አንድ ወዳጄ ያጫወተኝን አጋጣሚ ላካፍላችሁ።

## እዮብ

አንተ/እሱ

ስራዬ ቦሌ አከባቢ ነው። የዛን-ለት ማታ ከጓደኞቼ ጋር ተገናኝተን ራት ለመብላት ቀጠሮ የነበረን ቢሆንም ቅንዝር አናቴ ላይ ስለወጣ እነሱን ሰርዤ ስልኬ ላይ ተጣድኩ። ብዙ ሰው መሰመር ላይ ነበር ምርጫዎቼን እጥብቤ እጥብቤ ከአንድ ሁለቱ ጋር ማውራት ቀጠልኩ። እኔ ከቤተሰብ ጋር ስለምኖር የማዋራው ሰው የራሱ ቤት ሊኖረው ይገባል። አንደኛው በዚህ መስፈርት ወድቆ ከሌላኛው ጋር ከእድሜ እስከ ቁመት፣ ከመልክ ከለር እስከ የአልጋ ላይ ሚና የጽሑፍ እና የእሃዝ ጥያቄና መልስ ካደረግን በኋላ ፎቶ ተለዋወጥን። የፊት፣ የቁላ፣ የቂጥ የሰውነት የቀረን ፎቶ አልነበረም። ተገማግመን አንዳችን የአንዳችን ምርጫ መሆናችን ካረጋገጥን በኋላ ማታ ሶስት ሰአት እሱ ከጂም ሲወጣ አብረን እሱ ቤት ለመሄድ ተሰማማን። ሰአቱ እስኪደርስ እኔ ቤት ደውዬ ዛሬ ውጪ እንደማድር ተናግሬ ቢሮ ሆኜ ስልኬን መነካካት ቀጠልኩ።

ከጂም ሲወጣ ከነበርኩበት ሊያነሳኝ እየመጣ ስለሆነ ወጥቼ እንድጠብቀው መልእክት ላከልኝ። ቢሮዬን ቆልፌ እየወጣው ያ ስሜት ተጫጫነኝ። ሁሌ አዲስ ሰው ላገኝ ስል ክብድ ሚለኝ ነገር አለ። ፎቶው የውሸት ቢሆንስ? የማውቀው ሰው ቢሆንት? ብላክ ሜል ቢያደርገኝስ? መጥፎ ሰው ቢሆንስ የሚሉ ክፉ ክፉ ሃሳቦች ውልብ ይሉብኛል። እንደምንም ሃሳቤን ተጋፍቼ ላገኘው ወደ ውጪ ወጣሁ።

ምንም ያህል ሳያስጠብቀኝ መጥቶ መኪናውን አጠገቤ አቆመው። በሩን

ከፍቼ ወደውስጥ ስገባ በፎቶ ያየሁት ራሱ ነው። ትንሽ ቀለል አለኝ። እንስቶኛ ወደ እሱ ቤት ጉዞ ቀጠልን። ከከተማ ወጣ ብሎ ስለሚኖር ጉዞአችን አጭር አልነበረም። እተኩሬ ሳየው አውቀዋለሁ። ከረጅም አመታት በፊት አጊንቼው ነበር። በመሃላችን ምንም ሳይፈጠር ሻይ ጠጥተን ነበር የተለያየነው። ብዙም ወሲባዊ መሳሳብም ሆነ ለጓደኝነት የሚበቃ ጥንስስ ስላልነበረን ደግመን አልተገናኘንም። ይህን እንስቼ ስጠይቀው እሱ እንደማያስታውሰው ነግሮኝ ጉዞአችንን ቀጠልን።

ቤቱ የተንጣለለ ሰፊ ዘናጭ አፓርትመንት ነው። እንደገባን ውሃ ቀድቶልኝ ወደ መኝታ ቤቱ ገባ። ብዙ ክፍሎች ስላሉት የትኛው ክፍል እንደገባም አያስታውቅም። ሲመለስ ልብሱን ቀይሮ ለኔም ይዞልኝ ነው የመጣው። እራት እስካሞቅ ልብስ ቀይር አለኝ። እኔ ቅድሚያ መታጠብ መርጨ ያመጣልኝን ልብስ ተቀብዬ ወደ እንግዳ መታጠቢያ ቤት ገባሁ።

ስወጣ ምግብ አቀራርቦ ቲቪ እያየ ነበር የጠበቀኝ። አጠገቡ ቁጭ ብዬ መብላት ጀመርን። ሊያጎርሰኝ ሲሞክር ጉርሻ አልወድም ብዬ አስቆምኩት። ገበታው ከፍ እንዳለ ይተሻሸኝ ጀመር። እኔ ለምን እንደሆነ አላውቅም የሆነ ነገር ቀፎኛልና ተው እያልኩ ገፋ አደርገዋለሁ። ተነስቶ ለራሱ መጠጥ ሊቀዳ ሲነሳ አይኔ የሆነ ነገር ላይ ተተክሎ ቀረ። በቲቪው እና በውስኪ ማስቀመጫው መሃል ላይ ካሜራ አለ። አይኔ የካሜራውን ገመድ ተከትሎ ሲሄድ ተሰክቷል። ድንጋጤዬ ጨመረ። ቀስ ብዬ ከተቀመጥኩበት ተነሳሁና ሌላ ቦታ ቁጭ አልኩ። እንዴ የማይሆን ነገር ያየው አይኔ ማረፍ አቃታው። አሁን ቁጭ ካልኩበት ወንበር ፊት ለፊትም ካሜራ አለ። አሁን ለየልኝ። መጠጡን ይዞ ሲመለስ ቤትህ ካሜራ ብቻ ነው አልኩት። ቀለል አድርጎ አዎ ለሌባ ነው አለኝ። እኔ ግን ካሜራዎቹ የተቀመጡበት አንግል ለሌባ አልመሰል ስላለኝ ተነስቼ ቤቱን ማማተር ጀመርኩ። የተለያየ ቦታ የተቀመጡ ስድስት ካሜራዎች አሉ። ግራ መጋባቴን ሲያይ ና መኝታ ቤት እንሂድ አለኝ። ኮስተር አለማለቱ ትንሽ ረጋ ቢያደርገኝም ፍርሃቴ ግን አልቀነሰም። መኝታ ቤቱ ሰፋቱ ለጉድ ነው በዛ ላይ የጌጣጌጡ ብዛት። እዚህ ክፍል ካሜራ የለም ብዬ ማመን ከበደኝ። እዚህ ክፍል አላድርም አልኩትና ምክንያቴን ነገርኩት። ምሎ ተገዝቶ የለም አለኝ። እኔ በጭራሽ እዚ አላድርም ብዬ በአቋሜ ጸናሁ ።

ሌላ ክፍል ወሰደኝ እዛም አልጋ ምናምን አለ። እኔ እምቢ አልኩ። አንድ ተዘግቶ የቆየ ባዶ ክፍል ወሰደኝ። ይሄ ይሻላል አልኩት። ክፍሉ ከመብራት ውጪ ምንም የለውም። ባዶ ነው። ከአንደኛው ክፍል ፍራሽ አምጥተን አዳራችን እዛች አዋራም ክፍል ሆነ።

ወደ ቤቴ ተመልሼ መሄድ እችል ነበር ግን አንድ አንድ ጊዜ በአይምሮኣችን ሳይሆን በቁላችን ምናስብበት ወቅት ላይ ስንሆን እንዘናጋለን። እሱም ምቾት የሚነሳ ነገር አላሳየኝም፣ ለምን ያን ሁሉ ካሜራ እንዳስቀመጠ ስጠይቀው የሰጠኝ ምክንያት ባያሳምነኝም የሚፈራ አይነት ሰውም አልነበረም።

እና የዛን ለት እዛች ክፍል ውስጥ መልካም ምሽት አሳልፌ በንጋታው ወደ ቤቴ አቀናሁ። አሁን ሳስበው ድፍረቴ ትንሽ የበዛ ይመስለኛና ደነግጣለሁ።

## ቢኒ

እንተ/እሱ

መለመላዬን ከአራተኛ ፎቅ ላይ እየበረርኩ ስወርድ ከታች ያሉት ዘበኞችና በማስማው ድምጽ የተረበሹ የአልጋ ቤቱ ተከራዮች እብድ መስያቸው ደንግጠው ነበር ሚያዩኝ። እንደምንም ሃፍረተ ስጋዬን በእጆቼ ደብቄ የዘበኞቹ ቤት ከገባሁ በኋላ በውሸት የተለወሰ እውነቴን ማስረዳት ጀመርኩ።

ቢኒ እባላለሁ ተወልጄ ያደኩት አዲስ አበባ ሲሆን በስራ ምክንያት ላለፉት አምስት ዓመታት ከአዲስአባ ውጪ ነበርኩ ። ይህ ክስተት ሲፈጠር በስራ ምክንያት የተወለድኩባትን አዲስአባን ጥዬ ወደክሃለሀገር ካቀናው ስድስት ወር እከባቢ ሆኖኝ ነበር። የአዲሳባን የዜጋ ህይወት በተቀላቀልኩ በአጭር ጊዜ ወደ ክፍለሃገር መምጣቴ ብዙም አላስደሰተኝም ደግነቱ ከሸገር በቅርብ ርቀት ላይ ስለነበርኩ በሳምንት ወይም ቢበዛ በሁለት ሳምንት እንዴ እመላለስ ነበር። ለስራ የሔድኩባት ከተማ ትንሽ ባትባልም ሰፊ ግን አይደለችም። እንደልብ ሰው ማግኘት ያስፈራል ለዛ ወደ አዲስአባ ስመጣ ነው ሰው ማገኘው።

አዲስአበባ ስመጣ ከቤተሰብ ይልቅ በቅርብ ካወኳቸው ዜጋ ጓደኞቼ ጋር ነበር ብዙ ጊዜ ማሳልፈው። በዚህ መሃል ነበር አዲስ የመጣ hookup app እንደመጣ ነግረውኝ የተቀላቀልኩት። እካውንት እንደከፈትኩ ከብዙ ሰው ጋር ባወራም ማንንም ሳላገኝ ወደ ስራ ቦታዬ ተመለስኩ። አፑ ገና አዲስ ስለነበር እኔ የነበርኩበት አከባቢ ሰው የለም ስለዚህ እዛም ሆኜ የማወራው አዲስአበባ ከነበሩ ዜጎች ጋር ነበር። በዚህ መሃል ከአንዱ ጋር በጣም ተግባብተን ስልክም ተቀያይረን ማውራት ጀመርን።

በሚቀጥለው እኔ ወደ አዲሳባ ስመጣ እሱ አልጋ ይዞ ሊጠብቀኝ እና ቀጥታ እሱን እንዳገኘው ፕላን አድረገን ነበር። በቀጠሮአችን እለት ለጊዜው ትዝ የማይለኝ ነገር ቤት ተፈጥሮ መጀመሪያ ቤት መሄድ ነበረብኝ። ቤት ገብቼ የነበረብኝን ጉዳይ እስክጨራስ ጊዜው ረፈደ እና እሱን የማገኘው በማታ ሆነ።

ቀድመን ያሰብነው ነገር በአጋጣሚ ስላልተሳካ ወደ ሩም እንድመጣ ተነጋግረን ወዛ ሄድኩ። ስደርስ በሩን የከፈተልኝ ሰውና ያወራሁት ሰው የተለያዩ ናቸው። መጀመሪያ ቁጥር ተሳስቼ መስሎኝ ነበር ከዛ ስሜን ጠርቶ ሲያናግረኝ ነው የላከልኝ ፎቶ የውሸት እንደሆነ የገባኝ። ግር ግር ላለመፍጠር ወደ ውስጥ ገብተን ብናወራ ይሻለል ብዩ ገባን። ለምን እንደዛ እንዳደረገ ምክንያቶቹን ነግሮኝ ካወራን በኋላ እኔ ወደቤቴ ተመልሸ መሄድ እንደምፈልግ ነገርኩት። በመሃል መሳሳም ጀመርን እኔ ትንሽ ብግደረደርም እንቢ የማለት አቅም አልነበረኝም። ወንድ ከሳምኩ ቆይቼ ነበር።

ነገሮች እየተጋጋሉ መጥተው ወደዋናው ነገር ልንገባ ስንል ኮንዶም እንዲያደርግ ነገርኩት። በባዶ ማድረግ እንደሚወድ ነገረኝ። እኔ ድጋሚ አለሳልሼ ለጥንቃቄ ለዛሬ በኮንዶም እንድናደርግ ስነግረው እሱ በእምቢታው ፀና። እኔም የዛኔ ጥርጣሬዬ አየለና እምቢ አልኩት። የዛኔ ነበር ሃይለቃል መናገር የጀመረው እና በጉልበት ሊገናኘኝ የሞከረው። በጉልበት ታግሎኝ ሲያቅተው የአልጋውን ራስጌ መሳቢያ ከፍቶ ሽጉጥ አወጣ። ምን እንደምሆን ግራ ገባኝ። አሁን ሰውዬው ጤነኛ እንዳልሆነ በአይምሮዬ ወሰኛለሁ። እንዴት አድርጌው እንደማረጋጋው ግራ ገባኝ።

እሺ ሽጉጡን አስቀምጥ ካለኮንዶም እናደርጋለን ቅድሚያ ግን ልፀዳዳ ስለው ተስማማ። ይህ የሆነው ምናልባትም ከሃያና ስላሳ ደቂቃ ልመና በኋላ ነው። አሁን ትንሽ የተረጋጋ ይመስላል። ወደ መፀዳጃ ቤት ገብቼ ውሃውን ከፍቼ ትንሽ ካሰብኩ በኋላ ወጣሁ። እሱ ሽጉጡን አስቀምጦ ጋለል ብሎ ስልኩን እየጎረጎረ ነበር። የመውጫው በር ከሻወር ቤቱ ጎን ስለነበር በፍጥነት በሩን ከፍቼ ደረጃውን እየሮጥኩ ጥበቃዎቹ ቤት ደረስኩ። መለመላ ራቁቴን ነበርኩ። ቂጤን እና ብልቴን በእጆቼ ሸፍኜ በውሸት የተለወሰ እውነቴን መናገር ጀመርኩ። በዚህ ሰዓት ደረጃውን ስወርድ በተፈጠረው ድምፅ ተረብሸው ከየክፍላቸው የወጡ ሰዎች ነበሩ። ብቻ የተወሰነ ግር ግር ነበር።

በስራ ምክንያት የማውቀው ሰው እንደሆነና አሁን ግን ወደ ሩም ከገባው

በኋላ ሁኔታው እንዳላማረኝ ለዘበኞቹ ተናግሬ ልብሴን እንዲያመጡልኝ ለመንኳቸው። የያዘው ደብል አልጋ ስለነበር ነገሮች ብዙ አልተወሳሰቡም እኔም ስለ ሸጉጡ ማውራት አልፈለኩም። ዘበኞቹ ወንድ ከወንድ ጋር ባይሆንም ወንድ እና ሴት ጋር እንደዚህ አይነት ግር ግር እና ጭቅጭቅ ስለለመዱ ብዙም ሳያጨናንቁኝ አንደኛው ሄዶ ልብሴን አመጣልኝ። እኔም ለዘበኞቹ ቲፕ ሰጥቼ አልጋ ይዘው የነበሩ ሰዎች አይን እየገረፈኝ ልብሴን ለባብሼ ባገኘሁት ላዳ ወደቤቴ ላጥ አልኩ።

# DUALITY

**Zaytun**
She/Her They/Them That/Girl

Upon my first trip to Addis, I intentionally sought out queer community. A simply curious person who was new to this city, there was no way for me to navigate getting in contact with a community that was hiding in plain sight... so I called upon my queer ancestors, wrote down all of the qualities of the people I was interested in meeting, and let the energy of this chaotic city do the conjuring.




The domino effect began, I met one person who introduced me to another person, then another and another until I was at my first queer house party with my new found friends. The front porch was lined with patio chairs, some being occupied by boys giving each

other lap dances, one in which you would later find me discreetly stroking someone's pussy. Dabo kolo was intentionally placed in small bowls around the house, pizza and drinks were in the kitchen where a spotify playlist was competing with a youtube playlist, and beyonce was competing with afro beats.. Imagine, here I was a few weeks into my introduction to Ethiopia and I was in an exclusive space with the exact people I was told didn't exist. This old villa bet had been turned into our safe haven, even if only for a few short, horny hours... It was my dream come true.

"Who taught you to fear me? Was it the same person who taught you to fear God?" I wrote in a notebook recently.

The homo erotic essence of this city is so confusing, tormenting at times even. The men you see sharing openly intimate moments in the streets, holding pinkies, laying in each other's laps like long lost lovers from romance novels. Witnessing them share this degree of open, loving touch, it's hard to imagine they aren't openly gay themselves, until you catch the jealousy that slicks their tongues before they dare to call a more outwardly feminine, male bodied stranger "booshti", or label the girl who doesn't fit this society's ideas of femininity a lesbian. The way blood rushes to their genitalia as they incite violence on their kin. The self-hatred. The repression. The constant agitation of stradling the territories of both hyper visibility and invisibility in a country like Ethiopia that doesn't care if you're alive or dead, just that you played by the rules.

As a parent, my fears and hopes now extend beyond my physical body to an innocent soul. Sometimes I watch over my sleeping child, a sweet angel, who most people assume is of the opposite "gender"; I can't help but think of how to strategize for his future. Growing

up in Ethiopia, categorized “boy”, raised in a non-traditional household, steeped in alternative cultures & communities. I wonder in which ways he will be able to engage in an openly intolerant society without internalizing bits of it. I wonder if shame will overcome him as it had me, the stress of conformity, the soreness of always standing out.

I find myself calling upon his angels and ancestors, as I had once done for myself; that they cover him and provide him with the mental fortitude, awareness, and an unwavering commitment to be himself in all ways, always.

Haadhaa fi lafatu nama danda’a

Mother and ground hold everybody

As I send these prayers up, not only for my child, but for our society as a whole, I envision a people at peace with themselves. Peace for every person who has never felt permitted to express themselves in the ways that they crave; to explore and be themselves, free from shame. Freedom to love themselves, and whoever they desire, consensually, without fear.

**የይዘት ማስጠንቀቂያ**፥ መጋለጥ እና ራስን ስለማጥፋት ስለሚተርክ በጥሩ የአይምሮ ጤና ላይ ካልሆኑ ይህን ገጽ ይለፉት።

# የልቤ ሰው

## Nikol Vibe (Starz)

አንተ/ እሱ

ብሩክን የማውቀው ከልጅነቴ ነው። እንደማንኛውም የገጠር ልጅ አፈር ፈጭተን ጭቃ አቡክተን፣ ወንዝ ወርደን ውሃ ተራጭተን፣ ዕቃቃ ተጫውተን አድገናል። ከዚያም አለፍ ስንል ቤተሰቦቻችን ከዕድሜ እኩዮቻችን ጋር ትምህርት ቤት ሲልኩን በአንድ ክፍልና በአንድ ወንበር አብርን የፊደል ገበታን ተቋድሰናል።

በሰፈር ውስጥም ሆነ በትምህርት ቤት ሌሎች ብዙ ጓደኞች ቢኖሩንም የኛ ቅርበት ግን የተለየ ነበር። በመሃላችን የነበረው ፍቅር ከጓደኛነት አልፎ የአንድ እናት ልጆች ነበር የምንመስለው። ቤተሰቦቻችን ለማያውቁ ሰዎች መንታ እስክንመስል ድረስ ሚያስቀና የጓደኝነት ቅርበት ነበረን። በመሃላቸን የኔ የኔ የሚባል ምንም ነገር ኖሮን አያውቅም። የኔ የሆነ ነገር ሁሉ የሱ ነው። የሱም እንደዛው።

አብሮ በማደግ የመጣ ጓደኝነት እድሜ ሲጨምር፣ አዲስ ሰው ሲለመድ ሲቀዘቅዝ አይተናል። የእኛ ግን ቅርበታችንም ሆነ በማሃላች ያለው ፍቅር ከእለት እለት እየጋለ ነበር የሚሄደው። ሚስጥር የሚባል ነገር በመሃላችን የለም። አንደባበቅም አንወሻሽም። የልጅነት ፍቅር ሲይዘው፣ ሲከፋው፣ ምክር ሲፈልግ፣ ሲደብረው ...... እኔ ጋር ነው የሚመጣው። እኔም ከሱ ውጪ መሄጃ አልነበረኝም። አንዳችን የአንዳችን የሚስጥር ጎተራ፣ ሸክም ማቅለያ ስልቻ ነበርን።

እኔ ለተመሳሳይ ፆታ ተስህቦ እንዳለኝ የተረዳሁት ዘግየት ብዬ ነበር። አሁን ላይ ምክንያቱ ብዬ የማስበው ዘመናዊ ሰው አለመሆኔ ወይም የገጠር ልጅ መሆኔ ነው። ገጠር ለራስ ስሜት ግዜ ሰጥቶ ከመረዳት ይልቅ፤ ማህበረሰቡ ባበጀው ባይ መፍሰስ ይቀላል። ከፍ እያልኩ ሰመጣ ስያሜ ልሰጠው ያልቻልኩት ስሜት ይሰማኝ ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜ

ስለተመሳሳይ ፆታ ግንኙነት የሰማሁት በቤተክርስቲያን ነበር። ስብከቱ የነበረው ስለ ሁለት ሰዎች ፍቅር ሳይሆን ሰይጣናዊ ስለሆነ ወሲባዊ ግንኙነት እና ምን ያህል እጅግ ቆሻሻና አፀያፊ ተግባር እንደሆነ ነበር። በለጋ አይምሮዬ ድረጊቱን መልሼ መላልሼ ስለዋለሁ። “ወንድ እና ወንድ እንዴት ነው ሚያደርጉት? እንዴትስ ነው ሚረኩት”? በኢየሰስ ስም እላለሁ። ሰባኪዎቹ ስለወሲባዊ ግንኙነቱ እስነዋሪነት ያወራሉ እንጂ ሙሉ መረጃ ስለማይሰጡ አይምሮዬ እረፍት አጣ። በግዜው ግን በዚህ ጉዳይ ምንም አይነት የጠለቀ እውቀት አልነበረኝም። መረጃ ማገኛበት አጋጣሚም አልነበረም።

እድሜዬ ከፍ ሲል፣ በትምህርትም ትንሽ ከዘለኩ በኋላ ነበር እንደማንኛውም ሰው ዘመናዊ ስልክ የኖረኝ። ከብሩክ እና ከሌሎች ጓደኞቼ ጋር ተሰብሰበን የወሲብ ፊልሞችን ማየት ጀመርን። የምናያቸው የወሲብ ፊልሞች የተቃራኒ ፆታ ቢሆንም እኔ ግን ትኩረቴ ሁሉ ወንድዬው ላይ ብቻ ነው። እነሱ ስለ ሴቷ ተክለሰውነት እና ቁመና ሲያወሩና ሲያደንቁ በኔ አይምሮ ውስጥ ሚመላለሰው ወንድዬው ነው። በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ ለወንድ ልጅ ያለኝ ስሜት ምን እንደሆነ ግልፅ አልሆነልኝም ነበር።

ከጊዜያት በኃላ በአጋጣሚ ዌብሳይቶችን ሳገላብጥ ነበር ለመጀመሪያ ግዜ የተመሳሳይ ፆታ ወሲብ ቪዲዮ የተመለከትኩት። በግዜው የተሰማኝን ስሜት በቅጡ ባላስታውስም የማወቀው የተቃራኒ ፆታ የወሲብ ፊልም ከማይባቸው ጊዜያት በተለየ ደስተኛ መሆኔን ነው። ደግሜ ደጋግሜ ተመለከትኩት ወደድኩት። ግን ለምን በዚህ ልክ ደስተኛ እንደነበርኩ በጊዜው አልገባኝም ነበር። እውነቱን ለመናገር በጊዜው ከነበረው የቤተሰብ ሆኔታ፣ ካደግኩበት አስተዳደጌ፣ በክርስቲያናዊ ትምህርቱም አንፃር ይህንን ነገር እብዝቼ እጠየፈው ነበር። ነገር ግን ሳላሰበው ወድጄውና ሱሰኛ ሆኜ አረፍኩት። ይባስ ብሎ በቪዲዮ የማያቸውን ነገሮች ከወንድ ጓደኞቼ ጋር ማድረግ እያማረኝ መጣ። ሌሎች ጓደኞቼ ስለሴቶች ቁንጅና ሲያወሩልኝ ምንም መስሎ አይታየኝም። ስለወንድ ውበት ግን እጨነቅም ነበር። ሌሎች የእድሜ እኩዮቼ የሴት ፍቅረኛ ሲኖራቸው እኔ ነጠላ ነበርኩ።

እንደዛ እጠላውና እፈራው በነበረ የተመሳሳይ ፆታ ተማርኮ ውስጥ ራሴን አገኘሁት። ይህንን ነገር ማወቄን፣ ከልጅነቴ ጀምሮ ይሰሙኝ ለነበሩ ስሜቶች መልስ ስሰጥ እና ምን እንደሆንኩ እርግጠኛ ስሆን እንደራሴ ለማየው የልቤ ሰው ብዬ ለማምነው ለብሩክ ልነግረው ወሰንኩ።

አሁን ሳስበው ለሰው ለመናገር ትንሽ የቸኮልኩ ይመስለኛል። ችግሩ የነበረው ራሴን መቀበሌ ሳይሆን ይህ ነገር በሰዎች ዘንድ ምን አይነት ቦታ እንዳለው አለማወቄ ነበር። ብሩክ ይህንን ነገር እንደሚጠላው ባውቅም በጊዜው ካለን ቀረቤታ አንፃር ብዙ ተቃውሞ ይገጥመኛል ብዬ አላሰብኩም። ያኔ መዘዙ ምንም መስሎ አልታየኝም ነበር። ይልቅ የኔ ለምለው ሰው ተናግሬ እንዲቀለኝ ነበር የፈለኩት።

ስነግረው በመጀመሪያ እየቀለድኩ መስሎት ነበር ነገር ግን ደጋግሜ ስምልለትና በሃይማኖት ጉዳይ የማልደራደር መሆኔን ስለሚያውቅ የምሬን መሆኑ ገባው። ፊቱ በአንድ ጊዜ ሲቀያየርብኝ ትዝ ይለኛል። ድንጋጤው ዛሬም ድረስ ፊቴ ድቅን ይልብኛል። እኔም ሁሉንም ነገሬን አንድ በአንድ ዘረገፍኩ። እሱም አልፎ አልፎ በድርጊቶቼ ይጠራጠረኝ እንደነበር ነገረኝ።

ለብሩክ ሚስጥር ያልመሰለኝ ሚስጥሬን በማጫወቴ ምንም ቅር አላለኝም። ለተወሰኑ ቀናቶች ከብሩክም ጋር ብንጠፋፋም ለሶስተኛ ሰው አሳልፎ ይሰጠኛል ብዬ ለአፍታ እንኳን አስቤ አላውቅም። ብሩኬ እኮ ውዱ ጓደኛዬ ነው። እንዴት ጠረጥረዋለሁ?

ከዚያን ቀን በኋላ በመሃላችን የነበረው የጓደኝነት መንፈስ እየተቀየረ መጣ። ብሩክ በፍፁም የማላውቀው እንግዳ ሰው እስኪመስለኝ ድረስ እኔን አብዝቶ ጠላኝ። ለብዙ ዓመታት የተገነባው የጓደኝነት ካብ እንደዋዛ ተናደ። አዲስ ሰው፣ አዲስ ማንነን፣ አዲስ ባህሪ አሳየኝ። የማላውቀው ሰው እንኪመስለኝ ተለየብኝ። በስልክም በአካልም ስናወራ እንደተጠየፈኝ ያሳብቅበታል። ከመናገሬ በፊት ነገሮች እንዲህ በፍጥነት ይቀያየራሉ ብዬ አላሰብኩም። የምወደው የልጅነት ጓደኛዬ ብሩክ እንዲህ ጀርባውን ይሰጠኛል ብዬ አልጠረጠርኩም።

ግን ከእለት ወደእለት ጥላቻው በርትቶ ሊያየኝም ሆነ ሊያወራኝ እንደማይፈልግ ነገረኝ። እኔ ግን ከእውቀት ማነስ ይሁን ለነገሩ ክብደት ካለመስጠት በመሃላችን የተፈጠረውን ክፍተት እንደ ተራ የጓደኝነት ግጭት አድርጌ ቆጠርኩት። ከጥቂት ቀናት በኃላ ግን የቅርቤ ሰው ብዬ ሚስጥሬን ያወራሁት ጓደኛዬ ለሰዎች አሳልፎ ሰጠኝ። ሚስጥሬ ሌሎች ጓደኞቼ ጋር ደርሶ ያገሉኝና ያርቁኝ፣ ያወሩና ያስወሩብኝ ጀመር።

በሳምንቱ እሁድ እንደሁልጊዜው ቤተክርስቲያን ለመሄድ መንገድ ላይ ሳለሁ እሱና ሌሎች ጓደኞቼ ከሩቅ አይተውኝ ሁሉም ሳቁ፣ እኔም እንደወትሮው ስንገናኝ ምንገለፍጠው መስሎኝ እነሱ ወዳሉበት አቅጣጫ አመራሁ። እነሱ ግን እንኳን ሰላም ሊሉኝ ተጠይፈውኝ ወደሌላው አቅጣጫ መንገድ ጀመሩ። ልቤ ምቱን ማቆም እስኪሳነው ሰውነቴ ተልፈሰፈሰ። ድንጋጤው አተነፋፈሴን እስኪያዛባው ትንፋሼ ተቆራረጠ። ብርክ ሲይዘኝ ወደ ቤተክርስቲያን መሄዴን ትቼ ወደ ቤት ተመልሼ በመኝታ ክፍሌ በሬን ዘግቼ ለረጅም ሰዓታት አለቀስኩ።

ያ ቀን ለኔ የአመት ያህል ረዝሞ አይነጋ የለም ነጋ። በጠዋቱ ልቤ እየተረበሸም ቢሆን ወደ ትምህርት ቤት ሄድኩ። ስሄድም ሁሉ ነገሬ ልክ አልነበረም። ልክ ክፍል ገብቼ ወንበሬ ላይ እንደጠቀመጥኩ ወንበሩ ሁሉ ሚውጠኝ መሰለኝ። ግድግዳዎችም አፋቸውን አውጥተው “ጌይ” “ግብረሰዶማዊ”[2]...... የሚሉኝ እየመሰለ ጭንቀት ተቆጣጠረኝ። ከመች መች መጥተው ጎትተው ያወጡኝ ይሆን? የሚል ፍርሃት አደረብኝ። ሁላቸውም ስሜን ሲጠሩኝ ያንን ነገር የሚናገሩኝ መሰለኝ። ግን የዛን እለት ምንም የተለየ ነገር ሳይፈጠር እራሴን በማስጨነቅ ብቻ ዋልኩ። በነጋታው ግን ክፍል ውስጥ ሁሉም ስምቶት ጠበቀኝ፣ ለወትሮ ከበውኝ የሚቀመጡ ልጆች ብቻዬን በአንድ ወንበር እንድቀመጥ ፈረዱብኝ። ይህን ግዜ አልቻልኩም ክፍሉን ትቼ ወጣሁ።

ትምህርቴን አቋርጬ ቤት የዋልኩለት ወሬ በሬን አንኳኩቶ ደጄ መጣ። ለብሩክ ብቻ የነገርኩት ሚስጥር በዝቶና ተባዝቶ ከትምህርት ቤት አልፎ ሰፈሬ ገብቶ ቤተሰቦቼ ሰሙ። ከቤተሰቤ በመጀመሪያ ወሬው ታናሽ ወንድሜ ከሰፈር ጓደኞቹ ጋር ኳስ በሚጫወትበት ቦታ “የጌይ ወንድም” ብለው ከቡድናቸው አገለሉት፣ እያለቀሰ ቤት መጥቶ የሆነው ሁሉ ለእናቴ ነገራት። እናቴም ሆነች ወንድሜ ቃሉም ነገሩም አዲስ ስለሆነባቸው እና ወንድሜም ወደ ክለቡ መመለስ ስለነበረበት ለአባቴ ልጆቹ ጋር ሄዶ እንዲጠይቅ ሆነ። ሰምቶም ከመጣ በኋላ ደጋግሞ “ምናለ አምላኬ ይህህንን አይነት ጉድ ከምሰማ ብትደፋኝ! እኔው ባደባባይ ማወግዘው እና ምገሰፀው ሴጣን ሰተት ብሎ ቤቴ መጣ!? ምናለ ይህንን ልጅ ብለህ ከምትሰጠኝ ብትከለክለኝ!” እያለ በጩኸት እኔ ጋር ደረሰ፣ እጄን በእጆቹ ጨፍድዶ ይዞኝ ቁጭ ካልኩበት ወደ ቤታችን ሳሎን ወሰደኝ። ልጅነቴን እስከመካድ ድረሰ አፈረብኝ። ስሜታዊነቱ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ የሚባል አይነት ነበር።በግዜው ከነበረብኝ ጭንቀት ምን እንዳለኝ ዛሬ ላይ አላስታውስም። ቤተሰቦቼ

[2] ግብረሰዶማዊ፥ ከመጽሃፍ ቅዱስ ተጠቅሶ ወንድ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎችን ለመኮነን የሚዉል ቃል

እጅግ ሲበዛ ሃይማኖተኛ ስለሆኑ ከቤተክርስቲያን ሰዎችን አስመጥተው አስፀለዩልኝ። በእጄ መፅሐፍ ቅዱስ አስይዘው አስምለው ጠየቁኝ እኔም እጄን ጭኜ "ግብረ-ሰዶማዊ" አይደለሁም ብዬ ማልኩ።

ከዚህ ሁሉ በኃላ ግን አልቻልኩም የሰዎችን የበዛ ጥላቻ፣ ቤተሰቦቼ በኔ ምክንያት ያልተገባ ስም ማግኘታቸው፣ የልቤ ሰው ባልኩት ጓደኛዬ መከዳቴ ራሴን እንዳጠፋ ገፋፋኝ። በጊዜው ራሴን በጣም አምርሬ ጠላሁት። በየሄድኩበት ሁሉ "ግብረሰዶማዊ!" "ጌይ" "ቡሽቲ" እያሉ በተለያዩ ስድባዊ ተቀጥላ ስሞች ሲጠሩኝ ልቤ ወረደ። በተፈጥሮዬና በማንነቴ አፈርኩ። ተሸማቀኩ። ራሴን ማጥፋት እንደ ብቸኛ ምርጫ ወስጄው የተለያዩ ሙከራዎችን አደረግኩ። በመጀመሪያም ቤት ውስጥ የነበሩትን ግዜያቸው ያለፈባቸውን መድሃኒቶች ሰብስቤ ቅሜ ስንፈራገጥ ድንገት ታላቅ እህቴ ወደ ሐኪም ቤት ወስዳኝ ህይወቴን አዳነችልኝ። በሌላም ግዜ ሌሎች ሙከራዎችን አድርጌ ግን ቀኔ አልደረሰምና አልሞትኩም።

ከዚህ በኋላ ቤተሰቦቼ አመኑኝ ከውጪ የሚመጣውን ወሬ ልጃችን እንደሱ አይደለም ብለው ጥብቅና ቆሙልኝ። ከጥቂት እረፍት በኋላ ትምህርቴን መቀጠል እንዳለብኝ ተነግሮኝ ለመቀጠል ወሰንኩ። እኔ ግን የወሬውን ዳግም ግርሻት ሽሽት ትምህርት ቤት ነኝ በሚል ሰበብ ሌላ ቦታ ውዬ በመውጫው ሰዓት እመጣ ነበር። ቤተሰቦቼ ስራ ስለሚበዛባቸው የኔን የቀን ተቀን ውሎ ሆን ብለው አይከታተሉም ነበር።

በዚህ መሃል ቤተሰቦቼን ባተሌ ስለሆናችሁ ስራ ላግዛችሁ በሚል ምክንያት ለረጅም ጊዜ ትምህርት አቋርጬ ከጓደኞቼ ዓይን ተሸሸኩ።

ይህ ሁሉ ነገር ሲሆን ገና የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ነበርኩ። ነገሮች ከአፌ ከመውጣታቸው በፊት ያሰብኩትና ብሩክ ጋር ከደረሱ በኋላ የነበረው ምላሽ የሰማይና የምድር ነበር። በዛ የልጅነት እድሜዬ ያን ጥላቻ መቋቋም የሚያስችል አቅም አልነበረኝም። የጓደኞቼን ስድብና ዓይን ሽሽት ያቋረጥኩትና የቀረኋቸው የትምህርት ጊዜያቶች ከድብርትና ከፍላጎት ማጣት ጋር ተደማምረው የስምንተኛ ክፍል ሚኒስትሪን ሁለት ግዜ ደገምኩ። ያ ወቅት ለኔ እጅጉን በጣም ከባድ ነበር። እያንዳንዱ ነገር እረፍት ይነሳኛል። ቀስ በቀስ ራሴን መንከባከብና ማረጋጋት ጀመርኩ። ራሴን ከማንም በላይ እንደምወደው ለራሴ እነግረው ነበር። በተለይም እኔን ራሴን እንድቀበልና በሁኔታዎች ፀንቼ እንድቆም ያደረገኝ ክርስቲያን መሆኔ ነበር። ህይወት የእግዚአብሔር ናትና ካጠፋኋት እጠየቃለው

ብዬ ማሰቤ ጠቅሞኛል። ራሴን ባጠፋ የምጎዳው እኔ እንደሆንኩ ገባኝ። ስለዚህም ለራሴ መኖር እንዳለብኝና ህልምና ተስፋ እንዳለኝ አምኜ በፅናት መኖር እንዳለብኝ ራሴን አሳምኜ መኖርን ካለመኖር መርጬ ህይወትን ቀጠልኩ።

አሁን በህይወቴ ደስተኛ ነኝ። ዛሬን ስላየሁ ደስተኛ ነኝ። ራሴን አግኝቼዋለሁ። ራሴን ተቀብዬዋለሁ። አንድ ቀን ደግሞ ህልሜ ጋር ደርሼ ከዚህ በበለጠ ደስተኛ እሆናለሁ። ራሴን በትክክል እንዳገኝና ጥንቁቅ እንድሆን ደግሞም ህይወትን በሌላ አቅጣጫ እንድመለከት ያደረገኝን ጓደኛዬን አመሰግናለሁ።

አንድ ቀን….. መቼ እንደሆነች ማላውቃት አንድ ቀን ትመጣ ይሆናል። አንድ ቀን ለቤተሰቦቼ ራሴን ገልጬ እውነተኛ ማንነቴን በመረጃና በማስረጃ የምገልጥበት ቀን ትመጣ ይሆናል።

በዚህ ውብ ውስጥ ከብሮ ስላደረው መንፈስ ቅዱስ እምላኬን አመሰግነዋለሁ።

ሞቴን እየጠበቀ እያለ በህይወት እኖራለው።

ማንነት የአምላክ ስጦታ እንጂ ምርጫ አይደለም!

# ድግስ

**ፍጹም**

እንተ/እሱ

ዓለማችን በየዕለቱ በለውጥ ሂደት ላይ ነች። በተለያዩ የአለማችን ክፍሎች ህጎች እየተሻሻሉ ለተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪዎች ምቹ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ እንሰማለን። በዛው ልክ እኛ የምንኖርባት አፍሪካ ነገሮችን ከቀን ወደ ቀን እያጠበበችብንና ለመኖር አስቸጋሪ እየሆነች ትገኛለች። ለዚህ ቀላሉ ማሳያ በኡጋንዳና በኬንያ እየተደረጉ ያሉ የህግ ማሻሻያዎች ናቸው።

በሌላው ዓለም ያለው ተቀባይነት እየበዛ ሲመጣ በዛው ልክ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪዎች ለራሳቸው በራሳቸው የሚፈጥሩት ምቹ ቦታዎች እየተበራከቱ መጥተዋል። እነዚህ የጎዳናላይ እና በቤት ውስጥ የሚደረጉ ድግሶች ህይወትን ከማክበርም በላይ በመላው ዓለም ተጨቁነው ለሚገኙ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪዎች ድምፅ ማስሚያ መድረኮችም ናቸው።

በሃገራችን እንደዚህ አይነት ዝግጅቶችን አይደለም ማዘጋጀት ማሰብ በራሱ እራስ ላይ ካራ ከመምዘዝ የማይተናነስ ሞት ናፋቂነት ነው። ይህን አስፈሪ የሞት ጥሪ ተቋቁመው underground ፓርቲዎችን የሚያዘጋጁ በጣት የሚቆጠሩ ልበ ብርቱ ወጣቶች በተለያዩ ግዜያት ከተማችን አይታለች።

እኛም በዚህ እትም እንደዚህ አይነት ፓርቲዎችን ከሚያዘጋጀው ፍፁም ጋር አጠር ያለ ቆይታ አድርገን ሞላሹን እንደወረደ ለናንተ አምጥተናል። በዚህ ቃለ መጠይቅ ፍፁም ስለ ደስታው ፍርሃቱ እና በተለይ ይህን አይነት ድግስ ለመደገስ ምን እንዳነሳሳው ይነግረናል።

አብራችሁን ቆዩ።

ጥያቄ: ሰላም.. እንዴት ነህ?

መልስ: አለሁልህ ሁሉ ሰላም።

ጥያቄ: እስኪ ራስህን አስተዋውቀን?

መልስ: ፍፁም እባላለሁ። የአዲስ አበባ ነዋሪ ነኝ። በትርፍ ጊዜዬ ( ከዋናው ስራዬ በተጨማሪ) የተለያዩ ፓርቲዎችን አዘጋጃለሁ።

ጥያቄ: በቃ.... (ሳቅ)

መልስ: አይበቃም........( ፈገግታ)

ጥያቄ: እሺ.......የዜጋ ፓርቲዎችን ለማዘጋጀት ምን አነሳሳህ? በምን ያህል ግዜ ልዩነት ታዘጋጃለህ?

መልስ: እኔ ማዘጋጀው ፓርቲ በየወሩ ወይም በሁለት ወር አንዴ ነው ማዘጋጀው። እንደ የአየሩ ፀባይ ታይቶ እስከ ሶስት ወርም ሊቆይ ይችላል። ይህን ፕሮግራም ለማዘጋጀት ያነሳሳኝ በኛ ህይወት ላሉ ሰዎች ነፃ ግዜን ለመስጠት ነው። በነፃነት ራሳቸውን የሚሆኑበን ቦታ መፍጠር፣ በነፃነት የሚዝናኑበት ከሚመስላቸው ጋር ጥሩ ግዜ የሚያሳልፉበት መድረክ መፍጥር ነው። እንዲሁም የትም ቦታ ሰው አየኝ አላየኝ ብለው የሚያደርጉትን ነገር ወይም ሃሳብ ፕሮግራሙ ላይ እንዲያንጸባርቁ በማሰብ ነው የማዘጋጀው። እንዲሁም ለኔ ተጨማሪ የገቢ ምንጬ ነው።

ጥያቄ: የመጀመሪያው ሰው ወደ ግቢ ከመግባቱ በፊት ምንድነው ምትሰራው?

መልስ: ሰው ከመግባቱ በፊት ቤት ይፀዳል፣ አጠቃላይ ቤት የማስዋብ ስራ እንሰራለን። መጠጥ እናዘጋጃለን። የሚያስተናግዱ ሰዎችን አሬንጅ የማድረግ ስራ እንሰራለን። ቀኑን ሙሉ ዋና ዋና ነገሮችን ስንሰራ ስለምንውል መጨረሻ ላይ የምናደርገው ነገር ትንንሽ ነገሮችን ማስተካከል ነወ።

ጥያቄ: ሰው መምጣት ሲጀምር ምን ይሰማሃል?

መልስ: ብዙ ግዜ ፓርቲ የሚጀመረው ማታ አራት ሰዓት ላይ ነው። ልክ ፕሮግራሙ እንደተጀመረ ወይም ከመጀመሩ በፊት ወይም በየመሃሉ ትንሽ ነገር ኮሽ ሲል ክፉ ሃሳብ ነው ወደ አይምሮዬ የሚመጣው። ፕሮግራሙ በሰላም ይጠናቀቅ ይሆን? እረብሻ ይኖር ይሆን? ድብድብ ተነስቶ ፖሊስ ይመጣ ይሆን? የሚል ሃሳብ ውስጤን ያስጨንቀዋል። ሰው መምጣት ሲጀምር የሚሰማኝ ስሜት ሁሌም በስጋት የታጀበ ነው። በአንድ ጎን ብዙ ሰው ሲመጣ ደስ ይለኛል.. ሰዎች እንደፈለጉ ለብሰው እንደፈለጉ ተቀባብተው.. ራሳቸውን ሆነው ሳይ ደስ ይለኛል። በሌላ ጎኑ

ደሞ የሆነ ፀብ ቢነሳ አለመግባባት ቢፈጠር የሚያመጣው ጣጣ ትንሽ ሙዴን ይረብሸዋል። ፓርቲው ተጀምሮ እስኪያልቅ ድብልቅልቅ ያለ ስሜት ነው ሚሰማኝ።

ጥያቄ: የመጨረሻው ሰው ከፓርቲህ ሲወጣ ምንድነው ሚሰማህ? ሰው ከወጣ በኋላ ምንድነው ምትሰራው?

መልስ: ፕሮግራሙ ተጠናቆ የመጨረሻው ሰው ሲወጣ እፎይታ ይሰማኛል። ኡፍፍፍፍ..... ተመስገን ፈጣሪ እላለሁ። ደስ ይለኛል። ብዙ ግዜ የመጨረሻውን ሰው መሸኘት የፓርቲው አካል ነው። ምክንያቱም አንዳንዶች ከመጠን በላይ ጠጥተው ራሳቸውን ይስታሉ እነሱን ማደሪያ መፈለግ የኛ ስራ ነው የሚሆነው። አንዳንዱ በደስታ ውስጥ ሆነው ቆይተው ግን ማደሪያ የሌላቸው አሉ እነሱንም ማደሪያ እንፈልግላቸዋለን። የምንከራየው ቤት ትላልቅ ስለሆነ ማደሪያ አይቸግርም ሚለበስ ነው ችግሩ። ብቻ ሰው ከወጣ በኋላ ብዙ ሚሰሩ ነገሮች አሉ ጠርሙስ እንሰበስባለን፣ ቤት እናፀዳለን። የቻልነውን ሰርተን የቀረውን ለነገ አሳድረን...ስለ ነበረው ነገር... ስለ ፕሮግራሙ እያወራን፣ እየሳቅነነ በቀጣይ መሻሻል ስላለበት ነገር እየተመካከርን ራት በልተን እንተኛለን።

ጥያቄ: ፓርቲ ላይ ምን ተፈጥሮ ያውቃል? ለምሳሌ ፀብ ምናምን.. ?

መልስ: ይህን ፕሮግራም ሳዘጋጅ ያን ያህል ባይባልም ፀብ አጋጥሞኛል። ቤቱ ትንሽ ስለሚጨናነቅ ገፋኸኝ በሚል ሰበብ ፀብ ተነስቶ የተጎዳ ሰው አጋጥሞኛል።

ጥያቄ: ፓርቲ ላይ ያጋጠመህ አሳዛኝ ወይም አስቂኝ ገጠመኝ

መልስ: አሳዛኝ ገጠመኝ የምለው ሰው ተጣልቶብኝ የተጎዳ ሰው ነበር እና ልጁ በጣም ተጎድቶ ለረጅም ግዜ ታሞ ነበር። አስቂኝ የምለው የማዘጋጅ ፓርቲ ላይ እንደ ሴት አክት የሚያደርጉ ልጆች ናቸው። ወሬያቸው ለየት ያለና የሚያስቅ ነው።

ጥያቄ: ምን አይነት ሰዎች ናቸው አንተ ፓርቲ ላይ አዘውትረው የሚመጡት… ድባቡስ ምን ይመስላል?

መልስ: ፕሮግራሙ ላይ በብዛት አዘውትረው የሚመጡት ወጣት ወንዶች ከአስራ ስምንት እስከ ሰላሳዎቹ ውስጥ ያሉ ሰዎች ሲሆኑ አልፎ አልፎ ትልልቅ ሰዎችም ይመጣሉ። በብዛት ባይሆንም ሴቶችም ይመጣሉ።

ወጣቶቹ አለባበሳቸው የሚገርም ነው። ዘመኑን የተከተለ ነገር ግን ወደ ሴቶች ዲዛይን የሚያደላ ልብስ ነው ሚለብሱት። ጌጣጌጥ በጣም ያዘወትራሉ። አልፎ አልፎ በራሳቸው ሳይዝ ሆኖ የሴቶች ልብስ ለብሰው የሚመጡም አሉ። ሜካፕ ይጠቀማሉ። ሁኔታቸው በተለምዶ “ወንድ ልጅ” ከሚያዘወትረው አለባበስ እና ስታይል ወጣ ያለ ነው። በብዛት በተለይ “Bottom” ብለው እራሳቸውን የለዩት ማለቴ ነው። አወራራቸው እንደ ሴት ነው። ሲጠራሩ አንቺ አንቺ እየተባባሉ ነው። ንግግራቸው ላይ ማርዬ፣ ፍቅር፣ እናቱ ስሚ የሚሉ ቃላትን ይጠቀማሉ። አካሄዳቸው የሴት አክት አለው ፋጤ ብለን የምንጠራው ማለቴ ነው።

ስራቸው በብዛት ሼፍ፣ ፀጉር ቤት፣ ቡቲክ፣ መስተንግዶ ከአረብ ሃገራት እንደ ሽቶ፣ አልባሳት፣ ኤሌክትሮኒክስ ነገሮችን አምጥተው መሸጥ ነው። ከባድና የሚያስጨንቅ ወይም የጉልበት ስራ አይወዱም። ሁሌ ፅድት ብለው መታየት ይወዳሉ። ባላቸው ነገር ደስተኛ መሆን ይፈልጋሉ። ክፋት የላቸውም። እጃቸው ላይ ብር ካለ መጋበዝ ይወዳሉ። መዝናናት ያስደስታቸዋል። የዛኑ ያህል ደሞ በትንሹ ይከፋሉ፣ ይጨናነቃሉ። ስሜታቸው ወዲያው ይጎዳል። በብዛት ያለቅሳሉ። ስሜታቸውን ከልብ የሚረዳቸው ይፈልጋሉ።

ሌላው በዚህ ላይፍ ረጅም ዓመት የኖሩ ሰዎችም አሉ። አንዳንዶቹ መልካሞች ናቸው። በብዛት ግን ፀብ ይወዳሉ። አምባገነን መሆን ይፈልጋሉ፣ ይደባደባሉ እና ከባድ ባህሪ አላቸው።

ጥያቄ: ምን አይነት ሙዚቃ ነው ምታጫውተው? የሚመጣው ሰው ምን አይነት ሙዚቃ ነው ሚፈልገው ? ብዙ ግዜ ይደገም ሚባለው ሙዚቃ

መልስ: የምናጫውተው ሙዚቃ ሁሉንም ያማከለ ነው። እንግሊዘኛ፣ አማርኛ፣ ትግርኛ በብዛት እና ኦሮምኛ ከዛ በተረፈ ደግሞ በነሱ ምርጫ እናጫውትላቸዋለን። በብዛት የሚፈልጉት ሙዚቃ የሚያስጨፍር ውስጣቸውን የሚያነብ ሙዚቃ ሲሆን ይደገም የሚሉበት ግዜ አለ።

ለምሳሌ የፍቅር ዘፈን፣ የይቅርታ ዘፈን፣ የመለያየት ዘፈንና የመሳሰሉት ውስጣቸው ያለውን ነገር ከገለፀላቸው ያስደግማሉ።

ጥያቄ: የሰዎች አኳኋን ምን ይመስላል? በግሩፕ የሚመጡት? ለብቻቸው መጥተው ኮርነር ላይ ሚሆኑት ሰዎችም አሉ ይባላል። እውነት ነው?

መልስ: ለብቻቸው መጥተው ጥግ ይዞ የሚቀመጥ ሰው አለ። በግሩፕ ሆነው የሚመጡም አሉ። ካፕል ሆነው ሁለት ሆነው የሚመጡም አሉ። እነሱ ሌላ ሶስተኛ ሰው አይፈልጉም። ምክንያቱም ከሌላ ሰው ጋር የፍቅር ግንኙነት እንዳይጀምሩ በማሰብና በመቅናት ይመስለኛል።

ጥያቄ: የእድሜ እና የፆታ ስብጥሩ ምን ይመስላል?

መልስ: የእድሜ ስብጥሩ ጥሩ ነው። በብዛት የሚመጡት ወጣቶች ናቸው። ጎልማሶችና ትልልቅ ሰዎችም ይመጣሉ። ፆታን በተመለከተ በብዛት ወንዶች ይበዛሉ። በፐርሰንት ለማስቀመጥ ብንሞክር ዘጠና አምስት ከመቶው ወንዶች ናቸው የሴቶቹ ኮታ ከ አምስት ከመቶ አይዘልም።

ጥያቄ: ሰዎች ሲያወሩ የሰማኸው አስቂኝ ንግግር?

መልስ: በጣም የገረመኝና ያሳቀኝ አንዴ የሰማሁት ነገር ነው። ልጁ ቀጭን ነው ብዙ ግዜ በግሩፕ ሆኖ ሴክስ ማድረግ ይወዳል። ሁልግዜ ልጁ ሲታይ ከወገቡ በላይ ቀጭን ይሆንና ቂጡ አከባቢ ወፈር ይላል። እና ሰው በጣም ይገረምበታል። ሰውነቱን ብዙ ሰው ይወደዋል። ታዲያ አንድ ቀን የግሩፕ ሴክስ ከተደረገ በኋላ ቀጭኑ ልጅና የአንደኛው ልጅ ሱሪ አጋጣሚ ይሆንና ተመሳሳይ ነበር። ያኛው ልጅ የሱ ሱሪ መስሎት የቀጭኑን ልጅ ሱሪ አንስቶ ሊለብስ ሲል ከኋላ በኩል ወፈር ይልበታል ምንድነው ብሎ በመገረም ገልብጦ ሲያየው አርቴፊሻል የእስፖንጅ ቂጥ አይቶ በጣም እንደጮኸና እዛ ላሉት እንዳሳያቸው ሰምቻለሁ። ይሄ ለኔ ያሳቀኝና ያዝናናኝ ታሪክ ነው።

ጥያቄ: ፍርሃትህ ምንድነው? ምንድነው ሚያስጋህ ?

መልስ: ብዙ ግዜ ይህን ፕሮግራም ሳዘጋጅ በጣም እፈራለሁ። ምክንያቱም በጣም ትልቅ ሃላፊነት ተቀብዬ ነው የምሰራው። ፓርቲ የማዘጋጅበት አከባቢ ያሉ ነዋሪዎች እኔ ጋር የሚመጡ ሰዎችን አዩብኝ

አላዩብኝ የሚል ፍርሃት በተለይ ወንዶች ብቻ መሆናቸው ሰዎች እንዲጠራጠሩ ያደርጋቸዋል ብዬ ስለማስብ፣ እክታቸው ያስፈራኛል፣ አለባበሳቸው፣ አወራራቸው፣ ዋነኛው የሚያሳስበኝ ነገር ደግሞ በዚህ ሁኔታ ላይ ሲደባደቡ በጣም እሳቀቃለሁ። ምክንያቱም በሚጣሉበት ግዜ ሰው ይሰበሰባል። ፖሊስ ይመጣል በዚህ መሃል ማነው ይህንን ፕሮግራም ያዘጋጀው የሚባል ነገር ይመጣል። እስከ መታሰር ደረጃ ሊያደርስ ስለሚችል በጣም እሰጋለሁ።

ጥያቄ: በመጨረሻ ማለት የምትፈልገው ነገር ካለ?

መልስ: ሁላችንም በዚህ ላይፍ ውስጥ ያለን ሰዎች የራሳችን አስተሳሰብ፣ ፍላጎት፣ ባህል፣ ቋንቋ ሊኖረን ይችላል። በላይፉ ግን አንድ ነን። ሁልግዜ እንደዚህ አይነት ፕሮግራም ሲዘጋጅ ወይም ለዚህ ላይፍ አመቺ የሆኑ ቦታዎች በሚፈጠሩበት ግዜ በጥንቃቄ ይሁን። ሁሌም ነፃ ሆነን የምንዝናናበት ቦታን እንደራሳችን እንጠብቅ። እዚህ ላይፍ ውስጥ ለሌሉ ሰዎች በር እንክፈትላቸው። የተለያዩ ሚድያዎች ላይ የምንለቃቸውና የምናስተላልፋቸውን መልዕክቶች ተጠንቅቀን ይሁን። ግዜው በቴክኖሎጂ የተከበበ ነው ባይ ነኝ።

ስለነበረን ቆይታ አመሰግናለሁ መልካም ግዜ።

# Examining the Anatomy of Change

**Balege Hayasi**

(She/her)

As I write this, folks in our community are being harassed, physically attacked, and forced out of their homes by self-crowned champions of Ethiopian values who are allegedly protecting their fellow citizens from the 'evil' and 'unnatural' influence of the queer community.

I am not surprised by their beliefs. After all, as an Ethiopian living in Ethiopia, I walk the thin tightrope of self-affirmation while holding space for a family and an immediate community whose structural integrity somehow hinges on my heterosexuality. But faced with the rhetoric of these violent vigilantes and its devastating implication, I can feel the reservoir of energy and compassion that powers this precarious existence running dry. How long can I coexist within a dominant ideology that believes that nebulous and dynamic concepts of tradition and cultural identity are worth the destruction of individual life? It feels as impossible as fully embodying my identity and politics in the here and now. As I grapple with this personal question, I have been wondering what the future holds for us as a community.

The sociopolitical climate of the past few years has been a nutritious medium for long-held sentiments to bloom into the violence that we are experiencing. Anti-queer rhetoric was already on the rise, exacerbated and magnified by fervent zealots platformed on social media and institutionally condoned movements like 'Zim

Anilim' and its offshoots. The campaigning strategies of these movements, which lobby the government to criminalize queer existence, have been strategically potent and devastatingly effective. They leveraged child sexual abuse, specifically the abuse of young boys, magnified during the COVID-19 pandemic, to legitimize anti-queer rhetoric (never mind the sexual abuse of girls, of course). Using issues of deep importance and urgency, they created false dichotomies and associations to sway an already prejudiced society – by being even slightly tolerant of queer identity, one is supposedly complicit in the sexual abuse of children. They build on a long and deeply embedded global history of scapegoating queer people to explain misfortune, plagues, and disasters, including the HIV/AIDS epidemic.

Of course, Ethiopia as a whole has never been accepting of queer identity. In 2007, 97% of Ethiopians believed "homosexuality is a way of life that society should not accept".[1] In fact, the rate of acceptance of queer identity has decreased significantly since 2000.[2] But the recent spike in actively homophobic attitudes and anti-queer rhetoric, though not surprising, is alarming in intensity and devastating in reach.

The evolution of the systemic erasure, othering, and dehumanization of queer Ethiopians into coordinated violence by the massest signals  the precariousness of the delicate balance through which coexistence has been possible. So far, queer life has existed as a shadow network superimposed on the predominantly religious and conservative society and many of us are used to leading double lives, navigating a passage between two realities. Some who slip in and out of the country temporarily suppress parts of their identity as necessary. Some with less chameleonic outer manifestations of

their sexuality develop other coping mechanisms and/or stick to safe spaces, constructing their lives around avoiding unsafe situations as much as possible. This dangerous dance has been effective, almost as if the queer community and the larger society had an implicit pact - if we are not seen, we are not harmed; those who cannot help but be visible must pay, but perhaps not with their lives.

A similarly alarming progression can be seen in the continent and globally, where we have been witnessing a roll back of the hard-won rights and acceptance of queer folks, often happening in concurrence with the rise of far-right extremist political ideology. In March 2023, Uganda's parliament proposed legislation with extreme penalties for same-sex relationships that criminalizes anyone identifying as LGBTQ.[3] It was passed a few weeks later. During that time, Ghana was looking to follow in its footsteps while some Kenyan politicians were hoping to pass a similar law of their own. These measures were accompanied by rhetoric conflating child sexual abuse with queer relationships between consenting adults as well as conspiracy theories accusing "shadowy international forces" of "promoting homosexuality" in Uganda - naming LGBT rights as "a second colonisation" designed to shrink Africa's population in Kenya, and as a sign of infiltration of foreign cultures in Ghana.[4] These framings work because they build on a kernel of truth – the continent's struggle with colonial legacy and the neocolonial forces at play in the current geopolitical landscape – to justify their stance.

The intersection of Ethiopian identity (as much as national belonging can be reduced to an identity) with the reality of queerness seems particularly and

painfully fraught with tension. A strong and deeply rooted connection to tradition and culture, high levels of religiosity, low levels of economic development, overarching adherence to traditional gender roles, and a culture of silence: not only are these markers often correlated with low levels of queer acceptance in a country,[5] they are also highly accurate descriptors of our current reality. Our relationship to tradition and culture, even though it has been going through its own long due process of fragmentation, seems particularly resistant to evolving in the direction of acceptance.

All this draws a disheartening picture but our lived reality is not just of oppression; it is also of resistance, hope, and life-sustaining alternative networks. Well-resourced queer folk, activist organizations and collectives, and allies are constantly performing healing magic behind the scenes, showing up in beautiful solidarity to resource, house, and feed those who have been targeted by anti-queer violence. It is humbling, reinvigorating, and fortifying to see these mycelium-like networks of support – operating underground and full of such vitality – that have managed to thrive despite all odds.

And yet, the delicate pact that has allowed the existence of these networks, though nowhere good enough, now feels broken. I worry for our collective future and wonder if or when the reality of oppression will change. Will queer folks ever be valid in the Ethiopia we know and live in? Or does a different Ethiopia have to come into being for that to ever happen? (The author is in no way suggesting we burn shit down :)) Are we, as a collective, subject to the whims of history, fated to wait for seismic shifts in the sociopolitical fabric that create cracks within which we emerge, finally, as

valid humans? Are we going to keep being pawns in a larger political agenda, with our identity either seen as an invention of the West, or used in ‘well-intentioned’ global sanctions by the very same West, or latched onto by governments for whom we are ‘low-priority’ unless feeding the fire of existing prejudice is beneficial for their political standing?

And what can we hold on to when damaging light shines on our covert networks of resistance? What do we do when those who carry on when those doing the necessary work of care, support, and education get burnt out or chased out, as often happens?

The rules governing coexistence have once again changed and our systems need to adapt to a different reality - a daunting task which requires collective reckoning. In the meantime, I hope we can keep supporting each other in the shadows, learning new ways to connect, to be safe, and to keep our private sorrows from isolating and overwhelming us.

Thanks for reading. If you want to share your thoughts or you have any questions or comments, email **balegehayasi@protonmail.com**

---

[1] https://williamsinstitute.law.ucla.edu/wp-content/uploads/Global-Acceptance-Index-LGBT-Oct-2019.pdf

[2] https://www.aljazeera.com/news/2023/3/22/uganda-passes-tough-antigay-law-bans-identification-as-lgbtq

[3] https://www.economist.com/middle-east-and-africa/2023/06/01/ugandas-harsh-anti-gay-bill-is-now-law

[4] https://williamsinstitute.law.ucla.edu/wp-content/uploads/Global-Acceptance-Index-LGBT-Oct-2019.pdf

# Dhiiraa fi Dhiira

**Urjii Borii**
(Isa/Inni)

Jiituu onnee marga Birraa
Qabeenya ofii kenna uumaa
Gaaffii onnee situ  fura
Si'i hundeen situ bu'uura
Fedhiin Addaam Hewaan Caalee
Malkaan onnee Addaam waamee
Qe'ee Onnee  boojuu hundaa
Jilbeenfataa walfakkaataa
Hadheeffataa saala faallaa
Onneen zeegaa fedhii dhugaa
Kennaa Rabbii jiruu mishaa
Sirraa kaanee sirra facaane
Lammii taaneetu jiraanne
Qormaatilee buunee baanee
Ni mul'anne tulluu  taane
Ifnee jirra akka urjii
Qaanessinee amajaajii
Waankee martuu hawwisiisaa
Yaa jaalalaa dhiiraaf dhiiraa
Maal kee faarseen maal kee dhiisa?

# ፋጤ Who?

## ቪክቶር ጌታ

(አንተ/አንቺ)

“ሴቱ ሴቱ ሴቱ”....ከስሜ በኋላ የተሰጠኝ ቅፅላ ማዕረግ ነበር። ብዙ ጊዜ እኩዮቼ ወይም ትምህርት ቤት የሚሉኝ ነበር። ስድብ መሆኑ ነው። “ ሴታ ሴት” ደግሞ ትላልቅ ሰዎች ወይ ታላላቆቼ የሚሰድቡኝ ነበር... አባቴን ጨምሮ። “ምን እዚህ እንዲህ እንደሴት....” ብሎ ይጀምርና የሚለውን ይላል። በልጅነት እድሜዬ ምንም አይመስለኝ ነበር። አይሞቀኝ አይበርደኝ። እያደኩ ስሄድ ግን ሽምቅቅ እፍር እል ጀመር። ስድብ መሆኑ ተሰማኝ። ባዝንም ቢከፋኝም ለመቀየር ግን ብዙም አልጣርኩም። እራሴን ጠልቼ ወንድ ለመባል ወይ ለመመሰል ብዙም አልተጋጋጥኩም። ተቀብዬው የማንነቴ አካል ሆነ። በሌለሁበት ስሜ ሲነሳ “ያ ሴታ ሴቱ” እንደምባል አውቀዋለሁ። ነኝ! እና ምን ይጠበስ? ....ምንም!

አደግ ብዬ እድሜዬ ለአቅመ አዳም ደርሶ ዜጎች ስተዋወቅ ሴቱ ምናምን የሚባለው በዛኛው አለም እዚህ ተቆላምጣ ስሟ “ፋጤ” ሆኖ አገኘኋት። ግቢ እያለሁ ዶርም አልነበረኝም ግን space አድር ነበር ስቸክል። ታዲያ ዶርም ያላቸው ልጆች ስለፋጤ ሲያወሩ እሰማ ነበር። የግቢ ተማሪ ሆና በጥናት እና ቴንሽን ጨልላ ስለሞተች ልጅ ከዛም መንፈሷ እዛው ቀርቶ ማታ ማታ እንደምትታይ። ሌላው ታሪክ ደግሞ መንፈስ ሆና ወንዶችን እየጠራች እንደምታሳብድ። ለብቻ ማታ በጨለማ ሲሄዱ ተገልጣ እንደምታባርር። የማያወሩባት አልነበረም። ከሄሪ ፖተር መፅሃፍ ላይ የወጣች ገፀባህሪ ነበር ለኔ የመሰለችኝ። ትመሰጠኝ ነበር።

እና ፋጤ እሷ ትሁን ወይ ሌላ ፋጤ ዜጋው ጋር ስቀላቀል ደግሞ ድጋሚ ተገናኘኝ። አሁን ግን ስንገናኝ ፋጤ እሩቅ እና መንፈስ ሳትሆን እኔው ውስጥ ያለች ነች። ሰፍራብኛለች ለካ። እጅ አጣጣሌ፤ አረማመዴ፤ አቀማመጤ፤ አወራሬ እና ምግባሬ “ወንድ” ሆኜ ቃጭል አንጠልጥዬ ከህብረተሰቡ ወንድ ብሎ ከሚያሰበው ወደ ሴት ያደላው ሁላ ፋጤ ነው። ሴት ሆነው ህብረተሰቡ ወንድ ብሎ ወዳሰቀመጠው ዘይቤ ያደሉትን ሴቶች ግን ምን እንደሚሏቸው እስካሁን አልደረሰኩበትም። ኧረ ስም እናውጣለት።

“ፋጤሽን ቀንሺ” ግን አሁንም አለ። ጥሎብን ከነፋጤያችን ማንነታችን

የሚወገዝበት ሃገር ፈጥሮን በእለት ተእለት ኑሮአችን ፋጤያችንን እንደ ድሮ ራዲዮ tune ማድረግ አለብን። ከዜጋ ጓደኞቼ ጋር ወይም ከተቀበሉኝ ጓደኞቼ ጋር ስሆን እልል የምትል ፋጤዬ ሌሎች ጋር ስሆን ደግሞ ጥቅልል ትላለች። ያው ብዙም አትወጣም ብቅ ብቅ ትላለች እንጂ። ምንም ሳያጠፉ ሁሌ እራስን መቆጣጠር ያስጠላል ግን እውነታው ነው። ከምቀርባቸው ጓደኞቼ ጋር አንቺ በሚል አጠራር ስናወራ ኖረን እና ቆይተን ሌሎች መሃል ስንገባ አምልጦን አንቺ ላለመባባል ያለው ምጥ አንዳንዴ ያዝናናል።

አንዴ ታክሲ ውስጥ ዜጎች ሰብሰብ ብለን ወደ አንድ ማላስታውሰው ቦታ እየሄድን አንዱ ጓደኛችን እያመለጠው አንቺታውን አበዛው። እስሬ በአይኔ እቆጣዋለሁ። ብዙ ጊዜ እኔ “በጩ”[1] ስለሆንኩ እያመልጠኝም። ሚኒባስ ውስጥ ከኋላ አራት ሞልተነዋል። ከፊታችን ሁለት አሉ። የመጀመሪያው ቅሌት፦የአንዱ ስልክ ሌላኛው ጋር ነበር። ስልኩ ጠራ....የደወለው የባለስልኩ ቦይፍሬንድ ነበር። ስልኩ እጁ ላይ የነበረው ልጅ የት እንዳለን ርስት አድርጎት “እንኪ ባልሽ ደወለ” አለ ስልኩን እያቀበለው። ዞሬ ፍጥጥ አልኩበት። ሁላችንም ደነገጥን። ልጁ ያጠፋውን ለማረም ሲደናበር ስልኩን ለመስጠት እጁን እንደዘረጋ “ሚስትሽ ሚስትሽ” ብሎ ድጋሚ ጮኸ። ግማሻችን ክትክት ብለን እንስቃለን። ግማሻችን በመስኮት እንውጣ ወይስ ወራጅ እንበል ብለን ተሳቀናል። አፋችንን እፍን አድርገን ሳቅን። ህዝቤ አላስተዋለም።

ቅሌት ሁለት፦ ያው ደንባራ ጓደኛችን አንቺ አንቺ ሲል በየመሃሉ ተው ተው ብንለውም አፉን ይበላዋል መሰል አሁንም ተሳሳተ። ከጎኑ ስለነበርኩ በክርኔ ደረቱን ደቃሁት። አይይይ ብሎ ካቃሰተ በኋላ “ጡቴን” ብሎ መጮህ። ወራጅጅጅ.... ብለን ግንባራችንን ሸፍነን ላሽ ላሽ....ነበር ማድረግ የነበረብን። ሁላችንም ደንግጠን በመስኮት ወሬ ወሬ ማየት ጀመርን። መድረሻን እስክንወርድ ድረስ ከዛ በኋላ ትንፍሽ ያለም ሰው አልነበረም። ያው ፈስ ያለበት ዝላይ አይችልም ሆኖ እንጂ ነገሩ ጆሮ የሰጠንም አልነበረም።

ፋጤማ አትውለብለብ። ለነገ አትልም። ምናልባት አንድ ቀን ያለስቀቀን ቀጭ ቀምቧ እንል ይሆናል። ፋጤም ተለይታ ማንነት ሳይሰጣት በቃ እኛ ብቻ እንሆናለን። መደበቅም ሳይገባት የተለየች ነገርም ሳትሆን የአንድ ሰው የተፈጥሮ አንድ አካል ሆና ከምንም የማትቆጠር ማንነት ትሆን ይሆናል። በጨለመ ኮሮኮንች መንገድ ኮቴ ከኋላው እየሰማ

[1] በጩ: ፈሪ

እንደሚራመድ ሰው አስሬ ዞር ዞር እያልን አካባቢያችንን ማየት እና መቃኘት ይደክማል። በራሳችን ወገን በዜጋው መሃል ሆነንም “እሷማ ፋጤዋ ከባድ ነው ታስነቃብናለች” ተብለን መገለል እና መፈራትም ያማል። ሰውን በሙሉ ማንነቱ መቀበል ትልቅነት ነው። ፈረንጆች “የመስታወት ቤት ውስጥ ቁጭ ብሎ ድንጋይ መወርወር” ይሉታል። ፋጤ ኖረንም አልኖረንም ዜጋ ከሆንን አለቀ ዜጋ ነን። ፋጤ ምናምን ተባብለን ስንገፋፋ እና ስንከፋፈል ድንጋይ እየወረወርን ነው። ከሸ ያለ ቀን የመስታወት ስብርባሪ ውስጥ ያለነውን ሁላችንን ይወጋል።

# እታለሜ
## ዛክ
አንተ/እሱ

ቅዥቅዥ ያልኩ ልጅ ነበርኩ። መያዣ መጨበጫ የሌለኝ። እዚ ሲሉኝ እዛ፣ እዛ ሲሉኝ እዚ ነው ምገኘው። ትዝ ይለኛል መጀመሪያ ደረጃ ተማሪ እያለሁ የትምህርት ቤታችን ታዋቂ ረባሽ ነበርኩ። ረባሽ ነኝ ስል የቀልድ አይነት አይደለም። አንድ ጊዜ ከክፍላችን ዝምተኛ ተማሪ ጋር አስቀምጠውኝ ከአምስት ደቂቃ በኋላ ልጅቷ ጮክ ብላ ስትስቅ ሁሉም ተማሪ ነበር የደነገጠው። ከዚህ ቀደም ልጅቷ ዝምተኛ ከመሆኗ የተነሳ ዝጋታም ጋግርታም እያልን ነበር ምንጠራት። እሱ አልሆን ሲላቸው ከክፍላችን ሁሌ አንደኛ ከሚወጣው ልጅ ጋር አስቀመጡኝ እሱንም ወሬኛ አደረኩት። ይህ ሁሉ ሙከራ አልሳካ ሲላቸው ወንበሬን ከሌሎች ተማሪዎች ወደፊት አስጠግተው ብላክ ቦርድ ፊት ለፊት አስቀመጡኝ የዛኔ ደሞ ከጀርባዬ ላሉት ደብዳቤ እየፃፍኩ አስቸገርኩ። ረባሽ ነበርኩ ስል አሁን ምን ለማለት እንደፈልኩ የገባችሁ መሰለኝ። የክፍላችን ሳይሆን የአጠቃላይ የትምህርት ቤቱ ረባሽ ተማሪ ነኝ። ትምህርት ቤታችን እጥር ምጥን ያለች ስለነበር ሁሉም ተማሪ ይተዋወቃል። እኔን ማያውቀኝ የለም።

ረብሻዬ ለዛ አለው መሰለኝ አስተማሪዎቼ አይጨክኑብኝም። ተማሪዎቹ ግን በሁለት ይከፈላሉ በጣም የሚወዱኝና አምርረው የሚጠሉኝ። መሃል ላይ ያለ የለም። ለሚወዱኝ ጥርስ የማላስከድን ተጫዋች ስሆን ለሚጠሉኝ ደሞ መዝገር ነገር ነበርኩ። የማልፋታ ነገረኛ። ምንም ቢሉኝ አልናደድም። ሰድበው እያናድዱኝም ብቻ ሳይሆን አይችሉኝም። ሊመቱኝ ከሞከሩ ያ ሌላ ነገር ነው። መከታ የሆነች እህት አለችኝ።

ከእህቴ ጋር በመሃላችን ያለው የእድሜ ልዩነት የአሰራ አንድ ወራት ልዩነት ነው። ስንመዘገብ ሁሌ አባታችን አንድ ክፍል እንድንሆን ያደርገናል። እሷ ከኔ በተቃራኒ ዝምተኛ ነች። ጓደኞቿ ወንዶች የምታዘወትረው ኳስ እና ጅምናስቲክ…

እኔስ?

ጓደኞቼ ሴቶች የማዘወትረው አሉባልታ፣ ሱዚ፣ ስኞ ማክሰኞና አባሮሽ። ሱዚ ማንም አይችለኝም ሰው ጉልበት መዝለል የሚቀለውን ያህል ነው ብብት ምዘለው። እረፍት ሰአት ላይ የሴቶቹ ጀማ መሪ ነበርኩ። ከኔ ጋር የተቧደኑ ሁሌ በሚባል መልኩ ያሸንፋሉ። ካላሸነፍን እፍርቴን ማንም አይችልም። ግግም ብዬ ነው ምከራከረው። ያኔ ነው "ይሄ ሲያስጠላ ሴታሴት" የሚለው ስድብ ሚከተለው። እኔስ ከማን አንሼ አንገቴን እየወዘወዝኩ " ምናገባሽ ... ቀናሽ... ተበለጥሻ ..." እያልኩ እንጣጣለሁ። አፍ እላፊው ወደ ፀብ ሊጠጋ ሲል ኳስ ሜዳ ያለችው እህቴ የያዘችውን ኳስ ጠልዛ እየበረረች ትመጣለች ያኔ ማንም ትንፍሽ አይልም። የመጀመሪያውን ቡድን አፍርሼ አዲስ መስርታለሁ። ያቺ የሰደበችኝ ልጅ እኔጋም ሆነ ተቃራኒው ቡድን አትገባም። ነገረኛ ነኝ ስል የቀልዴን አይደለም።

እህቴ ተማሪ ብቻ ሳይሆን አስተማሪዎችም ቡሊ ሊያደርጉኝ ሲሉ ዝም አትልም። ወንድሜን አትናገሩት ብላ ጠበቃ ትቆማለች። እኔ ምጀምረው ፀብ በሷ አጭር መልስ ይደመደማል። ልጅነቱ ይሁን በአብዛኛው ተማሪ መወደዴ ይሁን ወይ የእህቴ መከታነት በባህሪዬ ምክንያት የምሰደበው ስድብ ብዙም አስጨንቆኝ አያውቅም። ሴቱ ሲሉኝ ምን አገባሽ ነው መልሴ። ወደ ውስጥ አስገብቼ አላጠነጥነውም። ይህ ባህሪዬ ቤት ውስጥም ያው ነው።

እናታችንን በልጅነታችን ስላጣንና አባቴ ሌላ ሚስት ስላላገባ ታላቅ እህታችን ከተቀጠሩ አጋዧቿ ጋር በመሆን ነው ያሳደገችን። ይህቺኛዋ እህቴ አብራኝ ከምትማረው እህቴ ትለያለች። እናታችን ነች። በስሟ አንጠራትም። እማ ነው ምንላት። ከአባቴ ቀጥላ የቤቱ ራስ እሷ ነች። አቤት ስወዳት። አቤት ስትወደኝ። እኔ ገና ከእንቅልፌ ስነሳ እየዘፈንኩ ነው ምነሳው። ቤት ውስጥ ሳቅ ፈጣሪ እኔ ነኝ። ያኔ እንዳሁኑ የቲቪ ቻናል የለም። አንድ ያለው ኢቲቪ ነው እሱም ማታ አስራ ሁለት ሰአት ጀምሮ ለሊት ስድስት ሰአት ነው ሚያቆመው። በመሃል ቲቪ አፍሪካ የሚል ቻናል መጣ እሱ ላይ የሚታዩ የአፍሪካ ሙዚቃዎችን እየሰማሁ የእኩያ እህቴን ሽንሽን ባለአበባ ጉርድ ቀሚስ (ሬዲ ሜድ ነበር ሚባለው) እሱን ለብሼ በካልሲ ጡት ሰርቼ ለእህቶቼ ወገቤን እያሾርኩ ደንስላቸው ነበር። ብቻዬን ህብረት ትርኢት ነበርኩ።

ህይወት ቀላል ሆና ሳለ የሆነ አመት ላይ አምስተኛ ወይ ስድስተኛ ክፍል እያለን ከኛ ሰፈር ራቅ ያለ ቦታ ጥሩ ትምህርት ቤት ሲከፈት እኔ

እዛ ገባሁ። የዛን ዓመት እኩያ እህቴ በተደጋጋሚ እያመማት ስለነበር ለቤት ቅርብ የነበረው የቀድሞ ትምህርት ቤታችን እንድትቀጥል ሆነ። መጀመሪያ ሰሞን አዲሱ ትምህርት ቤት ደስ ብሎኝ ነበር። ጊቢው ሰፊ ነው መጫወቻዎቹ ደስ ይላሉ። ግን እንደ ቀድሞ ትምህርት ቤቴ አልሆን አለኝ። እህቴ እዚ የለችም። ጭምት ነገር ሆንኩ። በአለባበሴ በአካሄዴ በአወራሬ ሲቀልዱብኝ እንደ ቀድሞው በኩራት ምን አገባህ? ምን አገባሽ ቀናሽ ማለት አቃተኝ። ጓደኛ ማፍራትም ከባድ ሆነ። ጓደኛ ለማፍራት ምሳቃዬን ለሰው ሰጣለው ምሳዬን በልተው ሲጨርሱ ይሰድቡኛል እንጂ ጓደኛ አይሆኑኝም። እዚ ከኔ ቀድመው የገቡ ልጆች የገነቡት የጓደኝነት ቡድን ውስጥ መግባት ከባድ ሆነ። ደሞ የሆነች ልጅ አለች ሁሌ ከሩቅ ጠርታ ምታሰቅብኝ።

የምሰራች.... ሙሉ ግቢው ምስር ነው ሚላት። በጣም ቆንጆ፣ በጣም ቀጫጫ የሆነች። እኔ አምስት ወይ ስድስተኛ ክፍል ነኝ እሷ ደሞ ሰምንተኛ ክፍል። ሰምንተኛ ክፍል ማለት ለኤለመንተሪ ተማሪ ልክ እንደ GC እና Fresh ተማሪ ማለት ነው። ምስር ግቢው ውስጥ ከማንም የበለጠ እውቅና አላት። እሷ ያለችው ይሆናል። የተማሪዎች ተወካይ ነች፣ ግቢው ውስጥ ያሉ ክለቦች ሁሉ ፕሬዝዳንት እሷ ነች። እኔ ደሞ የሰፈሬ አንበሳ የዚህ ትምህርት ቤት ደሞ መቀለጃ ነኝ። ምስር ጥምድ አድርጋ ይዛኛለች። አንድ ቀን ገና በጠዋት ወደ ግቢ ስገባ ከሩቅ ጠራችኝና ትንሽ ከቀለደችብኝ በኋላ፣ አዘወትሬ ከዩኒፎርሜ ስር ደማቅ ቀለማት ያላቸው ቲሸርቶች ስለምለብስ፤ ዛሬ ስም ላውጣልሽ ብላ ስም አወጣችልኝ። ቀለሟ።

የዛን ለት እረፍት ስንወጣ የግቢው ግማሽ ተማሪ አዲሱ ስሜን ሰምቶ ነበር። በነጋታው.... በሳምንቱ ሁሉም ተማሪ ስሜን ረስቶ መጠሪያዬ ቀለሟ ሆነ። ያን አመት ድምፄንም ስሜንም ተቀምቼ፣ እንደዛ ለያዥ ለገዥ ያስቸገርኩ ሰው እንዳረጀ አንበሳ ሆኜ አለፈ። በሚቀጥለው ዓመት ሞቴ ይመጣል እንጂ እዛ ትምህረት ቤት አልማርም ብዬ እህቴ ወዳለችበት ትምህርት ቤት ተመለስኩ። አሁን ፈገግታዬም ነገረኛነቴም አብሮኝ መጣ። እህቴ አለቻ። ወደ ቀድሞ ትምህርት ቤቴ በተመለስኩ ሳምንት ሳይሞላኝ በህይወቴ ለመጀመሪያም ለመጨረሻም ጊዜ ተደባደብኩ። ኤልሳ ከምትባል ልጅ ጋር። አስተኝታ እስኪበቃኝ ድረስ እሽት አድርጋ ወገረችኝ። ይህን የሰማችው እህቴ በማግስቱ ከመሃል ሜዳ የጠለዘችው ኳስ ሰኞ ማክሰኞ ትጫወት የነበረችውን ኤልሳን ከመሬት ደባለቃት። እኛም ወይ አጋጣሚ ብለን አለፍነው። ከዛን ቀን በኋላ ሰው

እጁን እንሰቶብኝ አያውቅም እኔም ሰው ላይ እጄን አንሰቼ አላውቅም። እውነት ለመናገር የዛን ቀንም ኤልሳ እንጂ እኔ እጄን አላነሳሁም።

ሃይ ስኩል ስገባ ዝጋታም ሆንኩ። መንቀዥቀዤ ጠፋ። እህቴም ረጋ አለች። ለመጀመሪያ ጊዜ “ይሄ ልጅ ቡሽቲ ነው እንዴ?” ተባልኩ። ትርጉሙን ባላውቀውም ስድብ መሆኑ ግን ገብቶኛል። እንደቀድሞው ስድቦችን በስድብ ከመመለስ ይልቅ ወደ ውስጥ እስገብቼ ማጠንጠን ጀመርኩ። የሆርሞን ለውጥ ሲመጣ ነገሮች እንደ ኤለመንተሪ አልሆን አሉኝ። እዚ ደሞ የሆነች ነቀዝ የሆነች ልጀ ጥምድ አድርጋ ያዘችኝ። ሁሌ ኮሪደር ላይ ስንገናኝ “Her” ብላ ነው ምትጠራኝ። ክላስ ለመቀያየር ወይም እረፍት ሰዓት ስንወጣ ወይ ወደቤት ስንሄድ ወደ ክፍል ስንገባ ብቻ ጆሮ ግንዴ ስር አለች። እሷ “her” ስትል ሙሉ ኮሪደሩ ነው ሚያሽካካው እኔ ደሞ ሙቅ ውሃ ውስጥ እንደገባ ጎመን ኩምሽሽ ነው ምለው። ብቻ ሃይስኩል ይሄ ነው የሚባል ጥሩ የጓደኝነት ሆነ የትምህርት ቤት ትውስታ ሳይኖረኝ አለፈ።

ከእህቴ ጋር ተያይዘን ዩኒቨርሲቲ ገባን። አንድ ከተማ የተለያየ ካምፓስ ነበር የደረስን። እሷ ከጎኔ በመሆኗ ደስታዬ ወደር አልነበረውም። የሆነ የመተማመን ስሜት ይሰማኛል። ሃይስኩል ባስተማረኝ መሰረት ግቢ ስገባ ጭምት ለመሆን ጥረት ማድረግ ጀመርኩ ተሳካልኝ። ግን ይህ የቆየው ለሁለት ሴሚስተር ብቻ ነበር። ሁለተኛ አመት አንደኛ ሴሚስተር ጀምሮ አንድ እስተማሪያችን ጥምድ አድርጎ ያዘኝ። ሰውዬው እስተማሪያችን ብቻ ሳይሆን ዲፓርትመንት ሄዳችንም ስለነበር ነገሩን ትንሽ ከበድ አደረገብኝ። ከሱ ውጪ ከአብዛኛው የዲፓርትመንታችን ልጆች ጋር ጥሩ ቅርበት ነበረኝ። የሆነ አለ አይደል ርቀቱን የጠበቀ ቅርርብ። በመከባበር ደረጃ ያለ አፍ እላፊ የሌለው ቅርበት ነበረን። ይህ እስተማሪ ግን አልፋታህ አለኝ። እንዴ በህይወቴ የማረሳውን ነገር አደረገ።

ሁለተኛ አመት ሁለተኛ ሴሚስተር ይመስለኛል። የሆነ ፀሓይ ሚበረታበት ወር ነው። የሱ ክላስ ከሰዓት ስምንት ሰዓት የነበረ ቢሆንም በሙቀቱ ምክንያት ወደ ማታ አሥራ ሁለት ሰዓት ተቀይሯል። ትዝ ይለኛል ከጓደኛዬ ጋር እርፍደን ነበር ወደ ክላስ የደረስነው። እንደተለመደው መጨረሻ ወንበር ላይ ጎን ለጎን ከተቀመጥን በኋላ ቀና ብዬ ዋይት ቦርዱን ሳይ ያየሁትን ነገር ማመን አቃተኝ። ነጩ ቦርድ ላይ በቀይ ማርከር “ Post modernization and homosexuality”

ይላል። ነጭ ላብ አላበኝ። ምነው የዛሬን ክላስ በቀረው። ምነው እግሬን በሰበረው እያልኩ ትምህርቱ ቀጠለ። እኔ አንዱንም ነገር አልሰማውም። አስተማሪውን ቀና ብዬ ማየት አልቻልኩም ግን እሱ እኔ እያየ እንደሚያስተምር ልቤ ነግሮኛል። ለአርባ አምስት ደቂቃ አቀርቅሬ ኖት እንደሚይዝ ሰው ሆኜ ክላሱ አለቀ። መጨረሻ ላይ “ በዚህ ርዕስ ላይ ተጨማሪ ጥያቄ ካላችሁ ስሜን ጠርቶ እሱን ጠይቁ” አለ። ተማሪው እንዳለ ዞሮ አየኝ። ላቤ ደብተሬ ላይ ጠብ አለ። የሆነ እንደ ማቅለሽለሽም...፣ እንደ ማጥወልወልም... እንደ ራስ ምታትም... ብቻ ዝብርቅርቅ ድብልቅልቅ ያለ ስሜት ተሰማኝ። ከተማሪ መጨረሻ እግሬን እየጎተትኩ ከክላስ ወጥቼ ወደ ዶርም ሄድኩ።

በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ቡሽቲነት በሉት ዜግነት አጥንቴ ድረስ ዘልቆ ተሰማኝ። ራሴን ጠላሁ። ሰው ጠላሁ። ብገላበጥ ብገላበጥ እንቅልፍ እምቢ አለኝ። ተነስቼ ሻወር ወሰድኩ ምንም ለውጥ የለም። ዶርማችን የመጨረሻው ወለል ላይ ሲሆን ለጥገና ወደ ጣራ የሚያስወጣ መሰላል አለው። በሱ ወደ ጣራው ወጣሁ። ጣራ ላይ ቁጭ ብዬ ምናልባትም በህይወቴ ለመጀመሪያም ለመጨረሻም ጊዜ ራሴን ስለማጥፋት አሰብኩ። ከዚህ ላይ ብወድቅስ ብዬ? ከልጅነቴ ጀምሮ የተሰደብኳቸው ስድቦች፣ አጥንቴ ድረስ የገቡትም ስቄም ያለፍኳቸው ሁሉም በማንነቴ የመጡብኝ ስድቦች የዛንለት አሁን የደረሱብኝ ያህል ቁልጭ ብለው ታዩኝ። ከአራተኛ ፎቅ ላይ ራሴን ብጥል ሚቀበለኝ ኮንክሪት በረንዳ ነው። የመሞት እድሌ ምናልባትም ዘጠና አምስት ከመቶ ነው። ግልግልም አይደል? ራስን ስለማጥፋት ማሰብ ከጀመርን ለመኖር የሚያጓጉን ነገሮች አይታዩንም። ራሳችንን ለማጥፋት ምክንያት የሚሆኑት ነገሮች ብቻ ናቸው ፊታችን ድቅን የሚሉት። እኔ ደሞ ብዙ ምክንያቶች አሉኝ።

በዚህ መሃል ስልኬ ጠራ። እማ ታላቋ እህቴ ነበር የደወለችው። ከነበርኩበት ሃሳብ የመውጣት ብዙም ፍላጎት ባይኖረኝም እማ ደውላ ስልኩን እያየሁ አለማንሳት ማይቻል ነው። ስልኩን ሳነሳ በደስታ ውስጥ ሆና “እንኳን ደስ አለህ አጎት ሆነሃል አለችኝ”። በእናት የምንገናኛት እህታችን ወልዳ ነበር። መከፋቴን ከድምፄ ተረድታለች መሰለኝ ረዘም ላለ ደቂቃ አዋራችኝ። እኔም የነበርኩበት ድብርት በዛው ጥሎኝ ጠፋ። በየመሃሉ እያሳቀችኝ ከነበርኩበት ሙድ አስወጣችኝ። ለተወሰኑ ደቂቃዎች እንዳወራን ውጪ ነህ እንዴ ንፋስ ይሰማኛል ስትለኝ ነው ሰውነቴ በብርድ እንደደነዘዘ ያወኩት። ከእሷ ጋር እያወራሁ ዶርም

ገብቼ ተኛሁ። በነጋታው ክላስ ስገባ ተማሪዎች በተለየ ሁኔታ ያዩኝ ይሆን የሚል ፍራቻ ቢኖረኝም ማንም ከቁብ ሳይቆጥረኝ የተፈጠረውን ረስተው የራሳቸው ጉዳይ ላይ ነበር ትኩረታቸው። የዛንለት ማታ እማ ባትደውል ኖሮ ግን በህይወት መኖሬ ሃምሳ ሃምሳ ነበር። የማያልፉ የሚመስሉን ቀኖች ያልፋሉ ማለት ይህ አይደል?

ቀናት ተደምረው ዓመታት ተቆጥረው ከአስራዎቹ ወደ ሃያዎቹ ከዛ ወደ ሰላሳዎቹ ገባን። አሁን ብዙ ጓደኞች ኖረውኛል። ፈልጌ ደምና ስጋ ሳያስተሳስረን በምርጫ ቤተሰቦቼ ያደረኳቸው ሰዎቹ ዙሪያዬ ከበውኛል። ከከንፈር አልፌ አልጋ ላይ ወድቄያለው። ለቀጥ ጓደኞቼ ማንነቴን ተናግሬ ማንነቴን ተቀብለውኝ አብረን በሰላም አለን። ብቻ እኔና ጓደኞቼ ከሩቅ ማይቻል የሚመስል ዓለም ለራሳችን ፈጥረን የሉም ሲሉን አይደል የሚል ሰላቅ አይነት ምላሽ እየሰጠን አለን። በአማካኝ ከበፊቱ በላይ በማንነቴ ደስተኛ ነኝ። እውነት ለመናገር ድሮም ደስተኛ ነበርኩ መስሎቼን ሳገኝ ይበልጥ ደስተኛ ሆንኩ።

ከላይ ያለውን ታሪክ ስታነቡ ከሁለቱ እህቶቼ ጋር ያለኝን ቅርበት በትንሹም ቢሆን ተረድታችኋል። አሁን ላይ የሚያስጨንቀኝ ነገር እነሱ እኔን በቀረቡኝ እና ሁሉ ነገራቸውን ባካፈሉኝ ልክ አለመሆኔ ነው። አዎ ዜግነቴ የህይወቴ አንዱ አካሌ እንጂ ሁሉ ነገሬ አይደለም። ነገርግን ይህን የህይወቴን አካል መደበቄ ሁሉ ነገሬ በሱ ዙሪያ እንዲሆን አድርጎታል። በተቻለኝ መጠን ላለመዋሸት ብጥርም የምዋሽባቸው ጉዳዮች ግን ከዜግነቴ ጋር የተገናኙ ናቸው። ጥቃቅን የሚመስሉ ግን ሁለት በጣም ቅርበት ላላቸው ሰዎች ብዙ ትርጉም የሚሰጡ ነገሮችን ከነሱ ጋር መጋራት አለመቻሌ ውስጤን ቅር ያሰኘዋል። መጀመሪያ ከማን ጋር እንደተሳሳምኩ ለእኩያ እህቴ ብነግራት ... ያን ቀን ገና ስሜቱ ሳይለቀኝ ቀድሜ ከሷ ጋር ባወራ ደስታውን አልችለውም።

ይህ ቅሬታ በውስጤ እያለ እማ ለሆነ የቤተሰብ ጉዳይ እኔ ያለሁበት አከባቢ መጥታ እኔ ቤት ለሁለት ሳምንት ልታርፍ ሆነ። ከዚህ በፊት ቤቴ ዘመድ የተባለ መጥቶ ስለማያውቅ ትንሽ ግራ ገባኝ። በዛ ላይ እማ OCD አለባት። በቃ ማፅዳት ነው.. መጥረግ ነው.. እሷ ያለችበት ዝንፍ ሚል ነገር አይኖርም። ማድረግ የምችለው የኔን እቃ አንድ ቦታ ሰብስቤ ለሷ የቁምሳጥኔን ግማሽ መስጠት ነው። እንደዛም አደረኩ። አልጋዬን ለቅቄላት እኔ ጓዜን ጠቅልዬ ወደ ሶፋ ተሸጋገርኩ። እሷ በመጣች በሶስተኛው ቀን አከባቢ የሳምንቱ መጨረሻ ሲደርስ ባለቤቷም መጣ

እኔም ነፃነት ልሰጣቸው በማሰብ ኮተቴን በበርሳዬ ሸክፌ ለሁለት ቀን ጓደኛዬ ቤት ሄድኩ።

ቅዳሜና እሁድን ውሎ ባለቤቷ ተመለሰ እኔም ቅራቅንቦዬን ይዤ ሰኞ ጠዋት ቤቴ ሄድኩ። እንደገባሁ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ሻወር ልወሰድ ፈልጌ ፎጣ ላወጣ የቁምሳጥኑን በር ስከፍት ጥላታችሁ ክው ይበልና ክው ብዬ ቀረሁ። እቃዎቼን ሰድር አድርጋ ደርድራቸዋለች። ያሉኝን ሉብሪካንቶች በአይነት በአይነት፣ ሬንቦ ስከርቭ ተጣጥፎ፣ ሌሎች እዚህ ጋር ማይጠቀሱ ለእርካታ ምንጭነት የምጠቀምባቸውን የግል ቁሶቼን በአይነት በአይነት አድርጋ አስቀምጣቸዋለች። የዛን ሰሞን እንዱ ጓደኛዬ ከውጭ ሲመጣ ያገር ነገር ነው ይዞ የመጣው። አይ ዛሬ ተበላው አልኩ በልቤ። ፋርማሲስት ስለሆነች እንደዚህ አይነት ነገር ላይገባት አይችልም። ቀስ ብዬ ዞሬ አየኋት ዓይን ላይን ተገጣጠምን። ምንም ሳልናገር ሻወር ቤት ገብቼ በሩን ዘጋሁት። ደንግጫለሁ ግን መደንገጥ ባለብኝ ልክ አልደነገጥኩም። አለመደንገጤ ይባስ አስደነገጠኝ። ተለቃልቄ ሰወጣ አልጋ ላይ ሆና የሆነ ነገር እየሰራች ነበር። እኔ ምንም አይነት ነገር ለማውራት በተለይ ደሞ ለመከራከር ዝግጁ አልነበርኩም። ፊቴን ዘፍዝፌ ሶፋ ላይ ሆኜ ፊልም ማየት ጀመርኩ። ስለተፈጠረው ነገር የዛንለት ምንም ሳናወራ አለፈ። በነጋታውም እንደዛው።

የመጣችበትን ጉዳይ ጨራርሳ ልትመለስ እቃዎቿን እያሰናዳች እንደሁልጊዜው ስሜን አቆላምጣ ጠርታ “ቁምሳጥኑ ውስጥ ያለው ነገር አጋጣሚ ነው ወይስ እንደማሰበው ነው?” አለችኝ። ዓይኗን እያየሁ ከምዋሻት የፈለገው ይምጣ ብዬ  እንደምታሰቢው ነው አልኳት። እ… ብላ ጥያቄዋን ልትቀጥል ስትል … እማ ዛሬ ምንም ማውራት አልፈልግም ብዬ አስቆምኳት። ወሬው በዚሁ በአጭሩ ተቋጭቶ እሷም ወደ መጣችበት ተመለሰች።

ከተወሰኑ ወራት በኋላ ለበዓል ሄድኩ። እማ ጋር አርፌ እኩያ እህቴን ደሞ ላያት እሷ ጋር ሄድኩ። ሰላምታ ተለዋውጠን ምግብ ልታቀርብልኝ ወደ ኪችን ስትገባ ተከትያት ገባሁ። ጥሎብኝ ሰርሰሯ መሄድ ወዳለሁ። ከመሶብ እንጀራ እያወጣች አላስችል ብሏት ምንቅር ብላ ዞራ “ ባለፈው እማ የነገረችኝ ነገር እውነት?” ነው አለችኝ። ከጥያቄዋ አዟዟሯ አስገርሞኝ ትንሽ ከሳኩ በኋላ አዎ እውነት ነው አልኳት። እንጀራው ላይ ወጥ ጨምራ ፊቴ ላይ ወርውራ ወጣች። ትንሽ ቆይታ መጥታ የሚጠጣ

ኬኔቶ ቀድታልኝ እሱንም ፊቴ ላይ ወርውራ ሄደች። ትንሽ ቆይታ ስትመጣ በልቼ ጨርሼ ጠበኳት። ጨምር አለችኝ አይ በዚህ ሁኔታሽ አልበላም ብዬ ቀለድኩባት። እ.... ብላ ጥያቄ ልታበዛ ስትል “ አሁን የመጣሁት በዓል ለማክበር ነው ጥያቄ ካለሽ ወይ ማውራት ካለብን ሌላ ግዜ ብዬ ቋጨሁት። እማ ጋር ስመለስ ከእህታችን ውጪ ለማን አወራሽ ብዬ ጠየኳት ለማንም አለችኝ። አመንኳት። በዓሉን አክብሬ ተመለስኩ።

በዚህ ርዕስ ደግመን ሳናወራ ወራት ከዛ ጥቂት ዓመታት ተቆጠሩ። ባለፈው .... አሁን በቅርቡ ስሄድ እነሱ ባያነሱትም ራሴ በጉዳዩ ላይ ለማውራት ተዘጋጅቼ ነበር የሄድኩት። እኔን ሳትጠብቅ እማ አንስታው እኩያ እህቴ ባለችበት አወራንበት። ብዙ ጥያቄና መልስ ነበረው። አብዛኛው ከእምነት ጋር የተያያዘ ነው። የእምነትን ነገር ያው በሎጂክ መመለስ ስለማይቻል መልስ መስጠት የምችለውን መልሼ አንዳንዱን በፈገግታ አለፍኩት። ከእምነት ጋር ያለኝን ግንኙነት ስለሚያውቁ ብዙ አላስጨነቁኝም። እኔም እምነታቸውን አክብሬ ነገር ግን የኔን እውነት እኔ በምነግራቸው የተኖረ ሃቅ ብቻ እንዲመዝኑ አስገንዝቤ ቋጨነው።

እውነት ለመናገር በርዕሱ ላይ ለማውራት ስንነሳ የነበረው ክብደት ውይይቱ ከተጀመረ በኋላ እየቀለለ ሄደ። አንዳንዴ በመሃል የሚጠይቁኝ ጥያቄዎች በሃይል ሲያስቁኝ እነሱም ሳቄን ተከትለው ሲስቁ... አንዳንዴ ለሚጠይቁኝ ጥያቄዎች ደረቅ እውነት ስነግራቸው ወሬው ለዘበ። ልክ ቂጥ እና ቁላ ስል እማ በቃ በቃ ከዚህ በላይ አያስፈልግም ትላለች። እኔ እውነቱን ለማስረዳት ሞከርኩ እነሱም ሊረዱኝ ጣሩ። ዋናው ነገርም እሱ ነበር። ህይወቱን የኖርኩት እኔ ነኝ እውነቱ ያለው እኔ ጋር ነው። እስከዛሬም ያልነገርኳቸው እውነቱን ሲሰሙ ይጠሉኛል ከሚል ፍራቻ አይደለም። በልቤ መቼም እንደማይጠሉኝ አውቃለሁ። እኔ ሁሌም ታናሽ ወንድማቸው ነኝ። ፍራቻዬ የነበረው በኔ ምክንያት ከእምነታቸው ጋር እንዳይጋጩ ነው። በኔ ምክንያት እኔን “ለማዳን” በሚል ምክንያት ራሳቸውን ይበልጥ በፆምና ፀሎት እንዳይጎዱ ነው። እንደ እናት ሆና ያሳደገችኝ ታላቋ እህቴ፣ መከታዬ የሆነችው እኩያዬ ከኛ ምን ጎሎ ነው ብለው እንዲጨነቁ አለመፈለጌ ዝም ያሰባለኝ እንጂ ምድርና ሰማይ ቢገለበጥ እንደማይጠሉኝ አውቃለሁ። እነሱ ጥያቄ ሲጨርሱ እኔ በተራዬ “ እንዴት ግን አትጠረጥሩም?” ብዬ ጠየኩ። ተያይተው እብድ ብለው መለሱልኝ። ያው ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ አይደል ዓይንም እንደዛው መሰለኝ።

አሁን ለኔ ሁሉ ቀሏል። ለእህቶቼ ይቅለላቸው ይክበዳቸው ወደፊት ማየው ይሆናል። እስካሁን ባለን ነገር ላይ የተለወጠ ነገር የለም እንደውም ባለፈው እንዷ እክስቴ ታናናሾችህ አግብተው ወለዱ አንተስ መቼ ነው ወግ ምታሳየን ስትል እማ ነበረች እሱ በህይወቱ ደስተኛ ነው ብላ መልስ የሰጠቻት። ከዚህ በኋላ ብዙ ውይይቶች እንደሚኖሩ ባስብም አሁን ባለን ነገር ደስተኛ ነኝ። በፍቅር ሁሉም ይቻላል።

# Dancing in the Dark: Navigating Addis Ababa's Queer Nightlife

**A.S**
She/her

The dimly lit streets of Addis hold many secrets, and among them, I found a relationship that dared to challenge the status quo. A couple of years ago I was with an older butch woman. I had only had fleeting and mostly sexual relationships with women until I met her. We hit it off immediately and it escalated pretty quickly. Addis buzzes with life during the day but offers little leisure beyond the confines of local bars, enticing siga bet's and the pulsating clubs centered in the city's heart. What it lacks in glitz and glamor it makes up for with its unique blend of rich and diverse culture. There is live music, traditional dance performances and new bars and clubs that are constantly evolving to tantalize the senses. My relationship with my androgynous former partner provided an intimate glimpse into what navigating nightlife as a queer couple in Addis can be like.

Our nightlife escapades always started with evenings of drinking tall bottles of whatever-the-fuck, tearing into raw meat, gored gored, before we headed out for the night. My girlfriend always knew which clubs were popping as she had a group of straight "not-quite-accepting-but tolerating" groups of friends telling her what was hot that day. My girlfriend could easily pass for a man at first glance which meant we always had to be careful, though, because some nights, despite being surrounded by a group of friends, the hateful stares and threats of violence would follow us. It was interesting to note that the level of drama and danger

seemed to escalate more when my partner, who had an androgynous appearance, was with me compared to when I was with feminine-presenting women. The mere sight of a Masculine-looking woman with a femme partner threatened the homophobic men more than two feminine women being together. This highlights how not only gender but also sexuality and power dynamics intersect to produce different treatments of butch and femme lesbians. The anger and hostility directed towards us were palpable, and they were starkly different from the reactions I received when I was with feminine-passing women.

Masculinity is often associated with power and dominance, while femininity is associated with weakness and submissiveness and butch lesbians are seen as challenging traditional gender roles and patriarchal order, which is threatening to the fragile egos of the males in this story and so many untold ones as well. These issues are rooted in patriarchal structures that prioritize the experiences of men, and view anything that challenges this order as a threat. But I digress, my partner's tendency towards confrontation also made us an even easier target for homophobic men. On more than one occasion, she has nearly got into physical fights to defend us both from homophobic men looking to start trouble.

One night, we were at a popular club known for its eclectic blend of open-minded young Ethiopians and Diaspora clientele, with a sprinkle of trash men to add to the mix. The blend of afrobeats, dancehall, and amapiano also created an atmosphere where people felt free to let loose. One time, we were dancing together, not too closely but clearly enjoying ourselves, when a group of young men started loudly making homophobic

comments while glaring in our direction. This is not an isolated incident, there has been a growing trend where individuals come into queer spaces to intimidate and harass members of the community which further exacerbates the trauma and harm experienced by members of the community. In fact, there have been recent incidents where individuals come into spaces that were intended to be safe, and later posted photos and videos on social media. This has put the safety and well-being of the LGBTQI+ community at risk and by exposing queer spaces and the people frequent them they are contributing to a culture of fear and intimidation that has serious consequences. It's not just a violation of privacy but also an active form of violence. That fateful night my partner did not take things lightly. Triggered by their comments, she angrily strode over with a bottle of Ambo in hand and asked what their problem was and if she could help them solve it. Within seconds, they were in each other's faces, screaming and pushing as a crowd gathered around them. The situation escalated rapidly, their hatred clashing with her fierce, almost delusional determination. I hurriedly pulled her away from the brewing chaos, her friends restraining the men as we made our escape. The derogatory cries of "bushti" rang in our ears as we fled in opposite directions, hearts pounding with adrenaline and fear. I rushed down the street to a sandwich shop to call a taxi to take me home. I was worried we had put a target on our backs and given ourselves away as a couple, so I avoided going to that place again. Though she apologized later about her short fuse getting the better of her, I realized then how dangerous her tendency towards confrontation could be for us in Addis. The drama of that night ultimately signaled the end of our relationship, though it continued on for a couple of months after. Even though our relationship eventually

came to an end, I am grateful for the experiences we shared together.

Though Addis's nightlife attracts many open-minded young people, as a queer couple, we constantly felt the need to scan for signs of danger and navigate different spaces and vibes. It was exhausting but also necessary to code switch and assess a space before letting loose. In a city where there are few spaces for LGBTQI+ individuals, we had to be careful and cautious in everything we did. It was moments like these that made me realize the importance of living openly and honestly, despite the risks.

Being queer in Addis Ababa can be difficult and is a constant reminder of the dangers and challenges that we face in our own city. But it also serves as a source of determination to create change and build a more accepting and inclusive nightlife scene for all members of our community because ain't we part of this city too? Damn! I believe that by creating safe and inclusive spaces, we can help break down the barriers that have prevented LGBTIQ+ individuals from living their lives openly and freely expressing themselves. These pages are one among many efforts that are striving to create that space as well as celebrate diversity and equality. Together, we can continue fighting to break down barriers and continue creating safe and inclusive spaces where we can thrive and be ourselves. We can do it FOR US. BY US. And that's on PERIODT.

# የቦኒ ጉዞ

## ቦኒ ጄ

አንቺ

መግቢያ:

የቦኒ ጉዞ በሚል ርዕሰ የማጋራችሁ ይህ አጠር ያለ ታሪክ ትክክለኛ በዜጋ ወይም በlgbtq ማህበረሰብ ውስጥ እንደ አንድ የማህበረሰቡ አካል ፆታዊ ተማርኮዬን እና ከልጅነት ጀምሮ ፃታዬን የምገልፅበትን መንገድ አምኖ ለመቀበል የገጠመኝን ፈተና፣ገጠመኞች ፣ የማህበረሰብ ጫና፣የግል ፍራቻዬን እና በመጨረሻም ተፈጥሮዬን ወድጄ ከራሴ ጋር እርቅ የመሰረትኩበትን ሂደት በአጭሩ ለማጋራት የሞከርኩበት ትክክለኛ የእኔ የቦኒ ታሪክ መሆኑን እገልፃለሁ።

ቦኒ እባላለሁ። ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ (ጌይ) ነኝ። ፆታዬ non binary ሲሆን ግልፅ ለማድረግ biologically የወንድ ሰውነት የተላበስኩ ፆታዬን መግለፅ የምችልበት መንገድ ግን የሴት አካል ተላብሰው ከተወለዱ እንስቶች ጋር ተቀራራቢ የሆነ እና ነገር ግን ከዚህ አኳያ medical transitioning አልምረጥ እንጂ በአመቺ ጊዜያቶች ሁሉ ፆታዬን ያለገደብ የምገለፅ ነኝ።

በአማርኛው በጣም የምመርጠው አንቺ የሚለውን ተውላጠ ስም ነው። ምክንያቱም "አንቱ" "እርሶ" የሚሉ ተውላጠ ሰሞች በእድሜ ለገፋ ሰዎችም ስለምንጠቀማቸው አሻሚ ይሆኑብኛል። ነገር ግን አንቺታን ልምረጥ  እንጂ አሁን ካለው የማህበረሰቡ ሁኔታ እና ካለንበት ሃገር አኳያ ተውላጠ  ስም ላይ ክርር ያለ አቋም የለኝም። ነገር ግን የlgbtq ማህበረሰብ አካል በሆኑ ሰዎች ፆታ ተኮር ነቀፋ እና ትችቶች በእንደ እኔ አይነት ከሁለቱ ፃታዎች ውጭ ራሳቸውን በሚገልፁ ሰዎች ላይ ሲደርስ ያስከፋኛል።

ትውልዴም እድገቴም አዲስ አበባ ነው። ለቤተሰቤ የመጀመሪያ ልጅ ነኝ። የልጅነት ህይወቴ ግርግር ያልበዛው እንደ ሌሎች ወንድ ህፃናት በኳስ መራገጥ እንዲሁም በብይ ጨዋታ ያልታጀበ ግር ግር የሌለው ይልቁንስ እንዲት የአጥር ጥግ ጋራ ቁጢጥ ብሎ ከእንሰት ህፃናት ጋር በቆርኪ  ቡና ጠጡ እቃቃ ጨዋታዎች እና ቅልብልቦሽ ሱዚ አልፎ አልፎም በሰርግ የእቃቃ ጨዋታ ላይ ሴቷን ሙሽራ ሁኖ በመተወን ነበር

የማሣልፈው፡፡
ታዲያ ነፍስ ካወኩ በኋላ ቤተሰቦቼ ሲነገሩኝ በልጅነትህ በጣም ከሚገርመን ነገር እንዱ የሌሎች ወንድ ህፃናት ልብስ ሲቆሽሽ እና በዛ ምክንያት ሲገረፉ የአንተ ልብስ ግን በፍፁም አይቆሽሽም ነበር ደግሞ የሚገርመው ጭቃን በጣም ትጠየፍ ነበር ይሉኛል፡፡እድሜዬም ለትምህርት ደርሶ ትምህርት ከጀመርኩበት ጊዜ ጀምሮም ይኸው ዝንባሌዬ አደገ እንጂ ፈፅም አልተቀየረም፡፡ ግር ግር የበዛበት የወንዶች እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ እንብዛም አይማርከኝም፡፡ ስለ እግርኳስም ሆነ ጠንከር ሰላሉ ስፓርታዊ እንቅስቃሴዎች ምንም አይነት እውቀትም የለኝም፡፡ እስካሁኗ እድሜዬም፡፡

በኋላ በክፍል እና በእድሜ ከፍ እያልኩ ስመጣ አኳኋኔ አረማመዴ አወራሬ እና አሳሳቄ ምግብ አመጋገቤ እና የሰውነት ጥንካሬዬ ሳይቀር ከኔ በዘሪያዬ ያለው የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ከሚጠብቀው የተለየ በመሆኑ ሴቱ የሚል ቅፅል ስም ወጣልኝ፡፡ በዚህ ጊዜ ምናልባት 5 ወይም 6 ኛ ክፍል ብሆን እንጂ ከዚህ የምበልጥ አይመስለኝም፡፡

ታዲያ መጀመሪያ ነገሩ ብዙም የከረረ ባይሆንም በኋላ ግን እኔንም አስቸገሪ ሁኔታ ውስጥ ከተተኝ፡፡ ሁሉም ተማሪ ሴቱ ሴቲላው ባሉኝ ቁጥር መብሸቅ እና አኳኋኔን መጥላት እና መበሳጨት ጀመርኩኝ፡፡ የሚደርስብኝን ጫና ለቤተሰብ የማጋራት ለምድ ስላልነበረኝ ደግሞም ሽንፈት ስለመሠኝ ዋጥ አድርጌ ትምህርት ቤት መመላለሱ ቢያስጠላኝም በትጋት እማር ነበር፡፡ ታዲያ የሚገርማችሁ አመም አርጎኝ ወይም በአንዳች ምክንያት ከትምህርት ቤት የቀረሁ እንደሆን የሚሰማኝ እረፍት እና ደስታ የሚገርም ነበር፡፡

ሰባተኛ ክፍል ሆኜ አስታውሳለሁ በጣም ለቆንጆ ወንዶች ወይም የተስተካከለ ሰውነት አቋም ላላቸው ወንዶች ይህ ነው ብዬ የማልገልጠው የተለየ አድናቆት እና ስበት ይሰማኝ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ጉዳይ እንዲሁ ከአድናቆት የዘለለ ይሆናል ብሎ ማሰብ ሚቻልበት የአእምሮ ብስለት ላይ ግን እንዳልነበርኩ አሁን ወደኋላ መለስ ብዬ ሳስብ ነው የሚገባኝ፡፡

በዚህ ድግግሞሽ ውስጥ ሆኜ ከሌሎች ወንድ ተማሪዎች በተለየ በሚታይብኝ አኳኋን አብረውኝ በሚማሩ ተማሪዎች እየተቀለደብኝ እና ሴታሴቱ እየተባልኩ ሃይ ስኩል ስደርስ በአንዳንድ የቤተሰብ ምክንያቶች

የተነሳ ት/ቤት መቀየር የነበረበኛ ሲሆን በዚህ ጊዜ ለራሴ አንድ ነገር ቃል ገባሁ። ይህም ሴታሴቱ የሚለውን ስሜን እዚሁ የቀድሞ ት/ቤት ጥዬው ለመውጣት እና እኳኋኔን ለማስተካከል ነበር።

ሃይስኩል የገባሁበት አዲሱ ትምህርት ቤት ደግሞ በጣም ለየት የሚያደርገው ተደባዳቢ አስፈሪ እና ተናጋሪ አብሻቂ ተማሪዎች ቢኖሩም ጥሩ ውጤት ለማምጣት የሚፎካከሩ እንዲሁም ትርፍ ጊዜያቸውን በመንፈሳዊ ቦታዎች የሚያሳልፉ ተማሪወች ይበዙ ነበር። በዛ ላይ ለራሴ የገባሁትን ቃል ለመተግበር የማደርገው ጥረት በተወሰነ መልኩ ፍሬ ሳያፈራ አልቀረም መሰል ሴቱ ሳልባል ለተወሰኑ ቀናት ከመበሽቅ እና ከመተረብ እረፍት አደረኩ። ሁለት ሃጎስ ና ቢኒ የተባሉ ጓደኞችም አፈራሁ። ታዲያ በራስ መተማመኔ የተመለሰ እየመሰለኝ መጣ። ነገር ግን ለበፊቱ  አይነት ተረብ እንዳልጋለጥ የነበረኝ ጥንቃቄ ይህ ነው የሚባል አልነበረም። ለመብል እና ለመፃፍ ወይም ሰው ለመጨበጥ ካልሆነ በስተቀር እጄን ከኪሴ የማወጣበት ድግግሞሽ በጣም ጥቂት የሚባል ነበር ይህም ብቻ ሳይሆን በምቆምበትም ሆነ በምራመድበት ጊዜ ለኔ ጭራሹን ምቾት በማይሰጠኝ ሁኔታ እግሬን ከፈት ማድረግ ነበረብኝ።

ከዕለታት ቀን በግምት ት/ቤቱን ከተቀላቀልኩ ሁለት ወር ይሆናል፣ እንደተለመደው ምሣ ሰዓት ላይ ከ ሃጎስ እና ከቢኒ ጋ ምሳ ለመብላት የምሣ እቃችንን ይዘን ከመማሪያ ክፍላችን ወተን ደረጃ እየወረድን ሴቱ ሴቱ የሚል ድምፅ ሰማሁ። ድምፁ አዲስ አይሁንብኝ እንጂ የማን ድምፅ እንደሆነ መገመት አልቻልኩም ነበር። በዛ ላይ እዚህ ት/ቤት ከመጣሁ ጀምሮ የገጠመኝ ነገር የለም ምን አጥፍቼ ነው አልኩኝ ከራሴ ጋ እየተነታረኩ። ነገር ግን ሃጎስ እና ቢኒ ድምፁን ልብም አላሉትም ነበር። በኋላ ምሣ በልተን ስንመለስ ፎቅ እየወጣን ደረጃው ጋር አንድ ልጅ አየሁ። ዴቭ ይባላል የምንተዋወቀው የበፊቱ ት/ቤት ነበር። አሁን ቅድም ማን “ ሴቱ” ብሎ ሲጣራ እንደነበር ገባኝ ። ስንመለስ ግን ሌላ ወሬ ከልጆች ጋ ስለያዘ አላየኝም።እኔ ግን በጣም ከፋኝ ሃጎስ እና ቢኒ መረበሼን እንዳያውቁ ስሜቴን ዋጥ አርጌ ዴቭም ድጋሚ አይቶ እንዳያዋርደኝ ቀደም ብዬ ፎቁን ወጣሁ።

በኋላ ከበዙ ቀናቶች ሽሽት በኋላ ዴቭ ጭራሽ ትምህርት ማቋረጡን ሰማሁ እና ደሰላኝ። አንድ ክፍል ስላልነበርን እንጂ የበፊቱን ስሜን ጠርቶ የዋርጀኝ ነበራ። ከዛ የተነሳ መተላለፊያ ላይ እንዳያገኘኝ በጣም

እሸሸው ነበር፡፡

ሌላው የሳበኝ እና ያስጨንቀኝ የነበረው ጉዳይ ግን ለወንድ ልጅ ያለኝ ድብቅ አድናቆት እና ስበት ነው በተቃራኒው ደግሞ ለሴት ልጅ ምንም አይነት ፍላጎት ሳይኖረኝ አስራ አንደኛ ክፍል መድረሴ ነው፡፡ ወንዶች ድንገት ለጨዋታ እንኳን ከተላፉኝ የሚወረኝ እንግዳ ስሜት ከምን የተሳ ነው ብዬ ራሴ ላይ መመራመር የጀመርኩበት ጊዜ ያጊዜ እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡

በኋላም አስራ ሁለተኛ ክፍልንም በተመሳሳይ አይነት ሁኔታ ከጨረስኩ በኋላ በትምህርቴ በጣም ገበዝ ተማሪ አልሁን እንጂ መካከለኛ ውጤት ከሚያስመዘግቡ ተማሪዎች መሃከል ስለነበርኩ የአስራ ሁለተኛ ክፍል መግቢያ ፈተና ውጤት ይመጣልኝ እና ስሙን መጥቀስ ወደማልፈልገው ካምፓስ ተመደብኩ፡፡

ነገር ግን እንደ እድል ሆኖ የተመደብኩበት ዩኒቨርሲቲ አከባቢ ከፍተኛ የፀጥታ ችግር ስለነበረ ቤተሰቦቼ እኔን እዛ ላለመላክ መወሰናቸው በጣም ደስታን ፈጠረልኝ፡፡

የእኔ ፍራቻ የነበረው የፀጥታው ችግር ሳይሆን ካምፓስ ዶርም የሚጋሩኝ ልጆች ሴታሴትነቴን አውቀው ያገሉኛል ወይም ይቀልዱብኛል የሚል ነበር፡፡ በመሆኑም ከተማ ውስጥ በግል የምማር ከሆነ ግን መጠነኛ ቅርበት ብቻ ፈጥሬ ሴታሴትነቴ ጎልቶ ሳይወጣብኝ መመላለስ እችላለሁ ብሎ ከማሰብ የመጣ ነው፡፡

በኋላ የኮሌጅ ትምህርቴን አዲስ አበባ ውስጥ በሚታወቅ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ተቋም ውስጥ መከታተል ጀምርኩ፡፡ በዚህም ጊዜ አስተውሳለሁ አንደኛ አመት ተማሪ ሆኜ ስለማንነቴ ውስጤ በእጅጉን ይጠይቀኝ ነበር፡፡ በመሆኑም “gay in ethiopia” እያልኩ ፌስቡክና ጎግል ላይ ሰርች አደርግ እና መልሼ እደነግጥና”በሰመአብ ምንሆኜ ነው” ብዬ አጠፋውና ነበር፡፡ በኋላ የአዲስ አበባ ጉዶች የሚል መፅሀፍ አገኝቼ ደበቅ ብዬ ማንበብ ጀመርኩ፡፡ “እጠለል” በመባል የምትታወቅ(የሚታወቁ) አሁን በህይወት የሌሉ ዜጋ የሰጡትን ቃለ መጠየቅ ሳነብ ውስጤ በመገረም ተሞላ፡፡ እውነት እንደዚህ አይነት ሰዎች እኛ ሃገር አሉ? የሚል ጥያቄ ተፈጠረብኝ፡፡ ነገሩን ሙሉ በሙሉ ባላምነውም ገርሞኝ አልፏል፡፡

ከዚያን በዚያኑ ሰሞን ብዙም ሳይቆይ ሰፈር ውስጥ ምክንያቱን ባላስታውሰውም መሸት ካለ በኋላ ወደ ቤት ለመግባት እየተራመድኩ " እንቺ ቆንጆ ስታምሪ እንተዋወቃለን አደል ቁሚና አናግሪኝ" የሚል ድምፅ ሰማሁ በኋላ ዞር ስል የሆነ ቆንጆ ወጣት "እዋ አንቺን ነው" እያለ ራመድ ራመድ እያለ ሲከተለኝ ግብረሰዶማዊያን ሰው ይደፍራሉ ተደፍሬ ነው ወደ ህይወቱ የገባሁት የሚል ምስክርነቶች ስላነበብኩ ውስጤ በጣም ድንጋጤ ተሰማኝ እናም በፍጥነት ተራመድኩ ልጁም አረማመዴን ሲያይ እንደማይደርስብኝ ስለገባው እና ከዚህ በላይ ራሱን አደጋ ላይ መጣል ስላልፈለገ ይመስለኛል መለሰ አለ። ቤት ስደርስ ድንጋጤዬ አልበረደልኝም ነበር እራትም መብላት ስላቃቸኝ መኝታ ቤቴ ገብቼ ብቻዬን መብሰልሰል ጀመርኩ።

ውስጤ" የልጁን መልክ ሳየው ለምን ደነገጥኩ?" "ተሳስቶ ነው ቆንጆ እንተዋወቃለን አደል ብሎ የጠየቀኝ?" "ግብረሰዶማዊያን እዚህ ሃገር አሉ?" "እንቺ ለምን አለኝ ሴታሴት ሆኜ ነበር ስራመድ?" "ከዚህ በፊት በአይኔ አይቼው የማላውቀው ልጅ ነው የት ያውቀኛል?" እያልኩ ጥያቄዎችን በውስጤ ማመላለስ ጀመርኩ። የሰፋ ማህበራዊ ህይወት እንኳ የለኝም ከትምህርት ቤት ልጆች ውጪ ከሰፈር ሰው ጋር እንኳ ትውውቅ የሌለኝ ልጅ ነበርኩ።

በኋላ በሌሎች ጊዚያቶች ሁሉ ልጁ ሊያናግረኝ በሞከረባት በዚያች ቦታ ባለፍኩ ባገደምኩ ቁጥር በዓይኔ ሳልፈልገው ቀርቼ አላውቅም ነበር። ጭራሽ ከዛን ቀን በኋላ ሳላየው ሳምንታት ተቆጠሩ። በእንድ በኩል በዚያን ቀን ሊያነግረኝ ሲሞክር ከመሸሽ ይልቅ ቁርጡን ባወኩ እና ሃሳቡን ባስጨረስኩት የሚል ፀፀት መሰል ነገርም ተሰማኝ በኋላ ደግሞ ምናልባት ፈጣሪ ሲጠብቀኝ ነው ደፍሮኝ ሂወቴን ቢያበላሸውስ ኖሮ የሚል የተምታታ ስሜት ውስጥ ገባሁ።

ከሳምንታት በኋላ ፒያሳ የታክሲ ሰልፍ ላይ አየሁት ከዚያም በጣም ደነገጥኩ። የምንሄድበት መሰመር አንድ ቢሆንም እኔ ከሱ ቀድሜ ተክሲ ደርሶኝ ስገባ እሱ ግን ወደ ኋላ ስለነበር አንድ ታክሲ ውስጥ ሳንገባ ቀረን። ነገር ግን እንደምንም ድፍረቴን አሰባስቤ ዛሬ ይህን ልጅ ማናገር አለብኝ የት እንደሚያውቀኝ መጠየቅ አለብኝ ብዬ ወሰንኩ። ዳሩ ግን አሁን ላይ ሳሰበው የሚገባኝ ነገር እኔም ወደ ልጁ ስለተሳብኩኝ እንጂ ውስጤ ፍላጎት ባይኖር እንደሸሸሁት እቀጥል ነበር። በሰዓቱ

ውስጤ በእሳት እየተጫወትኩ እንደሆነ ቢነገረኝም መጨረሻውን ለማወቅ እና ከልጁ ከራሱ እንደበት ጉዳዩን ለመስማት በነበረኝ ጉጉት ምክንያት ድፍረቴን አሰባሰቤ ባለፈው ሊያናግረኝ የሞከረበት ቦታ ቆሜ ጠበኩት። ከመጣ ለማናገር ዝግጁ ነበርኩ ካልመጣም አንድ ሃያ ደቂቃ ጠብቄው እሄዳለሁ እንጂ ይሄን ጉድ ሳላረጋግጥ ወደቤት አልገባም ብዬ ከራ ሴጋ ተማከርኩ። ሰዓቱ በግምት ሁለት ሰዓት ይሆናል። ልጁም እኔ ከታክሲ ከወረድኩ በኋላ አስር ደቂቃም ሳይሞላ ከተፍ አለ። ገና እንዳየኝ ኮስተር አልኩበት እና በኋላም ያ የማናገር ሞራሌ እና የልብ ልቤ ጠፋ እና መልሶ ፍርሃት ወረረኝ ወደ እኔ እየተራመደ እየሳቀ ፊት ለፊት ሲመጣ እየታየኝ ነው። በዛ ጭር ባለ አስፈሪ ሰፈር እንዲህ አይነት ነገር መጋፈጥ ከባድ ውሳኔ ቢሆንም እኔ ሳመነታ እና ከራሴ ጋር ትቼው ልሂድ አልሂድ እያልኩ ሳወላዳ እሱ ደረሰብኝና ፊትለፊቴ ቆመ። ኮስተር ብዬ በፍርሃት የሚንቀጠቀጠውን እጄን አይቶ የበለጠ ድፍረት እንዳያገኝ እጆቼን ኪሴውስጥ ከተትኳቸው። አንድ ቃል ሳልናገር እሱ እስከሚያወራ ጠበኩ። ልክ እንደ ባለፈው “እእ ቆንጆ “ካለኝ በኋላ ቀኝ እጁን ተከሻዬ ላይ አርጎ ደገፍ አለኝ። ቶሎ ቀበል አደረኩና

“እኔምልህ ወንድሜ የት ነው እንተዋወቃለን ወይ ያልከኝ? ከሰው ተመሳስዬብህ ነው? ባለፈው እንደዛ ያልከኝ እየቀለድክ መሰሎኝ መልሰ ሳልሰጥህ ከሄድኩ በኋላ ጥያቄ ስለሆነብኝ ልጠይቅህ ፈልጌ ነው” ስለው

ከት ብሎ ሳቀ እና ዘና ብሎ “እረ ፈፅሞ አላውቅህም “ብሎ ቁርጤን ነገረኝ።

“የማታውቀውን ሰው እንዴት ታናግራለህ?” አልኩት በብስጭት
እሱም “ደስ ብለከኝ ነዋ” አለኝ።

“ምን ማለት ነው ደስ ትላለህ ማለት? ወንድ እኮ ነኝ። ያነገር ነህ እንዴ?” አልኩት በከፍተኛ ድንጋጤ እሱ ግን ጭራሽ የሚገርም እርጋታ እና ድፍረት ነበረው። ፈገገ እያለ “yes I am gay” አለኝ።

ይሄኔ በጣም ደነገጥኩ። እናም እየተርበተበትኩ “ይህ ጥሩ ነገር አደለም ማቆም አለብህ” አይነት ምክር ልሰጠው መሞከሬ አሁን ላይ በጣም ያስቀኛል።
እሱ ግን እስከ ጥግ ኅትጉቶ ስልኬን ተቀበለኝ። ሰሙም ጆሲ

እንደሚባል ነገረኝ። በኋላም “ሰዓቱ እንዳይመሽ ወደቤት ልግባ” አልኩትና እና በቅጡም ሳልጨብጠው ሮጥኩኝ። የሚገርማችሁ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ በዜግነት ካገኘኋቸው ሰዎች ሁሉ እንደ ጆሲ ደፋር እና ሪስክ ቴከር አይቼ አላውቅም።

ከጆሲ ጋር ቀስ በቀስ መደዋወል እና በአካል መገናኘት ጀምርን እናም ጉዳት እንደማያደርስብኝ እያመንኩት መጣሁ። እኔ ቤት በምሆንበት ጊዜ ስልክ እንደልቤ ማውራት ስለማልችል በብዛት በ sms ነበር ምናወራው።

ለመጀመሪያ ጊዜ ቤቱን ካሳየኝ በኋላ የዛኑ እለት ከንፈሬን ሳመኝ። በሚገርም ሁኔታ የነበረብኝ ፍራቻ ከስሜት ትኩሳት ጋር ተዋህዶ ሲያቃጥለኝ ይታወቀኝ ነበር። ወዲያውኑ ብዙም ሳንቆይ ወሲብ መፈፀም እንደማልችል እና እንደማልፈልግ ነገሬው ወደቤቴ እንዲሸኘኝ ጠየኩት። ለጥቂት ቀናት በተፈጠረው ነገር ፀፀት ውስጥ ገብቼ ጠፋሁበት። በኋላ እራሴ ደወልኩለት እና ድጋሚ ማውራትና መገናኘት ጀመርን። ከዜጋው ማህበረሰብ ጋርም የምገናኝበትን ድብቅ አካውንት መክፈት እንዴት እንደምችል የነገረኝ እሱ ነበር። የሱን መመሪያ በመከተል የድብቅ አካውንት ከፍቼ ከሰዎች ጋ ማውራት እና አሳማኝ ሆኖ ሲገኝም መገናኘት ጀምርኩ። በኋላ ውስጤ የነበረው የሃጥያተኛነት ስሜት እና ወቀሳ ቀስ በቀስ እየቀነሰልኝ ቀለል ይለኝ ጀመር። በተለይም እንደኔ አይነት ህይወት በት/ቤት እና በልጅነት እድሜ የሳለፉ ብዙ ኢትዩጲያዊያን መሰሎች እንዳሉኝ ሳውቅ አዲስ ቤተሰብ እንዳለኝ ያህል ተሰማኝ። እናም በፊት ሳላውቀው በነበረኝ የወንድ ልጅ ባለኝ የስሜት ተማርኮ እንዲሁም bilogically የወንድ አካል ተላብሼ ብወለድም በሚታይበኝ ለየት ያለ የሴት ባህሪ እና አኳኋን የተነሳ ሲሰማኝ የነበረውን የሃጥያተኛነት እና የተረገምኩ አይነት ሰው አድረጌ ራሴን የመቁጠሩን ነገር ሁሉ በህይወቴ ድጋሚ ላይመለስ ወደ ኋላ ተውኩት። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርቴን በመከታተል ላይ በነበርኩበት ወቅት በተለይም ሶስተኛ ዓመት ስሆን ብዙ ፓርቲዎችን መካፈል እና እኔን ከሚመስሉ ሰዎች ጋር መዝናናቱን ገፋሁበት።ከጆሲም ጋር አልፎ አልፎ ብዙ ኢቨንቶች ላይ ስንገናኝ የኔ እንደዚህ መለወጥ ይገርመዋል።

የኮሌጃ ትምህርቴን ባጠናቀኩበት ወቅት እድለኛ ነበርኩ መሰለኝ ብዙም ሳልቆይ ስራ በማግኘቴ ራሴን ከቤተሰብ ጥገኝነት አላቅቄ ቤት ተከራይቼ ወጣሁ። ይህም ለኔ በጣም ጥሩ ስሜት የሚፈጥር አጋጣሚ

ነበር እንዲህ እያለ ጊዜውም ነጎደ። አሁን ስራ ከጀመርኩ ወደ አራት ዓመታት አልፈውኛል። የሚገርማችሁ ሴታሴት እንዳልባል እየተጠነቀኩ መራመድ መናገሩ ቢያታክተኝም ስራዬን በሚገባ ስራለሁ።

የቀረውን ጊዜ ደግሞ ቤት ውስጥ ፊልም በመመልከት፣ ኢንተርኔት በመጠቀም ከሌዝቢያን እህቶቼ እና ከ ጌ እኔን መሰል ወንድሞቼ እና አልፎ አልፎም በጣም ጥቂት ከሆኑ ስለማንነቴ ከማያውቁ እስትሬት (ቀጥ) ወዳጆቼ ጋር አሳልፋለሁ። አሁን ላይ ፈጣሪ ይመስገን ባለኝ ነገር በጣም ደስተኛ ነኝ። የኔ ነፍስ ሰው በሰራላቸው ቦይ ውስጥ ካልፈሰሱ የኩዊር ነፍሶች ውስጥ አንዷ ነች።በዚህ አጋጣሚ ማስተላልፈው መልእክት ፆታ ወንድ እና ሴት ብቻ አይደለም። ሰዎች ራሳቸውን በፈለጉበት እና ህይወት በመራቻቸው መንገድ ሲገልፁ ቅቡል መሆን አለባቸው፡ ግዴታ biological ወንድ masculinities እንዲያንፀባርቅ በቻ መጠበቅ ተገቢ አይደለም። የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ይህንን በፍፁም ለመቀበል እና ዜጋን እንደ አንድ የማህበረሰብ አካል አርጎ ለመቁጠር ባይችልም፤ እኛ ቢያንስ እርስ በእርስ መቀባበል፣ እንዱ የሌላውን ራሱን የሚገልፅበትን መንገድ የመቀበል እና የማክበር ሃላፊነትን እንዲወስድ እመክራለሁ።

# ጅምሬ...

## ዳኒ

እንተ/እሱ

አንድ ሰፈር ነን። አንድ ትምህርት ቤት ነው አብረን የምንማረው። እኔ ደብተሬ ላይ እሱ ኳስ ላይ ጎበዝ ነበርን። እኔ በአስተማሪዎች የምወደድ እሱ ደሞ በተማሪዎች የሚወደድ ልጅ ነው። እኔ ብዙ የሴት ጓደኞች ሲኖሩኝ እሱ ደሞ ትምህርት ቤታችን አሉ የተባሉ “ዱርዬ” ወንዶች ናቸው ጓደኞቹ። ከክላስ ይልቅ ኳስ ሜዳ ነው ውሎአቸው። እሱ ግን ፀባዩ ይለያል። የሆነ የዱርዬ መልክ ያለው ግን ስትቀርቡት በጣም የዋህ እና ገራገር አይነት ሰው ነው። ሲያዩት ደፋር ቢመስልም ሲያዋሩት በጣም አይን አፋር ነው። እኔ በተቃራኒው ሲያዩኝ ቅልስልስ እና አይንአፋር ብመስልም ሰው ስቀርብ ግን በጣም ተጫዋች እና ዝም በል ካልተባልኩ የቆጥ የባጡን ስለፈልፍ የምውል ሙጢ ነኝ።

ሰባተኛ ክፍል ስንደርስ ተመስገን እኛ ክፍል ካለች እና ከኔ ጋር ከምንቀራረብ ልጅ ጋር ፍቅር ያዘው። ልጅትዋ የማትናገር የማትጋገር ነበረች። እሷን በእጅ አዙር ለማግኘት ከኔ ጋር መቀራረብ ጀመረ። ተመሳሳይ የጓደኞች ሰርክል ባይኖረንም እኔ እና እሱ መግባባት ጀመርን። በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ብዙ ግዜ ተገናኝተን አናወራም። እንዳልኩት ጓደኞቻችን አይግባቡም ምርጫችን ፍፁም የተለያየ ስለሆነ እኔና ተመስገን የምንገኘውም ሆነ ጓደኝነታችን የተመሰረተው ከትምህርት ቤት ውጪ ነው። ቀላልም ነበር። ቤታችን ቅርብ ነው። አባቴ ከአባቱ ጋር አንድ እቁብ አንድ እድር ነው አብረው ሚጠጡት። ታላቅ ወንድሜ ከታላቅ ወንድሙ ጋር እጅ እና ጓንት ናቸው። እኔ እና እሱ ብቻ ነበር የቀረነው እኛም እሱ በወደዳት ልጅ ምክንያት መግባባት ጀመርን።

ትምህርት ቤት ያለን የጓደኞች ልዩነትና የክፍል ልዩነት በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ባያቀራርበንም እሱ በወደዳት ልጅ ምክንያት ከትምህርት ቤት ውጪ መቀራረባችን እየጠነከረ መጣ። በተለይ ክረምት ላይ ልጅቷን ማግኛ ብቸኛው አማራጭ እኔ ነበርኩ። ያኔ እንዳሁኑ ሞባይል ስልክ ባለመኖሩ በቤት ስልክ ነበር ሰው ሚገናኘው። የልጅቷ እናት በጣም ሃይለኛ ስለሆኑ ተመስገን መደወል ይፈራል። ባጋጣሚ እናትየው ከኔ ቤተሰብ ጋር ስለሚቀራረቡ እና እኔ ከልጃቸው ጋር አብሬ እንደምማር

ስለሚያውቁ ክረምት ላይ አልፎ አልፎ ስልክ መደወልም ሆነ ሰፈር ሄጄ ከልጆቻቸው ጋር መገናኘትን አይከለክሉኝም። ይህን እድል በመጠቀም ሁለቱን የማገናኘት ስራ ስራ ነበር። በመሃል ተመስገን ሚሰጠኝን አቴንሽንም እየወደድኩት መጣሁ።

አንድ ክረምት ላይ የማንለያይ ሆንን። ምክንያቱ ልጅቷ ብትሆንም አንድ አንድ ነገሮችን አብረን ማድረግ ጀመርን። የምንከራያቸውን የፊልም CD ከመቀያየር አብረን ወደማየት ተሸጋገርን። አብረን ምናሳልፈው ጊዜ እየበዛ መጣ። ልጅቷ ተመስገን ላይ ምንም አይነት ፍላጎት ስለሌላት ከሷ ጋር አብረው የመሆን እድላቸው ጠቧል። እኔ ደሞ ከሌሎች ጓደኞቹ ይልቅ ነገሩን ስለማውቅ ዋና አፅናኝ ሆንኩ። ይህም ቅርበታችንን አጠነከረው በዚህ መሃል አንደኛ ደረጃን ጨርሰን ሁለተኛ ደረጃ ስንገባ ትምህርት ቤታችን ተለያየ። እሱ ቀድመን የምንማርበት ሲቀጥል እኔ ሌላ ራቅ ያለ ትምህርት ቤት ገባሁ። ጓደኝነታችን ግን ከምንጊዜውም በላይ ሃያል ሆነ። ሁለት ወይም ሶስት ቀን ከቤት ስንቀር ቤተሰቦቻችን ጭምር የሚናፍቁን ሆንን ሁለት ቀን ቤት ካልመጣ ጥራው እባላለሁ እሱም እንደዛው። አንዳችን አንዳችን ቤት ባናድርም ውሏችን ግን አንድ ላይ ነው። እኔ ክፍሌን ከታላቅ ወንድሜ ጋር ስጋራ እሱ የብቻው ክፍል ነበረው። ፊልም ብዙ ጊዜ እሱ ክፍል ነው ምናየው።

አልፎ አልፎ ከከተማ ወጣ ብለን የእግር ጉዞ እናደርግ ነበር። አንድ ቀን walk አድርገን ተመልሰን እሱ ክፍል ገባን። እሱ እግሩን ዘርግቶ ሲቀመጥ እኔ በተቃራኒው አቅጣጫ ጭኑ ላይ ራሴን አሳርፌ ተንጋልዬ ወሬ ጀመርን። ብዙ ካወራን በኋላ አንድ ነገር ትኩረቴን ሰረቀው። ቁላው ትር ትር እያለ ከጭንቅላቴ ጋር እየተጋጨ ነበር። ቆሞብሃል ወይ ብዬ ጠየኩት አዎ አለኝ። ለትንሽ ደቂቃ awkward ሆነን ቆይተን ወሬ እችንን ቀጠልን። ለኔ ግን ያቺ ቅጽበት ምትረሳ አልነበረችም። ቤት ገብቼ ማሰላሰል ጀመርኩ።

ያኔ ዘጠነኛ ክፍል ነበርኩ። ልብ በሉ ስለ እሱ ስሜት እንጂ ስለራሴ አውቅ ነበር። ማለት ምንም ያየሁት ወይም የሰማሁት ነገር ኖሮ ሳይሆን ለወንድ ልጅ የተለየ ስሜት እንደነበረኝ አውቅ ነበር። ያስደነቀኝ እሱም ተመሳሳይ ስሜት እንዳለው ማወቄ ነው። ይህ ምልክት አእምሮዬ ውስጥ የሆነ ነገር ተክሎ ስላለፈ ከዛ ቀን በኋላ እንቅስቃሴዎቹን በጥንቃቄ ማየት ጀመርኩ። በጨዋታ መሃል ወይም በልፊያ ሰአት እንደሚቆምበት በተደጋጋሚ አየሁ። እንግዲህ የዛኔ እድሜያችን አስራ አራት አስራ

አምስት አከባቢ ቢሆን ነው። እኔ ምንም ማውቀው ነገር የለም። እሱ ግን ቆይቶ እንደነገረኝ ሴጋ[1] መቶ ያውቅ ነበር።

የሆነ ቀን አብረን እሱ ክፍል ቁጭ ብለን ስንላፋ ቁላው ቆሞበት አየሁ። ቀስ ብዬ ስፈራ ስቸር ነካሁት ምንም አላለኝም። ላውጣው አልኩት። እሺ እንደፈለክ አለኝ አወጣሁት። ከዛ ቀን በፊት ከራሴ ቁላ ውጪ ነክቼ ማላውቀው እኔ ቁላውን ካወጣሁት በኋላ ምን እንደማደርገው ግራ ገባኝ። እስከዛን ቀን ድረስ  ሴጋ መትቼም ሆነ የወሲብ ፊልም አይቼ አላውቅም ነበር። እሱ ሁሉን ነገር አሳየኝ። ቅባት እጄ ላይ አድርጌ እያሸሁ አስረጨሁት። እሱም ለኔ እንደዛ አደረገልኝ። የመጀመሪያዬ ስለነበር ስሜቱ መግለፅ ከምችለው በላይ ደስ ይል ነበር።

ከዛን ቀን በኋላ ራሳችንን በራሳችን ማርካት የየቀን ተግባራችን ሆነ። በመሃል መሳሳም ጀመርን። ጓደኛነታችን ይበልጥ ጠንክሮ የማንለያይ ሰው ሆንን። እወድሃለው እንባባላለን። ከትምህርት ቤት መልስ አብረን ምናሳልፈው ጊዜ አልበቃ ብሎን ክላስ እየፎረፍን አብረን መዋል ጀመርን።

ተመስገን ለሴት ልጅ ስሜት ቢኖረውም ከኔ ጋር አብረን የምናደርጋቸው ድርጊቶችን ግን አላቆምንም። ያኔ ባይሴክሽዋል[2] ምን እንደሆነ እናውቅም። እኔ አስራ ሁለተኛ ክፍል ስደርስ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ጀመርኩ። እስከዛ ድረስ ብዙም የቤተክርስቲያን ሰው አልነበርኩም። ተመስገንም እንደዛው። አስራ ሁለተኛ ክፍል ላይ ግን ሃይማኖተኛ ሆንኩ። ልክ የሶዶምና ጎሞራን ታሪክ ሳነብ ለተሜ ነግሬው የምናደርገውን ነገር ማቆም እንዳለብን ተስማምተን አቆምን። አብረን አንድ ክፍል ውስጥ ብቻችንን ስንሆን ምን ሊፈጠር እንደሚችል ስለምናውቅ በተቻለን መጠን ከቤት ውጪ መገናኘት አዘወተርን። ቀስ እያልን መገናኘታችን እየቀነሰ መጣ። በዚህ መሃል ተመስገን ከሌላ የኔ ሴት ጓደኛ ጋር የፍቅር ግንኙነት ጀመረ።

ነገሩን ከሱ ሳይሆን ከሷ ነበር ቀድሜ የሰማሁት። ሰጠይቀው አለሳልሶት አለፈው። እኔ ያልተቋጨው የመጀመሪያ ፍቅሬ አገርሽቶብኝ ቅናት ያንገበግበኝ ገባ።

እንደምንም አስራሁለተኛ ክፍል ማትሪክ መቶልኝ ዩኒቨርስቲ ልገባ ሆነ። ልሰናበተው በሄድኩበት ምሽት ለመጀመሪያ ጊዜ የወንድ ልጅ ቁላ አፌ

[1] ሴጋ፥ ራስን በራስ ማ ርካት

[2] ለሁለቱም ጾታ ተማርኮ ያለው ሰው

ውስጥ ገባ። ከዚህ ቀደም አንዳችን አንዳችንን በእጃችን ከማስጨረስ የዘለለ አልገፋንም ነበር። የዛንለት ግን በእጅ ብቻ በቂ አልሆነም። የተሜን ቁላ ፊልም ላይ እንዳየሁት ጠባሁለት። የጊዜ አጠባበቃችን አሪፍ ስላልነበር አፌ ውስጥ ጨረሰ። እውነት ለመናገር ጤና ላይ ስለሚያመጣው ችግር ብዙም ግንዛቤው ስላልነበረኝ በግዜው ብዙም ግድ አልሰጠኝም ነበር። የተመሰገን ቁላ አፌ ውስጥ ስለገባ እና ስፐርሙን ስላጣጣምኩት ደስ ብሎኛል። የመጀመሪያዬም ስለሆነ ነው መሰለኝ ለኔ ከሱ ጋር ሁሉን ነገር መጀመር አስደሳች ነገር ሆኖ አለፈ።

አሁን ላይ ሳስበው ተሜ የመጀመሪያው የፍቅር ግንኙነቴ እንደነበር ይሰማኛል። ከሱ ጋር የነበረን ግንኙነት ባለማወቅ እና በየዋህነት የተሞላ ነበር። አብረን የቆየንባቸው ዓመታት ብዙም አስቸጋሪና አልነበሩም። ጥርት ብሎ ሳይሆን ረጋ ብሎ የሚፈስ ጅረት ነበር። ምናየው፣ ምንሰማው የኛን መሰል ሰዎች ታሪክ ባለመኖሩ ከእውቀት ርቀን ነበር። የነበረንን ጥብቅ ጓደኝነት ነው ወደ ፍቅር ያሳደግነው። ግንኙነቱም ይለይ ነበር። ፍቅራችን እኩል ነበር። መተሳሰቡ ሚታይ ነው። የመጀመሪያ ንፁህ ፍቅር። እናወራበታለን፣ መፅሀፍ ቅዱስ እያነበብን እንከራከርበታለን፣ ምናደርገው ነገር ልክ አይደለም እናቁም ተባብለን እናቆማለን። ግን ደሞ ተመልሰን ከአልጋ እንወድቃለን። እወደው ነበር። እጅግ አብዝቼ። ከሱ ጋር የነበሩኝ ሶስት ዓመታት ምናልባትም እጅግ ጤናማ የሚባሉ የፍቅር ዓመታቶቼ ሳይሆኑ አይቀሩም።

ግንኙነታችን ውሉ ሳይታወቅ እኔ ወደ ግቢ ሄድኩ። ከተሜ ጋር የነበረን ግንኙነትም በዛው ከቀን ወደቀን እየደበዘዘ.... እየደበዘዘ..... ሄደ።

ዩኒቨርሲቲ ገባሁ...

ዩኒቨርሲቲ ለኔ ጥሩ ቦታ ነበር። አዲስ ህይወትና አዲስ ማንነት ይኖረኛል ብዬ አስቤ ከተወለድኩበት ራቅ ያለ አከባቢ ነበር የመረጥኩት። ስገባም እንዳሰብኩት ጥሩ ነገር ነበር የጠበቀኝ። የመጀመሪያውን ሴሚስተር ትምህርቴ ላይ ሙሉ ትኩረቴን አደረኩ። ከዶርም እና ከክላስ ውጪ ብዙም ወዲ ወዲያ አልልም። ዶርም ውስጥም ሆነ ክላስ በተቻለኝ መጠን ቁጥብ መሆንን መርጬ ጓደኛ ሳይኖረኝ ሴሚስተሩ ተገባደደ።

ወደ ግቢ ስንገባ ጥሪ ዘግይቶ ስለነበር እሱን ለማካካስ የተሰጠን semester break በጣም አጭር ሆነ። ራቅ ካለ አከባቢ የመጣን

ተማሪዎች መሄድ አልቻልንም ብዙም አዋጭ ስላልነበር ቀረን ፡፡ በዚህ መሃል ነው ከታደለ ጋር መግባባት የጀመርነው፡፡ አንድ ክላስ እና ድርማችንም እጠገብ ላጠገብ ነበር፡፡ ከዚህ ቀደም ሰላምታ ቢኖረንም ያ እረፍት ግን በጣም አቀራረበን፡፡ ታደለ ጠቆር ያለ ጠይም ነው፡፡ ከቁመቱ ዘለግ ብሎ ሰፋ ያለ ትከሻ እና ደልደል ያለ ሰውነት አለው፡፡ ከሁሉ ነገር በላይ አይናቹ ይማርካሉ፡፡ ንጹህ ልቡን በአይናቹ ብርሃን ማየት ይቻላል፡፡ አይታችሁት ቀና ሰው መሆኑን ምትገምቱት አይነት ሰው ነው፡፡ ክፍሉ ውስጥ ድምፃቸው ከማይሰማ ተማሪዎች መሃል አንዱ ሲሆን ውጤቱ ግን ጥሩ ከሚባሉት ውስጥ ያስመድበዋል፡፡

እኔ ያለሁበት ድርም ብሎካችን ላይ ካሉ ድርሞች ሁሉ ንፅህ ነው፡፡ መመሪያዎቹን ያወጣሁት እኔ ነበርኩ፡፡ ትዝ ከሚሉኝ ዋና ዋና መመሪያዎች ዉስጥ

- ድርም ውስጥ ጫማ እና ያልታጠበ ካልሲ ማስቀመጥ ክልክል ነው
- ሁሉም ሰዉ አልጋውን ማንጠፍ አለበት
- በሳምንት ሶስት ቀን ድርም እናፀዳለን …(ይህ በአብዛኛው የኔ ስራ ነበር ላይብረሪ ስለማልሄድ ድርም አፀድቼ ድርም ውስጥ ነበር ማጠናው፡፡)
- ድርም ውስጥ ምግብ የበላ ሰው ማፅዳት አለበት የሚሉ ነበሩ፡፡

ከዛ ዉጪ እኔ የማንም ሰው አልጋ ላይ አልቀመጥም ማንም የኔ አልጋ ላይ አይቀመጥም፡፡ በተቃራኒው የነ ታደለ ድርም የቆሻሻው ክምር እና ሽታው ሰው እያስገባም፡፡ የኛ ድርም ጽዳት የመሰጠው ታዴ ውሎው እኛ ድርም ሆነ፡፡ Break ላይ ከቅርብ አከባቢ የመጡ የኔ ድርም ልጆች ወደ ቤተሰቦቻቸው ሄደው ስለነበር ያለው ትርፍ አልጋ ላይ ማደር ጀመረ፡፡ በዛች አስር በማትሞላ ቀን ውስጥ ቅርርባችን በሚገርም ሁኔታ ከዜሮ መቶ ደረሰ፡፡ በፍጹም የማንለያይ አይነት ሰው ሆንን፡፡

ታዴ ሃይማኖቱን በጣም የሚወድ እና የሚያከብር ነው፡፡ ሁሌ እሁድ እሁድ እና ማክሰኞ ቀን ያሉ ፕሮግራሞች አያመልጡትም፡፡ በነበረን የእረፍት ቆይታ እኔ ድርም በሚመጣበት ሰአት መዝሙር መስማት እና የእምነት መጽሐፍትን ማንበብ ያዘወትራል፡፡ የመጀመሪያ አመት ትምህርት ተጠናቆ ወደመጣንበት እስክንመለስ ድረስ ቅርርባችን በየቀኑ ነበር ሚጠነክረው፡፡

የመጀመሪያ አመት ትምህርት ጨርሰን ስንመለስ ካለንበት ዩኒቨርሲት እስከ አዲሳባ አብረን መጣን። ራቅ ካሉ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ በአንዱ ስለነበርን የመንገድ ላይ የአንድ ቀን አዳር ነበረው። እኔና ታዴ አንድ አልጋ ያዝን። ምናልባትም ለመጀመሪያ ጊዜ ነው በአንድ ክፍል ውስጥ ለብቻችን የምናድረው። እኔ ከተመስገን በኋላ ሰው ስሜ አላውቅም እሱ ደሞ አመት አልፎታል። የዛን ለት ፈተናው ከባድ እንደሚሆንብኝ ገብቶኛ ነበር። የያዝው ክፍል ገብተን ተራ በተራ ታጥበን እራት ለመብላት ወጣን። ከራት በኋላ ትንሽ ዎክ አድርገን ወደ ክፍላችን ገባን። ሁለታችንም አልኮል ስለማንጠጣ እና የምናድረው የገጠር ከተማ ስለሆነች ክፍላችን ከመግባት ውጪ ብዙም የምናደርገው ነገር አልነበረም። በዛ ላይ ክረምት ነው። በዛ ላይ ደክሞናል በነጋታው ደሞ በለሊት ነው ምንነሳው።

ወደ ክፍላችን ከገባንበት ሰአት ጀምሮ እኔ በጣም ፈርቻለሁ። ራሴን አላመንኩትም። የማይሆን እቃ ነካክቼ ባለእዳ መሆንም አልፈለኩም። ብቻ በተቻለኝ መጠን የማደርገው ነገር ሁሉ በጥንቃቄ ነበር።

ምሽቱ እየበረታ ሲሄድ ነገራችን ከወሬ ወደመላፋት አደገ። እኔ ልፊያ አልወድም። ነገር ሁሉ በምላስ ሲሆን ነው ደስ የሚለኝ። ታዴ በተቃራኒው ትግል ይወዳል። የምንተኛበትን ጠርዝ ለመምረጥ በሚል የጀመርነው ትግል እየተሟሟቀ ሄደ። ዝቅ ብዬ ሳይ የታደለ ቁላ በለበሰው ቱታ ውስጥ እንደ ጅብራ ተገትሯል። ቆሞብሃል አልኩት። አዎ ያንተም ቆሟል አለኝ። አሳየኝ ስለው እምቢ አለ። አሁን ደሞ ሌላ ዙር ትግል ጀመርን። ታዴ አሸንፎኝ ሳያሳየኝ ቀረ። ልፊያችን የት እንዳለቀም ሳላውቅ ሁለታችንም ከአልጋው ውስጥ ሳንገባ የዛለው ሰውነታችን እንቅልፍ አሸነፈው።

ክረምት ላይ ወደ ቤት ከተመለስኩ በኋላ የሃይስኩሉን ተመስገንን አገኘሁት። በጨዋታችን መሃል ከሴት ጓደኛዬ ጋር የፈጠሩት የፍቅር ግንኙነት እንደዳበረ ነገረኝ። ክረምት አልፎ ግቢ እስክገባ ድረስ አልፎ አልፎ እየተገናኘን ጓደኝነታችን እንዳይሞት አደረግን። በዚህ ወቅት ከተመስገን ጋር ምንም አይነት አካላዊ ንክኪ አልነበረንም። ሰላሳለፍነው ነገርም እናወራም ነበር። ትዝ የሚለኝ ስለ አዲሷ ፍቅረኛው ሲነግረኝ ደስተኛ ነህ ወይ ብዬ መጠየቄ ነው። መልሱ አዎ ነበር። ከዚህ በላይ ሌላ ነገር ውስጥ መግባት አልፈለኩም። እሱ ደስታውን አግኝቷል። የኔ ደስታ ደሞ ጠይም የደም ገንቦው ታደለ ነው።

የክረምቱ እረፍት እስኪያልቅ ከታደለ ጋር በስልክ እናወራ ነበር። የመጀመሪያ ሰሞን በጣም አጭር የስልክ ልውውጥ ነበረን እየቆ ለሰአታት ማውራት ጀመርን። ወደቤት ስንመለስ ያደርንበት አልጋ ቤት የተፈጠረው ነገር ቤት ከመጣሁ በኋላ ተመስገን ሌላ ሰው ወደ ሳገኘው ይበልጥ ወደ ታደለ እንድሳብ አድርጎኛል። አሁን ወደ ኋላ ሚመልሰኝ ምንም ነገር የለም። እሱ ፍቃደኛ ከሆነ እኔ ነፃ ሰው ነኝ።

ጊዜው ደርሶ የሁለተኛ አመት ጥሪ ሲመጣ ከታደለ ጋር አብረን ለመሄድ ተስማማን። ቀኑ ሲደርስ ይበልጥ ይናፍቀኝ ጀምሯል። አዲሳባ ያለ ዘመድ ቀድሞ ትኬት ቆርጦልን ስለነበር እኛ ከሰአት አዲሳባ ደረስን። ባስ የሚወጣው በወጋገን ስለሆነ ለመነሻው ቀረብ ያለ አከባቢ አልጋ ለመያዝ ወሰነን እዛው አከባቢ ለመገናኘት ተስማማን።

እኔ ደርሳለሁ ብዬ ካሰብኩት ሰዓት በጣም ዘግይቼ ስለደረስኩ ታዴ አልጋ ይዞ ጠበቀኝ። ስንገናኝ እንዴት ሰላም እንደምለው እያሰብኩ ነበር። እሱ ግን ምንም ሳይመስለው እንደተነፋፈቁ ሰዎች እቅፍፍፍፍፍፍ አደረገኝና ጭንቀቴን አቀለለው። ሳገኘው ነበር በጣም እንደናፈቀኝ የገባኝ። ትንሽ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ወደ ሩም ሄድን። ደብል አልጋ ነው የያዘው። እዚ እንደ ክፍለ ሃገር አይደለም ተባብለን ተሳስቀን እኔ ተጣጥቤ ልንበላ ወጣን።

በለሊት ስለምንወጣ ብዙ አላመሸንም። በጊዜ ወደክፍላችን ገባን። ፊልም ለማየት እንዲመቸን አንዳኛው አልጋ ላይ ተመቻችተን ፊልም እያየን እያለ እኔ በመሃል ትንፋሼ እየጋለ እና እየተቆራረጠ ይሄድ ጀመር። ፊልሙ ሳያልቅ ታደለ ደክሞኛል ብሎ ተኛ። እኔም እዛው አልጋ ላይ ከጎኑ ተኛው። ታዴ አተነፋፈሱ እንዳልተኛ ቢያስታውቅም እንደተኛ ሰው ሆነ። ሰሩ ገብቼ ከኋላው አቀፍኩት። እጄን ከወገቡ ላይ አንስቶ ወደ ጭኖቹ መሃል ወሰዳቸው። እኔ ደንግጫለሁ ማመንም አቅቶኛል። ምንም አይነት እርምጃ ልወስድ ፈራሁ። ሌላ ምልክት ይሰጠኛ ብዬ እጄን እሱ ካስቀመጠው ቦታ ሳላንቀሳቅስ ቆየሆ። በሂደት በልብሱ ውስጥ ቁላው ሲገታተር እና ትር ትር ሲል ይታወቀኛል። እጄ እዛው ባለበት ነው። ትንፋሹ ሲቆራረጥ ይሰማኛል። የኔም እንደዛው። ጆሮ ግንዱ ስር ነበር ምተነፍሰው። አላስችል አለው መሰለኝ እጄን አንስቶ ቁላውን አስጨበጠኝ። አሁን የይለፍ ፍቃድ እንዳገኘሁ ተሰማኝ። መጀመሪያ በለበሰው ልብስ ውስጥ ቁላውን ዳበስኩለት ። ከዛ ቀስ ብዬ እጄን አስገብቼ ቁላውን አወጣሁትና ማሸት ጀመርኩ። እሱ ትንፋሹ

ይቆራረጣል እንጂ አይኑን ሳይገልጥ እንደበድን ተኟቷል። አዙሬው በጀርባው አስተኛቼው ከንፈሩን ሳምኩት። አይኑን እንደጨፈነ መልሶ ሳመኝ።ወደታች ዝቅ ብዬ ቁላውን አፌ ውስጥ አስገብቼ ጠባሁለት። በዛውም ራሴን በራሴ አረካሁ። ታዴም አፌ ውስጥ ጨረሰ። እኔ ተነስቼ ወደመታጠቢያ ስሄድ እሱ በዛው ተኛ።

ጠዋት ቀድሞኝ ነበር የተነሳው። ሲቀሰቅሰኝ እሱ ተጣጥቦ ጨርሶ ነበር። ስለማታው ምንም ሳናወራ ከሩም ወተን ወደ ባስ ስቴሽን አቀናን። ከአድካሚ መንገድ በኋላ ወደ ማደሪያችን ደረስን። አሁን አንድ ቀን ሳይሆን ሁለት ቀን ነው መንገድ ላይ አብረን ምናድረው። የመጀመሪያው ቀን አዲሳባ ሁለተኛው ቀን መንገድ ላይ። እዚ ደብል አልጋ መያዝ አይጠበቅብንም። ትላንት ማታ የተፈጠረው ነገር እዚም ዛሬ ተፈጠረ። ታዴም ተመሳሳይ ነገር አደረገ። ምንም እንዳልተፈጠረ ሆነ።

በጉዞ አጋጣሚ ወደ ወሲብ ያደገው ግንኙነታችን ግቢ ስንገባም አልቆመም። አሁን ዶርማችን አጠገብ ለአጠገብ ሳይሆን ከላይና ከታች ነው። ብዙ ጊዜውን እኔ ያለሁበት ዶርም ነበር ሚያሳልፈው። ዶርም ግን ብቻ መሆን ቀላል አይደለም። ብዙ ጊዜ ከሁለታችን ውጪ ሰው ይኖራል። አንድ ቀን የከሰአት ክላስ አልሄድ ብዬ ቀረሁ። እሱም ክላስ ቀጣና ብቻችንን ሆንን። እስከዛ ቀን ድረስ በቀን ምንም ነገር አድርገን አናውቅም ነበር። እኔ ግን መታገስ አልቻልኩም። ሁሉም ክላስ መሄዳቸውን ካረጋገጥኩ በኋላ ዘልዬ ከንፈሩን ጎረስኩት። አፀፋውን መለሰልኝ። ያን እለት ደጋግመን ፍቅር ሰራን። ብዙ እንደሱ አይነት አጋጣሚዎችን ሆን ብለን መፍጠር አዘወተርን።

ይህ ግንኙነታችን ለ3 ዓመታት ቢቀጥልም ጥርት ያለ ነገር አልነበረውም። በርዕሱ ላይ አናወራም፣ አንወያይም። በአይን ተግባብተን የምንፈልገውን ከፈፀምን በኋላ ምንም እንዳልተፈጠረ ነበር ምንሆነው። እኔ ማውራት ብፈልግም እሱ ምንም አይነት ፍላጎት ስለሌለው እኔም አላወራም።

የነበረን ወሲባዊ መሳሳብ እጅግ ከፍተኛ ነበር። ብቻችንን ዶርም ውስጥ ከሆንን በፍፁም ልብሳችንን እላያችን ላይ አይቆይም። ስንተያይ ነው ሚቆምብን። ያለንበት ቦታ ቢመችም ባይመችም ብቻችንን በሆንበት በየትኛውም አጋጣሚ እጃችን ወይም እፋችን አርፈው አይቀመጡም። ዶርም ውስጥ ስንሳሳም እንዴ ሁለቴ ተይዘናል ነገሩን ልፊያ በማስመሰል አለፍነው እንጂ።

ይሄኛው ግንኙነት ከመጀመሪያው ይለያል። መተሳሰቡ መዋደዱ መፈላለጉ እንዳለ ሆኖ የቃላት እጠረት ነበረው። ከታደለ ጋር በፍፁም ማውራት እንደማልችል ተረድቼው ነበር። ቀን ቀኖችን እየተካ ሄዶ አራተኛና የመጨረሻ ዓመት ላይ ስንደርስ ነው ለኔ ግንኙነታችን ከወሲባዊ መሳሳብ በላይ እንደሆነ እየገባኝ የመጣው።

ከታደለ ቅልጥ ያለ ፍቅር ያዘኝ። በመጨረሻው አመት ተማሪዎች ስለጥናታዊ ጽሑፋቸው ሲጨነቁ እኔ ከተመረቅን በኋላ በሁለታችን መሃል ስለሚፈጠረው ርቀት ነበር ማስበው። ከተለያየ አከባቢ መምጣታችን በግንኙነታችን ላይ የሚያመጣው ተፅእኖ የገባኝ አሁን ነው።

መመረቅ አይቀርምና የፈራሁት ቀን ደርሶ ተመርቀን ከግቢ ወጣን። በመሃላችን ያለው የመንገድ ርቀት ሳያግደን ለተወሰነ ግዜ አብረን ለመሆን ብንጥርም ሊሆን አልቻለምና በሁለተኛ አመታችን ተለያየን። ስንለያይም ልክ ስንገናኝ እንደነበረው ረጋ ያለ ነበር። ብዙ ጉዳትና የልብ ስብራት አልነበረውም።

እነዚህ ሁለት የፍቅር ግንኙነቶቼ ምንም እና ማንንም ከማወቄ በፊት ተጀምረው የተቋጩ ስለሆኑ ዜጋዊ ቃል የላቸውም። ዜጋዊ ድራማ የላቸውም። በንጹህ ጓደኝነት በህይወት አጋጣሚ ተጀምረው ነው ኩልል ብለው የፈሰሱት።

አንዳንዴ ሰዎች የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪነትን ከውጭ የመጣ ባህል እና በልምምድ የሚዳብር አድርገው ሲያወሩ ስሰማ ግራ ሚገባኝ ለዛ ነው።

**የይዘት ማስጠንቀቂያ**÷ ስለ ያለፍላጎት መጎንተል ስለሚተርክ በጥሩ የአይምሮ ጤና ላይ ካልሆኑ ይህን ገጽ ይለፉት።

# ትዝብት

## ቤቢ

እንተ/እሱ

ጓደኛዬ ነበር በሚቀጥለው ቅዳሜ የሆነ ቦታ ፓርቲ አለ ብሎ የነገረኝ። ከዛ በፊት የነበሩ ፓርቲዎችን እንሂድ ሲለኝ ፍቃደኛ ስላልነበርኩ ይሄንን የምሄድ አልመሰለውም። እንዲሁ ለወሬ ያህል ነበር የነገረኝ። እሺ ሄዳለው ስለው በግርምትና ባለማመን ዓይን እያየኝ ቦታው የሚታወቀው በእለቱ ነው በቃ ራት በልተን እብረን እንሄዳለን አለኝ። እሺ ስለው ብዙም አላሰብኩበትም ግን እንዴ መሄድና ማየት አሪፍ ሃሳብ ብዬ አሰብኩ።

ፓርቲው በሚካሄድበት እለት ማታ ጓደኛዬ በሰው በሰው አጠያይቆ ሄድን። የተዘጋጀው የመኖሪያ ሰፈር ውስጥ ነው። ስንደርስ በግምት ማታ አምስት ሰአት አከባቢ ቢሆንም ምንም አይነት ግር ግር የለም። ዝም ያለ ነበር። ቀድመን ነው መሰለኝ የደረስነው ስለው አይ ሰው ውስጥ ነው ያለው አለኝ። ውጪ አንድ ሰው መጥቶ ከጓደኛዬ ጋር ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ መኪና ማቆምያ ቦታ መርጦልን ወደ ውስጥ ይዞን ገባ። የዋናው በር ትንሿ ተካፋችን እንኳኩቶ ስሙን ሲናገር ከውስጥ ተከፈተልንና ወደ ውስጥ ገባን። G+2 ቤት ያለው ሰፊ ጊቢ ነው። የተወሰነ ሰው አለ። ቤት ውስጥ የተከፈተው ሙዚቃ እዚ ይሰማል። በርከት ያለ ሰው በቤት ውስጥ እንዳለም ያስታውቃል። ከርቀት በሙዚቃ ምት የተዋጠ የሁካታና ጫጫታ ድምፅ ይሰማል። ብዙ ሰው አለ ብዬ አሰብኩ። ትንሽ ፍርሃትና ትንሽ ድንጋጤ ተሰማኝ። ከዚህ በፊት ልምዱ ስለሌለኝ በትክክል ምን መጠበቅ እንዳለብኝ አላውቅም።

የመግቢያ ክፍያ ከፍለን በጓደኛዬ መሪነት ወደ ውስጥ ገባን። ባሩ ውጪ በቤቱ በስተግራ በረንዳ ላይ ነው የተሰራው። ለማስዋብ ሞክረዋል ግን በደንብ አልሞከሩም። ብዙ ነገሮች ከቦታቸው ውጪ ቁጭ ቁጭ ብለው ይታያሉ። የተንጠለጠሉት መብራቶችና ዲም ላይቶች እንዲሁ ለነገሩ እንደተሰቀሉ ያስታውቃሉ። ባሩ ውስጥ ውሃ፣ ቢራ እና አልኮል ይሸጣል። ጥሩ ፈገግታ ያላቸው ሁለት ልጆች ናቸው ሚሸጡት። አንድ ሂሳብ

ተቀባይ አንድ ባር ማን። ስራ እንደበዛባቸው ያስታውቃል ግን ሰውን ሁሉ በፈገግታ ነው የሚያስተናግዱት። ባሩ ጋር ያለው ሰው ሁሉ “እንቺ” እየተባባለ ነው ሚጠራራው።

ቢራችንን ይዘን ወደ ውስጥ ስንገባ ሳሎኑ በሰው ጢም ብሎ ተሞልቷል። ግማሹ ይደንሳል፣ ግማሹ በቡድን በቡድን ሆኖ ይስቃል ይጫወታል፣ ግማሹ የግድግዳውን ጥግ ይዞ ቆሞ ይመለከታል ብቻ ሁሉም ሰው የሚፈልገውን እያደረገ ነው። በቁጥር አነስ ቢሉም በድራግ[1] የነበሩም መለሎ መለሎ ሰዎች ነበሩ። ውጪ ፊልም ላይ የምናየው የዜጋ ፋሽን በደንብ ይታያል። ሙሉ ድራግ ከነበሩ በተጨማሪ የተወሰነ ሜክ አፕ የተቀቡ እዚም እዛም ይታያሉ። አጫጭር ቁምጣ፣ ሂል ጫማ፣ ዊግ እና ወደውስጥ የሚያሳዩ ከላይ አላባሾችን የለበሱ ሰዎች አሉ። ሁሉም ራሱን ሆኗል። ውጪ ላይ የተወሰኑ ሴቶች የነበሩ ሲሆን ውስጥም የተወሰኑ አሉ። ከነበረው የወንድ ዜጋ አንፃር ግን ቁጥራቸው ትንሽ ነው።

እኔ ለቦታው አዲስ መሆኔ ግንባሬ ላይ የተለጠፈ ይመስል አላፊው አግዳሚው እየገላመጠኝ ነው ሚያልፈው። መጀመሪያ ግር ብሎኝ ነበር። ትንሽ ሰቆይ ግን ለክፋት ሳይሆን ከፍ ዝቅ አድርገው ዋጋ እያወጡልኝ እንደሆነ ተነገረኝ። ለተወሰነ ግዜ ጓደኛዬ አብሮኝ ከቆየ በኋላ የሚፈልገው ሰው ሲያገኝ እኔን ጥሎ የልጁን ጭራ ተከትሎ ሄደ። እኔም ሽንቴን ልሸና አንደኛ ፎቅ ላይ ወዳለው መፀዳጃ ቤት አቀናሁ።

ይሄኛው ፍሎር መፀዳጃ ቤት ብቻ ሳይሆን የሺሻ ቦታም ነው። ሁለት ትላልቅ ክፍሎች ሺሻ በሚያጬሱ ሰዎች ተሞልተዋል። ገርበብ ብሎ በተከፈተው በር ሲያዩ ሲያስፈሩ። ምርቅን ብለው የዋሉ ይመስል አይናቸው ፈጧል። ከታችኛው ክፍል ከሚሰማ ውዚቃ ውጪ እዚህ ሙዚቃ ስለሌለ በተወሰነ መልኩ መደማመጥ ይቻላል። ከሺሻ ክፍሎቹ ፊት ለፊት ያለው ኮሪደር እኔ ያለሁበት መፀዳጃ ቤት ወረፋ በምንጠብቅ ሰዎች ተጨናንቋል። ከታች ለሺሻ እሳት ሚያመጣው ልጅ ከብረት የተሰራ እሳት መያዣውን በመቆንጠጫ እየደበደበ ሲመጣ ደንግጠን አየነው። እሳት መያዣው የሚያወጣው የእሳቱ ግለት ከልጁ አቲቱድ ጋር ተደማምሮ ያስፈራል። ሁሉም ጥጉን ይዞ ልጁን እየገላመጠ አሳለፈው።

ስልፌን ጠብቄ ወደ ውስጥ ልገባ ስል ከውስጥ የሚወጣው ልጅ ይሁን ሰውዬ የማያስታውቅ የተደገፍኩትን ግድግዳ በእጆቹ ይዞ ሊሰመኝ ሲሞክር እንደምንም አምልጬ ከፊቱ ዞር አልኩ። ተራዬ እስኪደርስ

[1] ድራግ፥ ወንዶች የሴቶችን ልብስ እና መዋቢያዎችን በመጠቀም ሴቶችን በማስመሰል የሚያቀርቡት ጥበባዊ ትእይንት ነው

ኮሪደሩ ላይ ሌሎችም ሰዎች ተመሳሳይ ነገር አደረጉ። የማይነካ ቦታ ይነካሉ ይጎነትሉኛል። ተው ማለት “እንቺ ማን ሆነሽ ነው?” የሚል ሌላ ድራማ መፍጠር እንደሆነ ስለተሰማኝ ለጊዜው በፈገግታ እያዋዛው አለፍኩት።

መፀዳጃ ቤት ወረፋ መጠበቅ ቀላል ነገር እንዳልሆነ ወዲያው ነው የገባኝ። ግማሹ ጥንድ ጥንድ እየሆነ እየገባ ዘለግ ላለ ግዜ ውስጥ ቆይቶ ይወጣል። አብሪያቸው ስላልገባሁ በትክክል ምን እንደሰሩ መናገር ባልችልም መገመት ግን አይከብድም። ግማሹ ያለ ወረፋው ገብቶ መስታወት ፊት ይቆምና መልኩን አይቶ ይወጣል። ብቻ ብዙ መከባበር አይታይም። ግድግዳውን ተደግፌ ወረፋ ስጠብቅ የሆነ ረዘም ያለ ወጣት ከኔ ቀጥሎ የተሰለፉትን አልፎ አጠገቤ ቆመ። ከኔ ቀጥሎ ያሉት ትንሽ ሰደቡት። ሰድቡ ቀልድ አዘል ስለነበር ከዚህ በፊት መተዋወቃቸው ግልፅ ነው።

አጠገቤ የመጣው ልጅ ትኩር ብሎ እያየኝ “አይቼሽ አላዉቅም አዲስ ነሽ?” አለኝ። ፈገግ ብዬ አዎ አልኩት። ጥሩ ሰው እጅ ላይ ነው የወደቅሽው እኔ አላምድሻለው ብሎ አልፎአቸው ወደ መጣው ልጆች እየጠቆመ “ይቺ አርጊት ነች እንዳታዋሪያት” ሲል ሁሉም ሳቀ። ይቺ ደሞ ብሎ ወደ ሌላኛው ልጅ እየጠቆመ “ ይቺ ደሞ በሽተኛ ነች… “ ብሎ ልጁን ከፍ ዝቅ አድርጎ ካየው በኋላ “ አባላዘራም” ብሎ ጨመረበት። ይሄኔ ከቅድሙ የበለጠ ሳቅ ተከተለ። የመልስ ምቱን ሳልሰማ ከኔ በፊት የገቡት ሁለት ልጆች ወጡ። ስልፈኛው በአሽሙር ተቀብሎ ሸኛቸው። እነሱ ማንንም ከቁብ ሳይቆጥሩ መንገዳቸውን ቀጠሉ።

ነፃ ወደተለቀቀው መፀዳጃ ቤት ገብቼ በሩን ዘግቼ ገና መሽናት ስጀምር በሩ ተከፈተ። ደንግጬ ሰው አለ ብዬ ዞር ስል.. ስልፉን አቋርጦ የገባው ልጅ ነው። ወደ ፊት ተራምዶ መጥቶ ከኋላዬ አቅፎኝ በትከሻዬ ተንጠራርቶ መሽኛዬን ያይ ጀመር። ትከሻዬን እያወዛወዝኩ ከጀርባዬ ላላቅቅው ሞከርኩ። ሽንቴ ከተዘጋጀለት ስፍራ ውጪ ወለሉን አዳረሰው። ሱሪዬን አራሰው። ከትከሻዬ ሳላቅቀው መቀመጫዬን ቸብ አድርጎ ጥሎኝ ወጣ። ንዴቴ ግንፍል አለ። የሱሪዬን ዚፕ ዘግቼ በሽንት የራሰውን ሱሪዬን ላደርቅ ሶፍት ስፈልግ የለም። የእጅ መታጠቢያውን ስከፍት ውሃ የለም የባሰ ንዴቴ ጨመረ። ለመጣላት እስፍስፌ ልጁን በዓይኔ እየፈለኩ ወጣሁ። በአከባቢው የለም። ንቀቱ እናዶኛል።
ከመፀዳጃ ቤት ስመለስ ጓደኛዬ አጣማጁን አግኝቶ ወደ ቤት

እንደተመለሰ የሚገልፅ መልእክት ደረሰኝ። አሁን ብቻዬን ነኝ የሚያስጥለኝም የለም። ጓደኛዬ ጥሎኝ መሄዱን ሳውቅ ሁለት ልብ ሆንኩ አንደኛው ቆይ ቆይ የሚል ሲሆን አንደኛው ደሞ ሂድ የሚል ነው። መቆየትን መርጬ ከበረንዳው ላይ ከተደረደሩት መቀመጫዎች ላይ አረፍ አልኩ። ይሄኔ አንድ እድሜው ሃያዎቹ አጋማሽ ላይ የሆነ ልጅ አጠገቤ መጥቶ ትንሽ ጀነጀነኝና ሄደ። ብዙ ወሬ አለመቻሌ ነው መሰለኝ ሲመጣ የነበረው ነገር እንደጠበቀው ሳይሆንለት ሲቀር ሄደ። ልክ እንደሱ ሌሎች ሁለት ሶስት ሰዎች አዋሩኝ። ከአንደኛው ጋር ስልክ ተቀያየርን። አንደኛው ልጅ ቤቱ ቅርብ እንደሆነና አብረን እንድንሄድ ጠየቀኝ። በትህትና አመሰግናለው ብዬ መለሰኩ። ልክ እሱን ስመልስ ቅድም ሽንት ቤት ልጣላው የፈለኩት ልጅ የሆነ ሰው ይዞ እኔ ወዳለሁበት ሲመጣ አየሁት። የቅድሙ ንዴቴ በርዷል ግን ደግሜ ሳየው ሰውነቴ ሲለዋወጥ ታወቀኝ። እሱ ልክ ምንም እንዳልተፈጠረ “ ስፈልግሽ ስፈልግሽ አጣሁሽ። ይሄ ምን የመሰለ ኮርማ ወንድ መሰለሽ... ደሞ መምቻው “ ብሎ ጠቀሰኝ። አሁን በንዴቴ መቆየት አልቻልኩም ስቄ አብሮት የመጣውን ልጅ ሰላም ብዬ አመሰግኜ ሸኘሁዋቸው።

እነሱ እንደሄዱ እኔ ከነበርኩበት አሰር ሜትር አከባቢ ላይ ሁለት የሚጣሉ ወጣቶችን አየን። ሊያገላግል የመጡ ልጆች አሉ አብዛኛው ሰው ግን ምንም እንዳልተፈጠረ ይጨፍራል። ፀቡ ብዙም ሳይጋጋል ተቋጨ።  እኔም ጓደኛዬ ከወጣ ከትንሽ ሰዓታት በኋላ ይበቃኛል ብዬ ወደ ቤቴ አቀናሁ።

በመንገዴ ሁለት ነገር እያሰብኩ ነበር። አንዱ ፓርቲ ላይ ያሉ ሰዎች አብዛኞቹ ከመሬት ተነስተው ለመጣላት የፈለጉ ይመስል ግልምጫቸው ነው። በጎ መልስ መልሱ ወይም ዝም በሉ አላፊ አግዳሚው እየገላመጠ ነው ሚያልፈው። ሁለተኛው ፍቃድ ሚባል ነገር ያለ አይመስልም። ልክ የውጪውን በር ስታልፉ ማንም ምንም ማድረግ ይችላል። እምቢ ማለት ያስድባል “እና እዚ ምን ትሰሪያለሽ” አይነት አስተያየት ያስከትላል። በዛው ልክ በግልም በቡድንም ሆነው ጥሩ ግዜ ሚያሳልፉ ጓደኞችም ብዙ ናቸው። እንደዚ አይነት ቦታዎች መኖራቸው በጣም ደስ የሚል ነገር ነው። ግን ደሞ ለሁሉም ሰው አይደሉምና እኔ የዛንለት ልምድ ይበቃኛል ብዬ ወሰንኩ።

# Akkee Jireenyaa Saala Walfakkaataa

**Urjii Boriitiin**
(Isa/ Inni)

Waa'een jaalala saala walfakkaataa yeroo ka'u jalqaba waayee maqaa ittiin hawaasni akkee jireenyaa kana jiraatuu ittiin wal waamuutu ka'a. Akka naannawaa Jimmaafi guutuu Oromiyaatti jecha Zega /Lammii jedhu fayyadamuun beekama. Kunis kan ta'e kallattiidhumaan jecha Afaan Amaaraa irraa fudhatameetu Lammii jechuun fayyadamna. Lamaanuu qixa fayyadamna. Kunimmoo haala ittiin iccitiidhaan walii galluufi namni akka dararaa biraa nurraan hin geenyeef jenneetu jecha kanaan wal waamna.

Hawaasni (community)saala walfakkaataa jedhamuu kun akka naannoo kiyyaatti faca'aadha. Tokkummaa hin qabu. Ani hiriyoota heddu fuulbarruu (facebook) dhaan alatti akkaataa haalli mijateefi bakka hiriyoota kiyyaa waliin oollutti jaalala uumamu bu'uureffadhee gamtaa armaan gadii fakkaatu qaba. Gamtaan kunis jaalala jimaa waliin qama'uu, dhugaatii waliin dhuguufi facebookii irratti walbaruu iraatti uumamu kan bu'uurefatee dha.

Nu arfanuu jaalalli saala walfakkaataa kan nuti dhandhamne addatti salmaaf yeroo walbarretti ture. Hiriyoonni kun hundumtuu jalqabarratti hiriyummaaf walitti dhufne. Afran keenya wal qunnamti baay'ee waliin qabna anis hunda waliinu fedhii foonii kiyyaaf karaa adda addaatinis ta'u yeroo dabarseera.

Kanneen biraas jiru namootni akkanatti sababa fedhii fooniif walitti dhihaanne. Warreen kuni marti osoo

naa wajjin wal hin quunnamin dura miirri jaalala saala walfakaataa Aadaa alaa dhufee fi jibbamaa godhanii ilaalu. Wanti kun ifatti dubbatama jedhaniis hin yaadanu turani. Warreen kun hundi ana baayyee na mararfatu . Yeroo saalquunnamtii goonu kondomii fayyadamna ture. kana keessaa namoonni lama gaahila horataniiru. Ilmoos qabu. Garuummoo suuta suuta jaalala(miira) kanaaf bakka kennaniiru.

Waliin Bashannanuufi gamtaan jiraachuun kan eegalame nama lamaan wajjin qaamuu sanarraan immoo nama tokko lama  dabalatee hanga nama 5 tti waliin taphachaa qaamuu aadaa godhanneerra. Yeroo qaamnu immoo hundi keenya uffata miidhagaa uffannee ykn babbareednee qaamna. Kan nama ajaayibu nu hundinuu akka wal hojjannu beekna. Waayee nama saalqunnamtii waliin raawannees waliin dubbanna mudannoo keenyas walii qoodna. Gidduu gidduutti immoo sababa adda addaatin walitti bu'iinsis ni uumama.

Namoonni kun wal arguuf mana nama Zeegaa /Lammii hin taaneettis wal arguun ni danda'ama. Waayee namaa yoo haasofnu garuu ishee jennee saala dubaraan bakka buufnee dubbanna.

Namoota zeegaa/lammii hin taane waliin yeroo qaamnu yookaan dhugnu waayeen zeegaa yeroo kahu ni mormina. Kunis nun galchu namni akka fedhiisaatti haa jiraatu nun tuqin malee waan nu miidhu hin jiru jechuun yaada waljijjiirra. Kanaafuu, hiriyoonni keenya miira jaalala saala walfakkaataa hin qabnes yookin hin beekne waayee kanaa kaafnee itti ni haasofna. kana keessatti altokko tokko nama biratti balaaleffatamuufi jibbamuun ni jira.

Waliin dhuguun immoo darbee darbee bakka namoonni hin baayyannetti sadi'iifi Afur taanee mana dhugaatiitti waliin bashannanna. Keessattuu waan guyyaa nagaha taanee dubbachuun nu rakkisuu gaafa sana miira machaa'inaatin sodaa malee dubbanna... waliin dhuguun garuu namoota muraasaan wal arganna waan tayeef carraan akka jimaa qaamuu walitti nama fidu hin jiru.

Caraan inni biraa immoo facebook (fuulbarruu) dha. Hawaasni Lammii/Zeegaa tahee miidiyaa hawaasummaa kan fayyadamnu naannoo Jimmaa keessatti irra caalaan Facebook dha. Nama haaraa baruufis haa tahu yeroo dabarfachuuf facebook tu gahee guddaa qaba. Fuulbarru sobaa (Fake account) dhaan walbaruuniifi suuta suuta bilbila dhimma kanaaf namni kamuu qopheeffateen waliin haasahuudhaan bakkaafi guyyaadhaan wal beellamuun wal arganna. Yeroo ammaa kana keessattuu facebook dhaan ala telegiraamiidhaanis hariiroon hawaasummaa ni uumama. Haa tahu malee hagas mara miti. Keessattuu an kan na ajaayibu hiriyoota koon Asoosama David Abraham barreessuufi maxxansu dubbisaa jedheen yoon kennuuf barreeffama hangana dheeratu dubbisuu hin barbaadu jechuun yeroo itti natti dubbatantu jira. An gama kootiin barreeffamoota heddu nan dubbisa. Barreeffamoota David Abrahamis hedduun dinqisiifadha.

Inni biraa immoo jireenya hawaasumma koo hiriyoota zeegaa/lammii hin taane waliin qabu ilaalata. Anaafuu altokko tokko gaaffii natti taha Hiriyoota koo fedha jaalala saala walfakkaata hin qabnee wajjin haasaan nuti bakka hojiittis haa tahu yeroo jimaa qaamnu dubbannu waayeen siyaasaa,diinagdeefi hawaasummaa akkuma jirutti tahee namootan baayyee jaalladhu yoo

xiqqaate waggoota 10 oliif hiriyummaan jiraanne nama sadii suuta suuta akkan jaallataa saala walfakkaataa tahe itti himeera.

Isaan keessaa namni tokko mana rifeensa waan qabuuf maamila isaati. Isatu rifeensakoo naa sirreessa. Baayyee na jaallatu, nama kamuu caala jireenya hawaasummaa waliin jiraanna. Isaan sadanuu qoba qobaattin duuka haasaya. Akkan isa tokkotti himu inni tokko hin beeku kanaaf immoo yeroon isaan faana dubbadhu baayyeen gammada. Isaanis jalqabarratti xiqqoo fudhachuuf isaan rakkisus qabatamaan barreeffamoota PDF dhaan bu'an kan David Abraham seenessu sana kenneefii jennaan baayyeesaa dubbisaniiru. Yoo osoo na hin argin torban gahan gammachuu hin argatan keessattuu, inni tokko seenessoo maajin (ማጅን) jedhamuuf David barreessaa ture jala buhee hordofaa ture. Waan irra gahes natti hima.

Kana jechuunkoo namoonni kun marti maatii horataniiru. Iccitiikoo mara tahuu baatus akkan zeegaa tahe itti himeera. Jarris amananii fudhataniiru. iccitiikoo dabarsanii eenyuttuu akka hin kennine nan amana. Kun akkana tahee osoo jiruu tokko tokko immoo uffannaafi akkaataa keerraa kahee sishakka. “Maaliif hin fuudhu? Qaamasaatu hin dhaabbatuuf “ jedhani!, “Qaama saalaa lama qaba” jedhanii dudduubatti dhoksanii odeessuunis darbee darbee ni mullata!. Ani jaalallee qaba akka jedhamuufis baayyee na gammachiisuu baatus dubartii wajjin saalqunnamtii raawwataa tureera. Sirriittan saalqunamtii waliin raawadhas tures. Gaaffiin gaa'ilaa ishee biraa dhufnaan achumaan dhaabuufan dirqame!

Hawaasa keessa jiraannu keessatti rakkinootaafi gufuuwwan mudatan mara moo'atanii darbuuf dirqama

cimuufi Gamtaa ykn hawaasa jaallattoota saala walfakkaataa bakka jirutti cimsaa deemuutufurmaata ta'a. Kanaaf immoo obsa qabaachuu,Wal danda'uufi walgorfataa fuulduratti tarkaanfachuutu nurraa eegama.

Jaalalli saala hin qabu!

# በመጀመሪያ ቃል...

## ቦቼ X ዶድ (ቦድ)

(አንተ/እሱ)

በተደጋጋሚ የሰልክ ጥሪ እንዳገኘው ከጠየቀኝና የዴቲንግ አፕ ላይ ከተዋወቅኩት አንድ ሰው ጋር የሆነ ቦታ ላይ ተቀምጠን ወግ ቢጤ ጀመርን። በወሬ ወሬ እኔ በምንኖርበት አካባቢ ስላለው የእኛ ማህበረሰብ ተነስቶ “እከሌ የሚባለውን ሆቴል ታውቀዋለህ?” አለኝ።

“አዎ በጣም እንጂ! ለመጀመሪያ ጊዜ ሰው እንዳገኝ የተቀጣጠርኩት እዛ ነበር” አልኩት።

“እዛ’ማ እኮ በጣም ይበዛሉ” ብሎኝ ሳቀ።

ሳቁ ፊቴ ላይ የነበረችውን ትንሽዬ ፈገግታ ስታጠፋውና አንድ ሃሳብ እእምሮዬ ውስጥ ውልብ ሲል አንድ ሆነ።

ይህ ሰው “ይበዛሉ” ሲል ምን ማለቱ ነው?

እሱ ማን ነዉ?

በዚህን ያህል ጉትጎታ ለፍቅር ቀጠሮ ያገኘሁት ሰው ራሱን ከእኔ እና እኔን መሰል ከሆነው ማኅበረሰብ ለይቶ “እነሱ” በማለት የሚናገረው አውቆ ይሆን ባለማወቅ? ብዙ ሃሳቦች አንጎሌ ውስጥ ሮጡ።

እንደ ሰው “እሱ” እና “እኔ” መሃል ብዙ የተለያየ ነገር እንዳለ ግልጽ ነው። ነገር ግን በፆታዊ-ተማርኮ ዝንባሌያችን አይደለም። ይህ ልዩነት ባለመኖሩ መሰለኝ አውርተን የተገናኘነው።

“እነሱ” እና “እኛ የሚል አንድምታ”፣ ለእኔ እራሴን ለተቀበልኩት ደግሞ “እናንተ” እና “እኔ” የሚል እስተሳሰብ በእኛ መሃልም እንዳለ ያሳየኝ ብቸኛው አግላይ ቃል “ይባዛሉ” የሚለው ነበር።

እሱ በጊዜው አውቆትም ይሁን ሳያውቀው ይህን ቃል ተጠቅሟል። በእኔ አእምሮ ውስጥ ግን ከቃሉ የተነሳ በጣም ብዙ ነገር ስለ ግለሰቡ

ተገልጧል። ብቻ እንደ መነሻ ይህን ያህል ካልኩ ዛሬ በዚህ ጽሑፌ "ጀማው ቃላት አጠቃቀም ላይ እንዴት ነው?" በሚል አርዕስት የግል የሆነ ምልከታዬን አስቀምጣለሁ።

እነሆ እኔ ከዚህ ገጠመኜ በኋላ የቃላት አጠቃቀማችንን አስቤ ይገርመኝ ጀምሯል ።በግሌ የቃላት ኃይል ገና የገባን አልመሰለኝም። ገብቶንም ይሁን ሳይገባን ቃላትን ተጠቅመን አንዱን ከፍ አንዱን ደግሞ ዝቅ እናደርጋለን። ቃላት አጠቃቀማችን አቃፊ እና አግላይ አስተሳሰብ እንዳለን እንደሚያሳብቅብን ስንቶቻችን እናውቅ ኖሯል? ወይም በሌሎች ላይ ምን ያህል ተጽእኖ እንደሚፈጥር እና የባህሪ ለውጥ ብሎም እሳቤን እና ማንነትን ለመጻረር አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ስንቶቻችን ተገንዝበናል? ጎበዝ ልብ በል አበው እንዲሉ 'ቃል ይገድላል፣ ቃል ያድናል'።

ቋንቋ ሃሳብን ትርጉም ባለው መልኩ የማስተላለፊያ ስርዓት ነው። ቋንቋ ምልክት፣ ንግግር ወይም ጽሑፍ ሊሆን ይችላል። ቃላት ሃሳባችንን በንግግር የምንገልጽባቸው የቋንቋ ንዑስ አካላት ናቸው። ለብቻቸው ወይም ተቀናጅተው ከሌሎች ሰዎች ጋር ለመግባባት መሳሪያ ይሆኑናል። በቃላት ፍላጎታችንን፣ ሃሳባችንን ፣ አመለካከታችንን አውቀን ድምጽ አውጥተን ወይም በፅሁፍ አማካኝነት እንገልጻለን።

አንድ አዋቂ ሰው በአማካኝ ከ15,000 እስከ 20,000 ቃላትን በቀን ውስጥ ይጠቀማል። ይህ ማለት አውቀነውም ይሁን ሳናውቀው በቀን ውስጥ በብዙ አጋጣሚዎች በሺዎች ቃላት ሺ'ዎች ጊዜያት እኛነታችንን ለሌሎች ሰዎች እንገልጻለን ማለት ነው። አንድ ሰው ጥሩ አድማጭ እና አስተዋይ ከሆነ በቃላችን ብቻ ብዙ ነገሮችን ስለ እኛ ማወቅ ይችላል ። ልብ ማለት ያለብን ቃላት ሂያጅም ናቸው። የእኛ ቃላት ከእኛ አንዴ ከወጡ በፍጹም አይመለሱም ይልቁኑም እንደ ይዘታቸውና ጉልበታቸው ቤተሰባችንን፣ ጓደኞቻችንን ፣ ማህበረሰብን ብሎም ሀገርን አልፈው ሊያፈርሱ፣ ሊሰሩ፣ ሊያፋቅሩ፣ ሊያጋድሉ፣ ሊጥሉ ወይም ሊያነሱ የት ድረስ እንደሆነ እኛ ባናውቀውም ወደ ፊት ይሄዳሉ።

ለምሳሌ አንድ አባት በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ሴት ልጁን "የእኔ ልጅ እኮ ወንድ ናት" በማለት አድናቆቱን ሊገልጽ ይችላል። ይህ አባት ታዲያ እንስታዊ ተፈጥሮዋን የተቀበለች ሴት ልጁን ጾታዊ ማንነት ክዶታል። ልጁን እንደ ሴት ተቀብሎ ከማበረታታት እና ከማድነቅ ይልቅ የወንድን

ጾታዊ ማንነት አስድግፎ በስንኩል አእምሮ የጎደለ አድናቆት ጾታዊ ማንነቷን እንዳላከበረ በቃላት አጠቃቀሙ አሳይቷል። ይህ አባት ስለ ሴት ያለውን አመለካከትና አስተሳሰብ ለማወቅ የትም ሳንሄድ በሴት ልጁ ላይ በተጠቀመው አንድ ቃል ብቻ ተመልክተናል። ቃል ሰዎችን ይገልጣል።

ሴትነት ህብረተሰባችን ውስጥ አሁን ድረስ ደካማ የመሆን እና ያለመቻል ምስል አለው። የዚህ ምስል ተጽእኖ ታዲያ እልፎ በእኛ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ማህበረሰብ ውስጥም በደንብ ይታያል።

የተራክቦ ሚናው (Role) ቶፕ የሆነን ሰው ሁሉ ፆታዊ-ማንነቱ ወንድ ነው በማለት ሚናው ቦተም የሆነን ሰው ደግሞ እንደ ሴት የመቁጠር ወይም የመውሰድ ይህን የተሳሳተ መረዳት በመያዝ እና ህብረተሰቡ ጋር ያለውን ሴት ደካማ እና እቅመ ቢስ ናት የሚል ስንኩል አስተሳሰብ በመጋራት ለመናቅ፣ ለማጥላላት እና ለማዋረድ “እንቺ” የሚል ቃል መጠቀም በዚህም ምክንያት ስድብ እና ዱላ መማዘዝ ሁሉ እንዳለ ታዝበናል።

ሚና የሆነው ነገር ሳይሆን የምናደርገው ነገር ነው። ይህ ምን ማለት ነው? ሚና የፆታ-ማንነታችን ሳይሆን በተራክቦ ጊዜ ልንከውነው የወደድነው ድርጊት ነው። ለዚህም ነው ሚና በእኛ የተራክቦ ስርዓት ውስጥ የተለያየ እና ተለዋዋጭ ሆኖ ያለው። ቶፕ የሆነ ሰው ሁሉ ቶፕ ሆኖ ላይዘልቅ ይችላል። ቦተም የሆነውም እንዲያው። ሌላው ምንም አይነት የተራክቦ ስጋ ወይም ሚና የሌለበት አይነት ግንኙነት ደግሞ አለ። ስለዚህ ይህ አሳብ ከጅምሩ በፆታ እኩልነት ላይ እንደ ሀገር ያለንን የተዛባ አመለካከት ነው ለእኔ በይበልጥ የሚያሳየኝ። የአጠቃላይ ህብረተሰቡ የፆታ እሳቤ ተጽእኖ የወሲብ ሚና እንስታዊ እና ተባእታዊነትን ፈጥሯል።

እኔ ለምሳሌ የተራክቦ ድርጊቶች ላይ ሚናዬ ቦተም ነው። እንስታዊ እና ተባእታዊ ባህሪያቶች እኔን ጨምሮ በሁሉም የሰው ልጆች ውስጥ እንዳሉ አምናለሁ። ከአብላጫው ባህሪያቶቼ እና ከሚሰማኝ ውስጣዊ ስሜት ፆታዊ-ማንነቴ ወንድ ነው ብዬ ተቀብያለሁ። ይህ ምን ማለት ነው ወንድነቴ የጾታዊ ማንነቴ (ውስጣዊ የፆታ ስሜቴ መገለጫ እንጂ የወሲባዊ ግንኙነት ባህሪዬን) ሚናዬ ወይም ዝንባሌ አልያም ፍላጎቴ ማሳያ አይደለም ማለት ነው። በተመሳሳይ በሴት የፆታዊ መጠሪያ የሚጠቀሙ (የፆታዊ ማንነታቸው ሴት የሆኑ) ትራንስ ጀንደሮችም የተራክቦ ሚናቸው ቶፕ አልያም ቨርሳታይል አልያም ቦተም በመሆኑ፣

ሚናቸው ወይም የወሲብ ፍላጎታቸው (ተማርኳቸው) ፆታዊ ማንነታቸውን እያሳይም። እንዲሁም የወሲባዊ ፍላጎት፣ ባህሪ እና ፆታዊ ማንነትን ሊመድብ አይችልም።

የፆታዊ-ማንነቴ መገለጫ ተውላጠ-ስም "አንተ" እና "እሱ" ሲሆን በግሌ እንደ ወንድ የምወደውን አለባበስ እና የጸጉር ቁርጥ እንዲሁም ስታይል እጠቀማለው። ይህ ሆኖ ሲያበቃ ገና ለገና ቦተም ነኝ ስላልኩ ብቻ ሆን ተብሎ ፆታዊ-ማንነቴን ባለማክበርና ማንነቴን በሚጻረር መልኩ እኔን "አንቺ" ብሎ ማናገር ለእኔ ጥላቻ ነው።

ይህ ብቻ አይደለም የሁለቱም ፆታዎች አፍቃሪ የሆኑ ሰዎች ደግሞ አሉ። ሌላ ምሳሌ ልጨምር የፆታዊ-ማንነቱ ወንድ የሆነ አንድ የሁለቱም ፆታ አፍቃሪ ወዳጅ ነበረኝ። ይህ ሰው ታዲያ የተራክቦ ሚናው ቦተም ነው። ነገር ግን ከሴት የወሲብ አጋሩ ጋር ሲወጣ ዘልማዳዊ በሆነ መልኩ ወሲብ ይፈጽማል። ታዲያ ይህን ሰው እንደኛ አባባል በተራክቦ ሚናው ተጠቅመን ፆታዊ ማንነቱን ምን ብለን ልንጠራው ነው?

የተራክቦ ሚናን ካነሳው አይቀር ሌላ ደግሞ ሚናን በተመለከተ የምንለው የተሳሳተ አመለካከታችንን የሚያሳብቅ የቃል አጠቃቀም አለ "ቶፕ ከቦተም ይሻላል" ይላል። ነገሩን ለንጽጽርነት ያበቃው ደግሞ ከብዙዎቹ አንዱ ቶፕ ከሴት ጋር መዋሰብ ይችላል ቦተም ግን ወሲብ ከሴት ጋር ለመፈጸም አይቆምለትም የሚል ነው። ይህ ፆታዊ-ተማርኮን ካለመረዳት ወንድ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎችን በተለይም የቦተም ሚናን የሚወስዱትን እንደ ስንፈተ ወሲብ ያሉ የወሲብ ችግሮች እንዳሉባቸው የማሰብ ችግር ነው። ይህ አይነቱ አስተሳሰብ ከዜጋው ማኅበረሰብ ውጪ ያለው ህብረተሰብ በአብዛኛው ለማለት እችላለሁ ሁሉም ወንድ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ላይ የሚያወራው ሃሳብ ነው። እኛ መሃል ደግሞ በቶፕ እና ቦተም ሚናዎች አንዳንዴ ደግሞ ባይሴክሺዋል (የሁለቱም ፆታ አፍቃሪ) በሆኑ ወንዶች እና የወንድ ፆታ ብቻ አፍቃሪ በሆኑ ሰዎች መሃል ለንጽጽር ይቀርባል።

ህክምናው ስለ ስንፈተ ወሲብ የሚለውን ሃሳብ እንዳለ እዚህ አንስቼ ለማውራት ቦታው አይፈቅድም ነገር ግን በአጠቃላይ ሃሳቡን ለማየት ያህል ስንፈተ ወሲብ ወንዶችን የሚያጠቃ በወሲብ ወቅት የብልት አለመቆም ችግር ነው። ይህ ችግር ዓለም ላይ ያሉ ወንዶችን ሁሉ የሚፈተኑበት ችግር ሲሆን ተለይቶ ከእኛ ማህበረሰብ ጋር መያያዙ እንደ

ተለመደው እኛን ጥላሸት ለመቀባት ነው። ችግሩ በተለያዩ መንስኤዎች የሚከሰት ሲሆን እንደ መንስኤው ሁሉ የሕክምና መፍትሄ ይሰጣል።

ሌላው የፆታዊ ተማርኮ ስሜት እና ፍላጎት የወሲብ አካላቶቻችንን ለማዘዝ ዋነኛ ነገር ነው። የትኛውም ወንድ ከሴትም ይሁን ከወንድ ጋር የወሲብ ድርጊት ለመፈጸም ሲዘጋጅ ስሜት ከሌለው አካሉ ሊታዘዝ እና ድርጊቱን እንደተፈለገው ሊፈጽም አይችልም። ለምሳሌ እኔ ሴት ልጅ ምንም ነገር ብታደርግ እና ምንም ያህል ብትቆነጅ ስሜቴን ለወሲብ አታነሳሳውም። ስለዚህ ስሜቱ ሳይሰማኝ እና ድርጊቱን እንድፈጽም የሚያነሳሳ መልእክት ለብልቴ ሳይደርሰው እንዴት ይቆማል? በተቃራኒው ምንም ነገር ሳያደርገኝ ወንድ ልጅ አይቶኛ ወይም አናግሮኝ ብቻ ብልቴ ሊቆም ይችላል ። ይህ ታዲያ የብልቴ ችግር ነው ማለት እንችላለን? ብልቴ ወንድ ጋር ከቆመ እኮ ብልቴ ይሰራል ማለት ነው ችግሩ ያለው የተማርኮ ፍላጎቴ ላይ ነው ማለት ነው።

ችግሩ ስለ ችግር አለብኝ እያልኩ ሳይሆን ሴት ልጅ ተማርኮዬ እንዳልሆነች ለመግለጽ ነው። ይህ የእኔ ሃሳብ ለቶፑም ይሰራል። አንድ ሰው ቶፕ ስለሆነ ብቻ ሴት ይወዳል ወይም ከሴት ጋር ወሲብ ለመፈጸም ይሆንለታል ማለት አይደለም። ከሴት ጋር ወሲብ ለመፈጸም ለሴት ፆታ-ተማርኮ አስፈላጊ ነው። መርሳት የሌለብን አንድ ነገር አንድ ሰው ለወንድም ለሴትም ፆታዎች ተማርኮ ሊኖረው ይችላል ይህም ነው ‘’ባይ’’ ወይም ‘’ሁለት-ወዳድ’’ የሚያሰብለው።

ሌላው ሚናቸው ቦተም የሆኑ የሁለቱም ጾታ አፍቃሪዎች አሉ። ከላይ ስለ አንድ ወዳጄ ያጫወትኳችሁን አትርሱ። ሌሎችም ከወንድ ጋር ቦተም ሆነው ተራክቦ ማድረግን የሚወዱ እና ከሴት ጋር ሲሆኑ ደግሞ ሴት ልጅን በፈለገችው ልክ በወሲብ የሚያስደስቱ ቦተም ሚና ያላቸው አሉ። እንደ አጠቃላይ ግን የአንድን ሰው የተማርኮ ስሜት እና ፍላጎትን ከእኛ የተዛባ እና ልክ ያልሆነ የፆታ ምልከታዎች አንጻር በመውሰድ ንጽጽር መሻል አለመሻል ውስጥ መግባት አግባብ አይደለም። ሲጀመር ይህን ንጽጽር ለማድረግ ማሰብ ሃሳቡ እንደ ሃሳብ ትክክል አይደለም።

እነዚህን እና መሰል ስንኩል የቃል አጠቃቀሞችን በሀገራች መመልከት የተለመደ ነገር ሲሆን፤ በአመለካከታችን ደግሞ እንደ አካባብቢ እያለ ህብረተሰብ ብሎም እንደ ሃገር ያለንበትን ደረጃ ለዓለም ሕዝብ ያሳያል። ዛሬ በእርግጥም በዚህ አጭር ጽሑፍ ለማውራት የፈለኩት

እንደ ተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ያለንበትን የቃል አጠቃቀም ችግር በወፍ በረር ለመቃኘት ያህል ነው።

እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የተፈጠርንበት ቤተሰብ እና ያደግንበት ማህበረሰብ የቃል አጠቃቀማችን ላይ የሚኖረው ተጽእኖ ግልጽ ነው። ነገር ግን ነፍስ ካወቅን ብሎም በሂደት ከትምህርት ያነሳናቸው ወይም ደግሞ የጣልናቸው የተሳሳቱ አመለካከቶች እንደመኖራቸው ሁሉ ቃላት ላይ ያለን አጠቃቀም ደግሞ ሌሎች ሰዎችን የሚያንቋሽሽ፣ የሚንቅ እና የሚያገል እንዳይሆን ሚዛናዊ ሆነን ራሳችንን በመፈተሽ ማረም ይጠቅማል።

ሰዎች የሰርዓተ-ፆታ ማንነታቻውን ወይም መገለጫቸውን በፍላጎታቸው፤ ምቾት በሚሰጣቸው ሊጠሩ'በት ወይም ራሳቸውን ሊገለጹበት ይገባል። ይህም ሊከበርላቸው የግድ ነው።

ተፈጥሯዊ የፆታ ማንነት መገለጫ የሆኑ ቃላትን ከመራቢያ አካል ጋር ወይም ከፆታዊ ሚና ጋር እያይዞ የሰውን ልጅ ክብር ለማዋረድ፣ ለማጥላላት እና ለመንቀፍ መሞከር አግባብ አይደለም። እንዲያውም በሕግ የሚያስጠይቅ እና የሚያስቀጣ ወንጀል ነው።

እሁን ድረስ ልክ ባልሆነ የቃል አጠቃቀም ተፈጥሯዊ የሰረዓተ-ፆታ ማንነቴን በመካድ ያለ ምርጫዬ እና ፍላጎቴ ያልተሰማኝን ሴትነት በግድ ለመጫን "አንቺ" በማለት የሚያወሩኝ ሰዎች መጥፎ ስሜት እንዲሰማኝ ያደርጉኛል። የሆንኩትን ወይም ያለሁትን እኔን እንድጠራጠር እና ሆነ ብለው እኔን ለማዋረድ ወይም ለማሳነስ ቃሉን የተጠቀሙት እንደሆነ ይሰማኛል። ወንድ መውደዴ ወይም በሕብረተሰብ ውል የሴት የተባሉ ሚናዎችን ወድጄ ማከናወኔ "አንቺ" ሊያስብለኝ አይገባም።

አንድ እዚህ ላይ እንድታውቁልኝ የምፈልገው ነገር "አንቺ" ወይም "አንተ" ተብሎ መጠራት ቃሉ ላይ ምንም አይነት ችግር የለውም። ወንድም ይሁን ሴት ወይም ከሁለቱም ያልሆነ የፆታ መገለጫ ያለው ሰው እኩል ነው። ዋናው ግን የትኛውን ተውላጠ-ስም መጠቀም እንዳለብኝ የመምረጥ ሃላፊነቱ የእኔ ነው። ሰዎች እኔ ወንድ ልሁን ሴት አልያም ሌላ ምንም የሚያውቁት ነገር የለም። ምክንያቱም ይህ የእኔ የራሴ ግንዛቤ ወይም የራስ ተጨባጭ ስሜት ነው። ስለዚህ እኔ ራሴን ለመግለጽ እና ለማስተዋወቅ የሚጠቅመኝን ምቾት የሚሰጠኝንና የሚስማማኝን ቃል

በመጠቀም ብቻ ሌሎች ሰዎች እኔን ማናገር ወይም ስለ እኔ ለማውራት መጠቀም ይኖርባቸዋል።

አሁንም ድረስ ሀገራችን ኢትዮጵያ ላይ ፆታዊ-ማንነት፣ ፆታ እና ፆታዊ ሚና ላይ ያለው መረዳት እጅግ ገና ነው። ይህን በተመለከተ የሚሰጥ ትምህርት እና ግንዛቤ ማስጨበጫ ባለመኖሩ አንድን ሰው ከአለባበሱ ወይም ከምርጫዎቹ ብቻ በመነሳት እና በመገመት ከተፈጥሮዊ የፆታ-ማንነቱ ባፈነገጠ መልኩ በዘልማድ ብቻ "አንተ" ወይም "አንቺ" በማለት ሰዎችን እናወራለን። ይህ "የሰዎችን ጾታዊ-ማንነትን" እኔ አውቅላችዋለው ማለት መሆኑን ግን ስንቶቻችን አውቀን ይሆን?

በተሳሳተ የፆታ ማንነት መገለጽ በተሳሳተ ስም ከመጠራት በላይ ስሜት እንደሚጎዳ ስንቶቻችን ልብ ብለናል? አንድ ሰው የሰርዓተ-ፆታ ስሜቱን በተመለከተ ራሱ እና ራሱ ብቻ ነው የሚያውቀው። ይህን የሰርዓተ-ጾታ ስሜቱን ይገልጽልኛል የሚለውን ቃል የመምረጥ ድርሻው ደግሞ የግለሰቡ ብቻ ነው።

ይህ ብቻ ሳይሆን ሌሎች የምንግባባቸው ቃላት ግለሰብን ብቻ ሳይሆን እንደ ህብረተሰብ በጠቅላላ አግላይ አስተሳሰብን ለማሳየት መሳሪያ ሲሆኑ እና ሰዎችን ሲፈርጁ በዚህም እኩይ ባህሪያትን ማሳያ ተደርገው ሲወሰዱ ይታያሉ።

ለምሳሌ በእኛ ማህበረሰብ ውስጥ በብዛት "ደሞ ለዜጋ" "ከዜጋ ምን ይጠበቃል" የመሳሰሉ ልክ ያልሆኑ ቃላትን በብዛት እንሰማለን። እነዚህ ቃላት በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የምንጠቀማቸው ትክክል ያልሆኑ አገላለጾች ናቸው።

ዜግነት የአንድ ሰው የፆታዊ-ተማርኮ ማንነት ብቻ ነው። አንድ ሰው በተፈጥሮ ያገኘው እና ከተወለደ በኋላ ከቤተሰቡ ወይም ከኖረበት አካባቢ የሚያገኘው የተለያየ የማንነት መገለጫዎች ወይም ማንነት ሊኖረው ይችላል። ለምሳሌ ፆታዊ-ማንነት፣ ዘር፣ ብሔር፣ ጎሳ፣ ሐይማኖት፣ ስራ፣ የፖለቲካ ምርጫ___ወዘተ። ዜግነት የአንድ ሰው ሙሉ ማንነት መገለጫ አይደለም። አንድ ሰው ዜጋ በመሆኑ ብቻ ሌላ የሆነውን ማንነት ሁሉ መጨፍለቅ አላዋቂነት ወይም ግብዝነት ነው።

ሌላው ደግሞ አንድ ሰው በተፈጥሮ ግራኝ ነው ማለት እና ይህ ሰው

ሌባ፣ ውሸታም ወይም እኩይ ባህሪ አለው ማለት ግራኝ የሆኑ ሰዎች ሁሉ ልክ እንደዚህ ግራኝ ሰው እኩይ ባህሪ አላቸው ማለት አይደለም።

ሌላው በጽሑፌ መጀመሪያ ላይ ያልኩት ቃል ነው። “እነሱ”፤ “እሉ” ወይም “ናቸው” የሚሉ አግላይ ስሜት የሚፈጥሩ ራሳችን ይህ ማንነት እያለን ግን ማንነቱን የሚጋሩ ቤተሰቦችን ለማሳጣት የምንጠቀምባቸው ቃላት።

“ይህማ የእነሱ ሰፈር ነው”
“እዚህ አካባቢማ ብዙ እሉ”
“ኧረ እነሱ እንዲህ ናቸው” ወ.ዘ.ተ.

ይህን የሚለው እራሱ ዜጋው መሆኑ ነው እንግዲህ የቃል አጠቃቀሙን ስህተት ወይም ለገዛ ራሱ ያለውን የተሳሳተ መረዳት ያሳያል የምለው። “እነሱ” “እሉ” “ናቸው” አንዳንዴ ስናወራ እራሳችንን “እኔስ እዚህ ገጽ ላይ የት ጋር ነኝ?” ወይም “ይህን ቃል ስጠቀም የእኔን የማንነት መገለጫ ያጠቃልላል ወይስ አይመለከተኝም?” ብለን መጠየቅ ያስፈልገናል። ምክንያቱም ያሰተዛዝበናል። ያራርቀናል።

ሌላ ደግሞ አለችን “እዚህ ላይፍ (እዚህ ህይወት)”
‘እዚህ ላይፍ’ ምን ማለት ይሆን? ስንት ላይፍ ይሆን ያለን? “እኔ” እና “ላይፌ” የምንለው ምንድነው? ይህ በብዛት ራስን ካለመቀበል እና ራስን ከመጥላት የሚነገር ቃል ይመስለኛል።

በመጨረሻ የቃል አጠቃቀማችንን በዘላቂ መልኩ ለማረም ስለምናወራው ነገር የሚኖረን እውቀት እና መረዳትም የራሱ ድርሻ አለው። በዚህ አጋጣሚ ሁላችሁም ስለ ፆታ(Sex)፣ ፆታዊ-ማንነት (gender identity)፣ የፆታዊ-ተማርኮ(Sexual identity) እና የተራክቦ ሚና (Sexual role) ይበልጥ በማንበብ መረዳታችሁን ታሰፉ ዘንድ አደራ እላለሁ።

ከዚህ በታች ያለው ታሪክ በመጽሐፉ መግቢያ ላይ በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ተጽፎ የቀረበ ጽሑፍ ነው። የተነሣንበትን ሃሳብ የሚደግፍና ብዙዎች ቢያነቡት የሚማሩበት መሆኑን ስላመንን በአማርኛ ተርጉመን አቅርበነዋል።

የይዘት ማስጠንቀቂያ፦ በዚህ ታሪክ ውስጥ ራስን ስለማጥፋት፣ ልቅ የሆነ የወሲብ ግንኙነት፣ አደንዛዥ ዕፅ እና አልኮሆል መጠጥን አብዝቶ ስለመጠቀም የሚገልፁ ቦታዎች ስላሉ በጥሩ የአይምሮ ጤና ላይ ካልሆኑ ይህን ገፅ ይለፉት።

# ዘማች ልብ

## ውርስ ትርጉም፦ ቦኒቸ ቦና

(አንተ/እሱ)

ክፍል አንድ

የማውቀውን ከማወቄ በፊት፦
እንደ ሴት በመላ የተሞላ፣እንደ ሊቅ የሚያሰብ ደቂቅ፣ ጉዳዩን በእናቱ ሆድ ጨርሶ የወጣ ጠቢብ።

“ፓ....ይሄማ በሽታን ከነዘር ማንዘሩ የሚያጠፋ ዶክተር ነው ሚሆነው።”
“ምን ዶክተር ብቻ አብራሪ ሆኖ አይሮፕላኑን ወደ ሰማይ ያመጥቀዋል እንጂ... እዎ የሚወራረድ አለ? ከምላሴ ፀጉር ይነቀል።”

“ይሄ ልጅ እነ አንስታይንን የሚያስንቅ ሳይንቲስት ሆኖ ሰማችንን ካላሰጠራ!”
እነዚህ የልጅነት ማለዳዬን ከበው፣ የነገ ፍልሚያዬን ተንብየው ያሳደጉኝ በአድናቆትና በአግራሞት የተሞሉ ውብ ቃላቶች ነበሩ። እኔም ታድያ የእነዚህን ቃላቶች ድምፀት በውስጤ ባቃጨለው የተሰፋ ጭላንጭል ተንተርሼ ሩቅ አሳቢ ነበርኩኝ። ለነገ የበላይ ኑሮ የታጨች የልጅነት ልቤም ታላቅነትን የናፈቀ ትርታዋ ልዩ ነበር።

ሌንጮ ሸገር እባላለሁ። እንዲት ምዕራብ ኦሮሚያ በምትገኝ ከተማ ነው የተወለድኩት። ቤተሰቦቼ የመንግስት ሰራተኛ ሲሆኑ፣ ሶስት ወንድሞችና ሁለት እህቶች አሉኝ። የላዩ የጥበብ አባት ፈጣሪ ውሃን ወደ ስጋ ቀይሮ በእናቴ ማህፀን ውስጥ እኔን ሲፈጥረኝ እንደ ወንድምና እህቶቼ መልኬን ኩሎ ቁመናዬን አሳምሮ አልነበረም። ቢሆንም ሙሉ ሰው፣ የደስደስ እና የደም ግባት ያልጎደለኝ ነኝ። እንዲሁም በምዕተ ዓመት አንዴ የሚገኝ ለእውቀት ምቹ በሆነ መልኩ ተቀርጾ የተዘጋጀ ስል የሆነ የልጅነት አዕምሮ ሰቶኛል። ለቤተሰቤ መኩራሪያና መመኪያ፣ ለጎረቤት ልጆቻቸውን የሚገሰፁበት ጥሩ ምሳሌ፣ በእምነት ቤት በቸርነቱ ቀብቶ የፈጠረኝ ብሩክ፣ በትምህርት ቤቴ ትልቅ ተስፋ የተጣለበት የነገ ባላደራና ሃገር ተረካቢ ሌንጮ።

እንግዲህ ከላይ ከተጠቀሱት እውነታዎች የጠዋቱን የህይወቴን ምዕራፍ ከማሳመር አልፈው ለትልቅ ስልጣን ወይም ዙፋን የታጨውን የንጉሱን ልጅ ልዑሉን አድርገውኝ ነበር። በተሻለ ሥነልቦና እና ሥነዓምሮ እንዳድግ የሚደረግልኝ እንክብካቤ እንዲሁም በመንፈሳዊ ህይወቴና በአዕምሮ እድገቴ ላይ የሚደረግልኝ ድጋፍ እጅግ ልዩና ድንቅ ነበር። እውነቱን ለመናገር ከማስደነቅም አልፎ ሸክም ነበር ማለት ይቻላል። እንደውም በእያንዳንዱ እርምጃዬና ድርጊቴ ላይ ይደረግብኝ የነበረው ክትትል የባርነት ስሜት እስኪሰማኝ ድረስ ያስጨንቀኝ ነበር። የኔን ህይወት መቆጣጠር ለቤተሰቦቼ የሙሉ ግዜ ስራቸው ነበር። ከመከታተልም አልፈዉ ማንን ጓደኛ ማድረግ እንዳለብኝ እስከ መወሰን ሳይቀር የኔን ህይወት ተክተው ይኖሩልኝ ነበር።

የትኛዉም በኔ ህይወት የሚካሄድ ጉዳይ ከነሱ እይታ የተሰወረ አልነበረም። የውጪው ኑሮዬ ይቅርና ሙሉ እኔነቴን፤ የጡንቻዬ እድገትና የደም ዝዉዉሬ ሁሉ ሳይቀር ይከታተሉልኝ ነበር። የኔን ህይወት አቅጣጫ እናውቃለን ብለው ያምናሉ ፤ ጭራሽ ይኩራሩበትም ነበር። ዳሩ ግን ለከፍታ ያጩትን ልጃቸውን እናውቀዋለን ብለው ቢያስቡም እኔ ለወንድ ልጅ ወይም ለዘማች ያለኝን ልዩ ፍቅርና በልዩ ማህደር ከልቤ ጓዳ ቆልፌ ያስቀመጥኩትን ሚስጥሬን ለማወቅ ፀጋውን አልታደሉም ነበር። እውነቱን ለመናገር እንኳን እነሱ ቀርተው እኔው የስሜቱ ባለቤት በወቅቱ የዚህን ስሜት ምንነት በቅጡ ለመረዳት አልታደልኩም ነበር።

ዘማች የወንድነትን ልክ ከወታደር አባቱ የወረሰ የትምህርት ቤታችን እንደልቡ እና ጉልቤ ነዉ፤፣ ትእቢት ልቡን የወጠረው፣ ህይወቱ እጅ እጅ የሚልና ትምህርት ከቀልቡ የማይገባ ድፍን ቅል ነበር። የትምህርት ዓለም በአንድ ላይ ያመጣን ቀን ነበር ዘማችን ያየሁት። በዚሁ ግዜ ነበር የሚያደናግርና ግራ የሚያጋባ ስሜት የተሰማኝ። ዓይኔም ቀልቤም ዘማች ላይ እንደ ሙጫ ተጣበቁ። ከዚህ ቀን ጀምሮ ዘማችን አይቼ መጥገብ አልቻልኩም። አልችልም። ዛሬ ተለያይተን ነገ ደግሜ እስካገኘው ድረስ ዓመታት ያለፉ ይመስለኛል። ካጠገቤ እያለ ሳይቀር ይናፍቀኛል።

ዘማችን ጓደኛ ከማድረግ ግን የዱር እንሰሳን ማላመድ ይቀል ነበር። ለዘማች ህይወት ማለት ከትምህርት በኋላ ከማን ጋር ትሪዲዮ ገጥሜ ጉልበቴን ላሰመስክር ማለት ነዉ እንጂ ጓደኝነት አልነበረም። ትሪዲዮ ማለት የትምህርት ቤታችን የትግል ፕሮግራም ነው።
ዘማችን እንደ ልቤ ማቅረብ አለመቻሌ ደግሞ ለሱ ያለኝን ስሜት እጥፍ አደረገው። እንደ መታደል ሆኖ ግን እኔ በትምህርት ጎበዝ መሆኔና እሱ ከትምህርት ጋር ሆድና ጀርባ መሆኑ ነገሩን አቀለለው። የቤት ስራውን ከመስራት እስከ ፈተና ማስኮረጅ ድረስ ጉቦ ከፈልኩና ከዝምድናው እልፍኝ ተቀላቀልኩ። ከአንደኛ እስከ አምስተኛ ክፍልም ከመሬት ሰበት በሚልቅ ሃይልና

ሌኔም በማይገባኝ ስሜት ከዘማች ጋር ተጣበኩ። ጓደኝነታችን ለሱ ብዙ ትርጉም ያለው ባይሆንም፤ በትምህርት እኔ ላይ መደገፉ ግን አምስት ዓመታትን አብሬዉ እንዳሳልፍ ረድቶኛል። ስድስተኛ ክፍል ላይ አባቱ ለስራ ወደ ሌላ ሀገር ስለተቀየሩ ዘማች ድብቁን ፍቅሬን ከነቋጠሮዉ ይዞብኝ ተለየኝ። በነገራችን ላይ ዘማችን ካጠገቤ ማጣት ፤ ማጣትን የተለማመድኩበት የመጀመሪያውና ትልቁ የልጅነቴ ማጣት ነበር።

ስድስተኛ ክፍል ላይ ከጎኔ የተቀመጠውን አዲስ ተማሪ ማቅረብ ትልቅ ጭንቅ ሆነብኝ። ሞሃመድ በዘማች ምትክ አጠገቤ የተቀመጠው ተማሪ ነበር። ከኦሮሞ አባት እና አርመናዊት እናት የተወለደ፤ ቀይ፣ ግንባሩ የሆድ ያህል የሚሰፋ፣ ፋንጋ ከመሆን አልፎ ዓይኖቹ ሊነካኩ ትንሽ ቆዳ የገደባቸዉ፣ ቅላታቸው አጀብ የሚያሰኝ ወፋፍራም ከንፈሮች.... ሞሃመድ! ከሌላ ትምህርት ቤት ተቀይሮ ነበር የመጣው።

ዘማችን በሞሃመድ መተካተና መላመድ አብዝቶ ቢከብደኛም ማሜ ከዘማች በተቃራኒ ጥሩ ፀባይ ያለውና ትምህርት መቻሉ ምክንያት ሆኖ አቀራረበን። አብሮ በማጥናትና ጥያቄ በመጠያየቅ የተጀመረው ጓደኝነታችንም በቅጽበት ተለወጠና ከትምህርት ቤት ተሻግሮ ወደ ውጪ ወጣ። ከኔ ጋር በመቀራረቡና አብሮ በማጥናቱ የማሜ ውጤት መሻሻሉ ደግሞ ቤተሰቦቹንም ጭምር ስላስደሰተ ጓደኝነታችን ከኛ አልፎ በቤተሰቦቻችንም ተቀባይነት አገኘ። ማሜም አብሮኝ አንድ ቤት እስከማደር መብት ያገኘ የመጀመሪያው ጓደኛዬ ሆነ።

ዘማቿ ልቤም ለዘማች ያላትን ስሜት ወደ ማሜ ቀየረችና ለሌላ ድብቅ ፈቅር ሸፈተች።
ስሜቴን በጓደኝነትና በጥናት መጋረጃ ሸፍኜ፤ ተዋኝቶ በማያልቅ የፍቅር ባህር ውስጥ እንደሰጠምኩ መዋኘቴን ተያያዝኩት። ድንቅ የነበሩ ዘጠኛ ወራት አልፈው የስድስተኛ ክፍል ትምህርት ሲጠናቀቅ እኔ እና ማሜ እንደ በቆጂ አትሌቶች ተከታትለን አንደኛ እና ሁለተኛ ሆነን ጨረስን።

አንድ የናፈቆት ክረምት አልፎ መስከረም ጠባ፤ እኔም ብዙ ሰዓታት ከማሜ ጎን እንዳሳልፍ ምክንያት የምትሆነኝን ሰባተኛ ክፍል በጉጉት ጀመርኩ፤፤ እንደ አጋጣሚ ሆኖ ግን ሰባተኛ ክፍልን የጀመርኩት ከብዙ ለውጦችና ተግዳሮቶች ጋር ነበር። የቤተሰቦቼ ትዳር በፍቺ መገባደዱን ተከትሎ የለመድኩት ኑሮ ላይ ቀዳዳዎች መታየት ጀምረዉ ነበር። አባቴ እናቴን ከስድስት ልጆች ጋር ትቶ ሌላ ሚስት ማግባቱ ከፈጠረብኝ ስሜት ላይ ደገሞ ይህ ክስተት የእናቴ የተሰፋ ዓይኖች እኔ ላይ እንዲወድቁ አድርጓል፤፤ ከዝህም አልፎ ትልቅ ቦታ ደርሼ የተሰበረዉን የጎጂችንን ህይወት የመቀየር አደራ በሳር እና በአሞሌ ተጠቅልሎ ተሰጠኝ። ይህ ለኔ ቀላል ጉዳይ አልነበረም፤፤ በሌላ በኩል ደግሞ

እድሜዬን እስታከው የመጡ አዳድስ ስሜቶች ለማሜ የነበረኝን ስሜት ወደ ፍቅር ለውጠዉ እሳት በመዳፌ ይዤ የመዞር ያክል ከብዶኝ ነበር። ያም ሆኖ ግን የእናቴን ተስፋና ቀዬያችንን የመቀየር አደራን እንደ ዝናር ታጥቄ፤ የልብ ቃጠሎ ሆኖ ሁለንተናዬን የወረረውን የማሜን ፍቅር ከልቤ ጓዳ ደብቄ የሰባተኛ ክፍል ትምህርቴን ጀመርኩ።

## ክፍል ሁለት
## መቅሰፍቱን ሸሽት፦

ከቀኑ ወደ አስር ሰዓት ገደማ ነበር። በእድሜ ተቀራራቢ የሆንና ቁጥራችን ከሃያ የማይበልጥ ወንዶች እና ሴቶች በአንድ ትንሽዬ ክፍል ውስጥ ተቀምጠናል። ይህቺ ክፍል ቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ የምትገኝ ስትሆን እዛ የመሰባሰባችን ምክንያት ደግሞ ከልጅነቴ ጀምሬ የምከታተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ፕሮግራም ለመካፈል ነበር።
ይህች ቀን ግን እንደወትሮው ወይም እንደ ሁልግዜው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን ለመከታተል የመጣሁበት አይነት ቀን እንጂ ሙሉ የህይወቴን አቅጣጫ የምትቀይር ቀን ትሆናለች ብዬ አልገመትኩም ነበር። የዕለቱ መምህራችን ነጠላውን አገልድሞ ከትንሿ ክፍል ሲገባ እንደ ወትሮው ሁሉ የክብር ሰላምታ ሰጠን። በመምህሩ መሪነት አጭር ጸሎት ካደረግን በኋላም፤ በዕለቱ የምንማረውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነግሮን ሁላችንም እጃችን ላይ ያለውን ወንጌል ከፈትን።

ኦሪት ዘሌዋዊያን ምዕራፍ 18 ቁጥር 22
ዘፍጥረት ምዕራፍ 13 ቁጥር 12
ዘፍጥረት ምዕራፍ 19 የሰዶምና ገሞራን መቃጠል ይናገራል።

ደነገጠኩ፤፤ ስልፍ ይዘው የተደረደሩትን ፊደላት ማየት እስኪያቅተኝ ድረስ የዐይኔ ብርሃን ከዳኝ። የፊደላቶቹን ስልፍ ጥሼ ከአንዱ እንቀጽ ወደ አንዱ መሻገር እስፈራኝ። በዓይን ውልብታ ቅፅበት የሃጢያተኛነት ስሜት ከእግር ጥፍሬ እስከ ራስ ፀጉሬ ተሰማኝ። እግሮቼ በተቀመጥኩበት ተንቀጠቀጡ፤ ጉልበቴም እዛዉ ከዳኝ።

"የእሳት ዝናብ የሚያዘንብ የእርግማን ዛፍ " መሆኔን የሆነ ዘግናኝ ድምፅ ደጋግሞ አምባረቀብኝ፤፤ እጅግ የከፋ እውሎ ንፋስ በድንገት ተነስቶ የመኖሬን የተሰፋ ኩራዝ ከልቤ እድማስ ሲያጠፋት በብዥታ ታየኝ። ለራሴ እንሼ ታየሁት። በጣም አፈርኩኝ። በጣም ፈራሁ።
በዝህ ላይ ደግሞ መምህራችን የምጠቀማቸዉን ዘግናኝ ቃላትም አንገሸገሹኝ፤፤ ከዚህ በላይ እዛች ጠባብ ክፍል ዉስጥ መቆየትም ሆነ ስሜቴን መቆጣጠር አልቻልኩም። ተፈትልኬ ወጣሁ። እንኳን ክፍሏን የቤተክርስቲያን ደጃፍ

ሳይቀር ለቅቄ እስክወጣ ድረስ ትንፋሼን ሰብስቤ፤ ባለኝ ሃይል ሁሉ ሮጥኩኝ። በዚህች ቅጽበት የፈጣሪንም ሆነ የሰዉን ዓይን አፍሬ የሮጥኩትን ያህል አዳም ከተከለከለው ዛፍ በለሷን የበላ ግዜ ተሸማቆ ሮጧል ብዬ አላስብም።

ቤት እንደ ደረስኩ “እኔ ተሳስቼ ይሆን እንዴ? “ በሚል የሞኝ ግምት ያንን የመጽሃፍ ቅዱስ ክፍል ደጋግሜ አነበብኩት። ግን ምንም አልተቀየረም፤፤ በቃ ያ ሌንጮ ሞተ!፤፤ ያ በእናቱ ማህፀን ጥበብን ጨርሶ የተወለደው፣ የቤተሰቡ ኩራት የሆነው፤ ጎረቤት ሁሉ “የኔ በሆነ” እያለ የሚቀናበት፣ የነገው ሳይንቲስት ... ሌንጮ የመርዛማውን ዛፍ መርዛማ ፍሬ በልቶ ከሞቶች ሁሉ በላይ የሆነዉን የቁም ሞት ሞተ።

ከዚህች ቀን ጀምሮ የትምህርት ጉዳይ ተከደነ። የእናቴን አደራ ከግብ የማድረስ ህልምም በፍርሃት ደመና ተሸፈነ። “ፈጣሪ ሆይ ነግቶ ከእንቅልፌ ስነቃ ይህን የሰይጣን ሰሜት ከውስጤ ንቀልልኝና ወንድ አድርገኝ። ካልሆነ ደግሞ እባክህ አታንቃኝ በዛው ልተኛ… “ የሚሉ ልመናዎች የሁሉም ለሊቶቼ ማሳረጊያ ሆኑ። ግን የሆነው ተቃራኒ ነበር፤፤ ከሰሜቴ እለት ከእለት መናር ባሻገር ፈጣሪም ለልመናዬ ፈፅሞ ጆሮውን ነሳኝ። ደመና በደመነ እና ሰማይ ባጉረመረመ ቁጥር “የሚዘንበው ውሃ ነው ወይስ እሳት ይሆን? እያልኩ መጨነቅ፣ መብረቅ በጮኸ ቁጥር ሸንቴን መቆጣጠር እስኪያቅተኝ ድረስ በድንጋጤ መንዘፍዘፍ ኑሮየ ሆነ፤፤ ፍርሃት ህይወቴን ወረሳት። እናቴ ራሷን እሟት ከተኛች በኔ ሰበብ ነው። የቤተሰቦቼም ትዳር መበተን ሰበቡ እኔ ነኝ። ትንሹም ትልቁም መጥፎ ነገር የሆነው በኔ ሰበብ ነዉ ብየ ማሰብ ጀመርኩ። ከቤተሰቤ አልፎ ጎረቤት እስኪገረም ድረስ የህይወቴ ሀሁ ተለዋወጠ። የአስተማሪዎቼ የከንፈር መምጠጫ አሻንጉሊት እስክሆን ድረስ ከትምህርት ጋር ባዳ ሆንን። ከሱ መለየተ ሞት ስመስለኝ የነበረዉን ማሜንም በዓይኔ ማየት እንኳን ሸከከኝ።

በዚህ ላይ የገጠምኩትን ሰዉር ጦርነት ያልተረዱ ቤተሰቦቼ በኔ ተስፋ ቆርጠው ተውኝ። እናቴ ደግሞ ሰወጣ በእንባ ሸኝታ ስገባም በእንባ እኔን መቀበል ስራዋ አደረገችው። ነገሩን ሳጣጥረው ፤ ሰውም አምላክም ኦና ምድረ በዳ ላይ ብቻዬን ተውኝ።
ከፈጣሪም ሆነ ከሰዉ መፍትሔ ባጣሁ ግዜ ፈጣሪን ጠይቄዉ የከለከለኝን ሞት ለራሴ ልሰጠው ወሰንኩ። ነገር ግን ተቆጥረው ለማያልቁ ቀናት ገመድ ይዤ ጫካ ብገባም ላደርገዉ አልቻልኩም፤፤ መርዝ ልጠጣ አንድ ሺህ ግዜ ቆርጬ አንድ ሺውንም ግዜ የመርዝ ብልቃት አቅፌ ከነ ፍርሃቴ ተኛሁ። ሃሳቤን ከግብ ማድረስ ዳገት ሆነብኝ። ዛሬ በህይወቴ አቅዶ ከግብ ያለማድረስ ክፉ አባዜ አለብኝ። ይህ አባዜ ግን እንዲሁ የመጣ ሳይሆን እራስን የማጥፋት አቅድ ሱስ እስኪሆንብኝ ድረስ ለሚሊዮን ግዜ ወስኜ ባለማሳካቴ የተነሳ ነዉ።

ይህን ክፉ የመከራ ባህር እየዋኘሁ፣ መኖሬን እንኳን ሳላውቀው ልጅነቴ ጭልጥ ብሎ ጉርምስና መጣ። ጉርምስናና ፍቅር ደግሞ ድንቅ ቁርኝት አላቸው አይደለ? ታዲያ የእድሜ እኩዮቼ በጦር የተወጋ የልብ ቅርጽ እየሳሉ በፍቅር ቃላት አሸሞንሙነው ልባቸውን ለሰረቀችው ኮረዳ የፍቅር ደብዳቤ በመላክ ተጠመዱ። የተሳካለትም በፍቅር የጣለችውን በፍቅር ጥሎና አቅፎ ደረቱን እየነፋ መራመድ ጀመረ።

እኔ ደግሞ በቅናት ዉጋት ተያዝኩ፤፤ ያነስኩ መሰለኝ፤፤ ከቅናት መርፌና ለራሴ ከማነሴ በላይ ደገሞ “ እሱ ከሴት አያወራም ጃንደረባ ነው ... “ የሚል ድምፅ ንፋስን ተንተርሶ ጆሮዬን ይዳሰሰ ጀመር። ሰው ይበለኝ ቀልቤ ይበለኝ ባላውቅም በሃፍረት እና በፍርሃት ተውጬ ተወዘወዝኩ። “ምን ይሻለኛል?” ብዬም ለራሴ አጉረመረምኩለት። በማጉረምረም ብቻም አልቀረዉም፤ ጊዜ ወስጄ አሰብኩበትና መላ አበጀሁ። “ ከወንድ መዋል፣ ወንድ የሚያደርገውን ማድረግና ምን ተብሎ የኮረዳይቱን ልብ ማቅለጥ እንደሚቻል መማር”። ከዛም ጓደኛ አበጀሁ። ጓደኝነቱ እንዲጠነክር እና የወንድነት ሚናዬ ሙሉ ይሆን ዘንድም ከወንዶች ጋር ጫት መቃም ጀመርኩ። ጫት ደግሞ ትንባሆን እና ጨብሲን አስከተለ። በአጭር ግዜ ውስጥ ወንድ ያደርጋል ብዬ ያሰብኩትን ሁሉንም አደረኩ። እንደውም እራሴን “ከወንድነተት መሃል አገኘሁት “። ቢሆንም አንድ ጉዳይ ላይ ግን አሁንም ችግር ገጠመኝ፤፤ እሱም አንድ ወንድ ለተቃራኒ ጾታ ወይም ለሴት ያለው ስሜት ምን እንደሆነ መማር ዳገት ሆነብኝ፤፤ የሚማሩት ጥበብ ሆኖም አላገኘሁትም። ያም ሆነ ይህ ግን ጉዳዩ የመኖርና ያለመኖር ጉዳይ፤ የወንድነቴ መለኪያ ስለሆነ በምርቃና እና በጨብሲ ሃይል ታግዤ፤ እንድሁም ከጓደኞቼ የተማርኩትን ቃላት ምላሴን ቀብቼ የመጀመሪያ ኮረዳ ጣልኩ፤፤ ለመጀመርያ ግዜም ከሴት ጋር ተኛሁ። የማይታመን እውነታ ነበር። በደስታ ከነፍኩ፤ ደረቴን ነፍቼ በኩራት ሸለልኩ። ጉልበታሙ ፈጣሪ ያልገፈፈልኝን ሰይጣን በአረቄና በጫት ያሸነፍኩት መሰሎኝ ደስታዬ ጣሪያ ነካ።
አተኩረዉ ካዩት ዉስጥም ሌላ ዉስጥ አለዉ እንደምባለዉ ግን ከሴት ጋር መተኛት በቻዉን ወንድ እንደማያሰብል ቶሎ ነበር የተረዳሁት፤፤ ልቀላቀለዉ በምታትረዉ የወንድነት ዓለም ውስጥ የወንድነት ልክ የሚለካው ከሴት ጋር በመተኛት ብቻ ሳይሆን አብረው በተኙት የሴት ብዛት፣ ኪሰ ውስጥ ባለ የገንዘብ መጠን ና የመሳሰሉት ነበር ። ይህን የተረዳችው ዘማች ልቤም ሸፍታ እንዳላበቃች ገባትና ለሌላ ሸፍትነት ተሰናዳች። የሱስ ጌታው፣ የሴት አተራማሽ፣ የበጂ መለኪያ፣ የወንድ አውራ ተብዬ መጠራት አማረኝ። በምኞት ብቻ አልቀረሁም፤ ያለምንም ርህራሄ ከእናቴ መቀነት ሸረፍራፊ ሸልንጎችን ከመቦትረፍ የቤት ዕቃ አዉጥቼ እስከ መሸጥ ደረስኩ። እንደ ወንድ ቅሜ መረቀንኩ። እንደ ወንድ ጠጥቼ ሰከርኩ፤፤ ዓይኗን ሰበር ካረገችልኝና ልቧ ከራራልኝ ሴት ሁሉ ጋርም ተንከባለልኩ። “እረገዝኩ ምን ይሻለኛል?” ያለችኝ

ሴት ላይ የምጸት ሳቅ ሰቄ ወንድነቴን ሃገር እንዲያውቅልኝ አደረኩ። ከጋንጃ ቅጠል ጋር ተይዤ እስር ቤት ገባሁ። በእናቴ ውትወታ እና የእንባ ጎርፍ ብፈታም ለኔ ግን “ የአራዳነት “ ሪከርድ ነበር።

“ ፓ! ሌንጮ እኮ የሴት መድሃኒት ነው፣ የበጁ ልክ፣ ምላሱ የሴትን ልብ ፈቶ እንደገና ይገጥማል።”
“ ምን ይህ ብቻ! ሃያ ጠርሙስ ቢራ ለሱ ምንም አይደል የተጎነጨም አይመስለውም፣ ጋንጃውንም እንደ ውሃ ነው ሚጠጣው” ተብሎ ተወራልኝ።

የህልም ዘውዴን ጭኜ፤ እራሴን የወንድነት የከፍታው መቀመጫ ላይ አስቀመጥኩት። በውሸት እና በሞኝነት ከሰፈርኩበት ዙፋኔ ላይ ላለመውረድም የዝሙት ጥጋ ጥጉ ሳይቀረኝ ተመላለስኩበት። ታዲያ ከመቀነቷ የምነጥቃቸዉ ሽልንጎች ከምሸሸዉ የሰዶማዊነት ማጥ ከጠበቁኝ የእናቴ እንባ ከአንድ ጠርሙስ ቢራ በምን ይበልጥልኛል? የሐጥያቴን ሸክም ያሸከምኳቸው ሴቶች እንባስ? የእሳት ዝናብ ከሚያዘንበው ሰዶማዊነቴ ጋር ሲነጻጸር ለቅሷቸዉ ለጆሮ የሚለሰልስ ሙዚቃ አይደለምን?

እናም በዚህ ማለቂያ በሌለው የጥፋት ባህር ውስጥ ስመጥኩና በደምብ ዋኘዉ... ዛሬ ላይ ለማሰብ እንኳን የሚከብደኝን በደልም በራሴ፣ በቤተሰቦቼ እና በታዳጊ እህቶቼ ላይ ፈፀምኩ። የጉርምስናዬ ግማሽ እድሜም ነገው ባልታለመ የጭላንጭል መብራት ተመርቶ ተሰፋ በሌለው መሽቶ መንጋት አለቀ።

## ክፍል ሶስት
## መረራ እና ወሊሶ፦

በነዛ የሞኝነት አመታት ውስጥ ተሰፋ የቆረጥኩበት የትምህርት ዓለም ፈጽሞ ፊቱን አላዞረብኝም ነበር። በሕልም ዓለም ውስጥ እንዳለሁ የመጀመሪያ ዲግሪዬን በጥሩ ውጤት ጨረስኩና ወደ ስራ ተሰማራሁ። በዚህ ጊዜ ግን ሁለት ትልልቅ ዉሳኔዎችን ወሰኜ ነበር፤፤ እነሱም ከሴቶች ጋር ያለኝን ቅርርብ ማላላትና ብዙ ዋጋ ያስከፈልኳት እናቴን መካስ ነበሩ፤፤ በነዚህ ዉሳነዎች ምክንያት ቀልቤ ቢረጋጋም ያ የተደበቀዉ ሰሜቴ ደግሞ “እስከ መቼ?” እያለ መኮርኮሩን ጀምሮ ነበር። በእንዲህ እያለሁ ከአሰራ ሁለት ዓመታት የተጠማዘዘና የሞኝነት ጉዞ በኋላ በአንድ ሰልክ ምክነያት አዲስ ጮራ በድንገት ህይወቴ ላይ በራ።

ምን ሆነ መሰላችሁ፤ አንድ ቀን ጥዋት ላይ ቢሮዬ እነደገባዉ ጠረጴዛዬ ላይ ባለው ኮምፒውተር ጉግል ከፈትኩ። ላፍታ ያህል የኮምፒውተሬ መስኮት ላይ ካፈጠጥኩና ካሰብኩ በኋላ ለመጀመሪያ ግዜ “Gay” የሚል ቃል ጻፍኩኝና ፍለጋዬን ቀጠልኩ። ከትንሽ ሴኮንዶች በኋላም የተለያዩ ጽሁፎችና

የሰዎች ፎቶ ጥቁር ነጭ ሳይሉ ሰልፍ ይዘው ተከሰቱ። ፎቶዎቹን በየተራ እያየዉ ሳለ የአንድ መልከ መልካም ፈረንጅ ፎቶ እየሁና ቆምኩኝ። እዚህ ፎቶ ስር ብዙ አስተያየቶች ተሰጥተው ነበር። ከነዚህ አስተያየቶች መሃል ግን አንድ አስተያየት ማየቴን እንኳ ማመን አቃተኝ። “091135.....” የኢትዮጲያ የሰልክ ኮድ ነበር። በድንጋጤ ከፈትኩት።

“I like your face” ይላል የመጀመሪያው አስተያየት። የስልክ ቁጥሩ ባለቤት አስተያየት መሆኑ ነው። ቀጥሎም “reply” ወደሚለው ቁጨት ገባሁ
“oh thank you. From where you are?” የፎቶው ባለቤት መልስ ነበር።
“Im from Ethiopia” ቀጠለ
“Oh, really! I have a plan to visit Ethiopia soon ...”

091135....ድንጋጤየ ጨመረ! የኔን አይነት ስሜት የሚጋራ ሌላ ሰው ኢትዮጲያ ውስጥ መኖሩን ውስጤ አምኖ መቀበል አቃተው። ቁጥሩ ይጠፋብኝ ይመስል በፍጥነት ወደ ስልኬ ገለበጥኩትና ሳላስበዉ ስልኬን ከጆሮዬ ከደንኩት። ጠራ! በድንጋጤ ዘጋሁትና ወረወርኩት። ስልኬ ከጠረጴዛው መውደቁና የጥሪ ድምጽ ማሰማቱ እኩል ሆነ። አንስቼ ሳየው አሁን የደወልኩት ቁጥር ነበር። ዘጋሁት። ተደወለ። ዘጋሁት፤፤ ተደወለ…። በዛ ጫፍ ያለው ደዋይ በቀላሉ የሚለቀኝ ሆኖ አልተገኘም። ስልኬን “Switch off” አደረኩ ና በሩጫ ከቢሮ ወጣሁ።

ከቢሮ እንደወጣሁ ጫቴን ገዝቼ ከአነዱ ሽለቆ ብከተትም ውስጤ መረጋጋት አቃተው። አንዴ የሚመስለኝን ሰዉ በማግኘቴ ደስታ፤ አንዴ ደግሞ ቸኩዬ በመደወሌ ፍርሃትና ፀፀት… በቃ በስሜቶች ወጀብ መሃል ገባሁና የሰይጣን ከበሮ ሆንኩኝ።

ለማላስታውሰው ግዜ በሃሳብ ሰብከነከን ከቆየሁ በኋላ ምርቃናን ምሰጋና ይድረሰውና መጥቶ አረጋጋኝ። በምርቃናዬም ዳግም ብርታት አገኛቼ ስልኬን አበራሁት። ገና ጣቴን ሳላነሳ ግን አሁንም ስልኬ ጫጫታዋን ጀመረች። እሱ ነዉ፤፤ እንደ መጀመሪያው ሁሉ መልሼ ዘጋሁበት። ደጋግሜ ብዘጋበትም በዛ ጎን ያለው ሰው ምን አይነት ትዕግስት እንዳለው አላውቅም መደወሉን አላቆም አለ። ምን አይነቱ ነው የገጠመኝ ባካችሁ! አብዶ ድኖ ነው ወይስ አብዶ? ብዬ ራሴን ጠየኩ።

ምን ማድረግ እንዳለብኝ ሳወጣ ሳወርድ አሁንም ምርቃናን ምሰጋና ይግባውና የሚገርም ሃሳብ አመጣልኝ። “ተመሳሳይ ስሜት ያለን ይመስለኛል” የሚል አጭር መልዕክት ላኩለት። በፍጥነት መልሰ ሰጠኝ። ከዚህ በኋላ በድምፅ ማውራት እንደፈራሁ እና በአጭር የጽሑፍ መልዕክት ብቻ ማውራት እንደምንችል አስረድቼው ማውራት ጀመርን። ከተወሰኑ መልዕክቶች በኋላ

ደግሞ በድምፅ እንድናወራ መልሶ አሳመነኝ እና ተግባባን። ይህን ታሪካዊ ስልክ ለማውራት ግን ምርቃና ብቻውን በቂ ስላልነበር በቅርብ ያለች አንድ ግሮሰሪ መግባት ግድ ነበር። አንድ ሁለት ብዬ ሞቅ ካለኝ በኋላ በቢራ ጠርሙሶች ተከልዬ ስልኬን ተጫንኩት። አንድ ረጋ ያለ ድምፅ ከወዲያ ማዶ ሄሎ አለኝ። ይህ ድምፅ ግን ድምፅ ብቻ አልነበረም። ለአዲስ ህይወቴ የንጋት ጮራና ሁለንተናዬን በርጋታ የሞላ ከድመጾች ሁሉ በላይ የሆነ የተባረከ ድምፅ ነበር። “my guardian angel ጠባቂ መልአኬ” የሚል ድምፅ ውስጤ ሲደውል ተሰማኝ። አጭር ሰላምታ ተለዋወጥን፤፤ ከሰልምታ ቀጥሎም በወቅቱ ያልገቡኝን ብዙ ጥያቄዎች ደረደረልኝ። ከመልሶቼ መሃል ያላሳቀው መኖሩን ግን አላስታውሰም።

ቀጠልን፤፤ ደቂቆች ወደፊት በተንደረደሩ ቁጠር መቾት እየተሰማኝ ውስጤ ባዶ የሆነ እስኪመስለኝ ድረስ ያለኝን አራገፍኩለት። ከሰባ ደቂቃ ወሬና ውይይት በኋላ “ጠባቂ መልአኬ” እንዲህ አለኝ “ አሁን ጥሩ መደፍ ላይ ወድቀሃል። ይህን ስልክ እንደዘጋህ አንድ ስላንተ ትክክለኛ መረጃ የማይገልጽ የውሸት ፌስቡክ አካውንት ክፈት። ሰሜ እገሌ ይባላል። ከከፈትክ በኋላ ፈልገህ ጓደኛ አድርገኝ፤፤ በመቀጠልም ከጓደኞቼ ዝርዝር ውስጥ ግባና Victor Geta, Happy Addis, Robel Hailu, Tegbabi Wetat, Boche Doche Bino, Nathy Nathy, Solomon Fiker, Kamal Fitsum..... የሚባሉ ሰዎችን ፈልገህ ጓደኛህ አድርግ… ስልኩ ተዘጋ።

ሌንጮ ሸገር ተወለደ! እሱን ጨምሮ ያለኝን ሰዎችም በፌስ ቡክ ተጎዳኘሁ። እውነቱን ለመናገር እነዚህ ሰዎች እንዲሁ በህይወት አጋጣሚ ያወኳቸው ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ የወደቀውን ህይወቴን ያነሱልኝ የፍቅር መልእክተኞች ነበሩ። ያንን የሞኝነት ዘመኔን እያስታወሰኩ እስክሰቅ ድረስ ብቸኝነቴን አሰረሱኝ። መካሪ ሆኑኝ። አስተማሩኝ። ወደር ለሌለው ውለታቸው አቻ ባይሆንም በዚህ ፅሁፍ ሰም ላመስግናቸው እወዳለሁ።

በዚህ መልክ የተጀመረዉ የማንነት ጉዞ ነበር ከወራቶች በኋላ ከመረራ ጋር ያገናኘን። እኔና መረራ ከፌስቡክ ወደ ስልክ፣ ከስልክ ወደ ፎቶ መለዋወጥ ተሻገርን ለወራቶችም አወራን። የህይወት ሚስጥራችንን አንድ ሁለት እያልን ተጋራን። ወደድኩት ወደደኝ። በሰስት የተሞላ የርቀት ፍቅር ሁለታችንንም አከነፈን። ያየኝ ሁሉ እስኪገረም ፀባዬ ሙሉ በሙሉ ተለውጦ ሙሉ ሰው ሆንኩኝ። ለዘመናት የሸሸሁት ኑሮዬና ማንነቴ ጋር እርቅ ፈጥረን ጉዞ ጀመርኩኝ። ግንቦት 21 2007 ዓ.ም ወሊሶ ከተማ አንድ ሆቴል ክፍል ውስጥ እኔና መረራ አልጋ ላይ ቁጭ ብለናል። ፍርሃት አይሉት ጥርጣሬ የተደበላለቀ ስሜት ወሮን ነበር። እኔማ ከፍርሃት አልፌ ልቤ በአፌ ልትወጣ ደርሳለች። በዚህ አስፈሪ ቅጽበት መራራ እንደ እሳት የሚፋጁ ወፋፍራም ከንፈሮቹን ከመንቀጠቀጡ ከንፈሮቼ ጋር አላተማቸዉ። የወንድ ከንፈር።

ዓይኖቼን ጨፈንኩና ውስጤን አደመጥኩ። የአስራ ሁለት ዓመት የሞኻነት ሃሳብና ውዥንብር እንደ ጅራፍ እየተንጣጣ ከላዬ ላይ ሲወርድ ተሰማኝ። ሊወድቅብኝ ይዳዳ የነበረው የፍርሃት ተራራ በፍቅር ሃይል ተንዶ ፍርክስክሱ ሲወጣ ባይኔ በብረቱ እየሁ። የእሳት ዝናብን የቋጠረው ደመናም በድንገተኛ አውሎ ንፋስ ተበተነና በህይወቴ ላይ አዲስ ፀሐይ አበራች። ሰላም በተሞላው አየር ዉስጥ በአዲስ የፍቅር ዜማ ታጅቤ እጄን ዘረጋሁ። በሙሉ ራስ መተማመን መረራዬን አቅፌ በፍቅር ባሕር ውስጥ በፍጹም ደስታ ሰመጥኩ።

## ክፍል አራት
## ማንነት ህልም ባይሆን እንኳ እኔ ግን ህልም አልከለክልም፦

ዛሬ ያለንበት ክፍለ ዘመን ሰልጣኔ ጫፍ የነካበት ዘመን ነው። በተለይ ማህበራዊ ግንኙነቶች ላይ ያተኮረ ቴክኖሎጂ ከልህቀት አልፎ ዛሬ ከዓለም ጫፍ ዓለም ጫፍ ሆኖ መገናኘት እጅጉን ቀላል ሆኗል። ወደ እኛ ወደ ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪያን ስንመለስ ደግሞ እኛ ከዚህ ቴክኖሎጂ ብዙ አትርፈናል ማለት ይቻላል። በተለይ ባለፉት አሰርት ዓመታት ውስጥ ሃገራችን ውስጥ መስፋፋቱን ተንተርሶ ብዙ ጥቅሞችን ሰጥቶናል። ይህን ሰልጣኔ ተንተርሰንም በብዙ ኪሎ ሜትሮች ርቀት ላይ ሆነን ተዋውቀናል። ጓደኛሞች ሆነናል። ለእናት ልጅ እና ለቅርብ ጓደኛ የማናጋራዉን ሚስጥራችንን ተጋርተናል። በአካልም እንድንገናኝ ምክንያት ሆኖን ደስታን ተጋርተናል።

ሆኖም ግን ይህንን እድል ተጠቅመን መሰባሰባችን እንደ ጥሩ እድል ቆጥረን የተሻለ ህይወት ለመፍጠር ጥረት አድርገናል ወይ? የሚለው ጥያቄ ወሳኝ ጥያቄ ነው። በተለይ ከመሃል ሃገር ርቀን ያለን ሰዎች ይህን እድል ተጠቅመን ጓደኝነት መሰርተናል? ከወገብ በታች ካለዉ ስሜታችን ባለፈ እንደ አንድ ማህበረሰብ ራስን ለመገንባት፣ ለመተጋገዝ፣ ለመማማር እና ለመበረታታት ምን ያህል ሰርተናል? መልሱ ቀላል ነው! ምንም አልሰራንም:: እንደዉም የተጎዳነው እና ሌላዉንም የጎዳነው ይበልጣል ቢል ማጋነን አይሆንብኛም:: ምክንያቱስ ምንድነው? እስኪ የኔን የሕይወት ልምድ ተንተርሰን ትንሽ ነገር እናዉጋ...

1ኛ. ለራሳችን ማንነት ያለን ግንዛቤ የተሳሳተ መሆን።

አንድ ወዳጄ እንዲህ ብሎኝ ነበር “ይህን የተረገመ ህይወት መኖር ላንተ አይገባህም እኔም ካንተ ጋር ይህን እፀያፊ ድርጊት የማደርግበት ሞራሉ የለኝም...”። ከዚህ ጓደኛዬ ጋር በማህበራዊ ሚድያ ነበር የተዋወቅነው። ለብዙ ጊዜ ሃሳቦችን ተለዋውጠን የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ብንስማማም፣ በተወሰኑ ምክንያቶች የተነሳ በአካል እስክንተያይ ድረስ ማንነቴን አላወቀም

ነበር። የቀጠሮ ቦታችን ተገናኝተን ለወራት ሲያወራዉ የነበረው ሰው እኔ መሆኔን ሲረዳ ግን ወዳጄ በድንጋጤ እና ጥርጣሬ ተወረረ። በሌላው ዓለም ከሚያውቀው ማንነቴ የተነሳ እኔ በእውነት ይህን የኃጢያት ኑሮ (በእሱ አመለካከት) የሚኖር ሰው ነዉ ብሎ ለመቀበል ከበደው። ምክንያቱም በሱ እምነት ይህን ህይወት የሚኖር ሰው (ወንድ አፍቃሪ ወንድ) ማለት፣ ኃጢያተኛ፣ የተረገመ ፍጡር፣ ለሃገሩ እና ለወገኑ መኖር ወይም አዋቂ መሆን ቀርቶ ለራሱም ኑሮዉን ማቃናት የተሳነው ስነፍ እንደሆነ ነው።
አመለካከቱ እጅጉን ቢያናድደኝም ስሜቴን ዋጥ አደረኩና የተለያዩ ርዕሶችን አንስቼ ላስረዳው ሞከርኩ። ቢሆንም “የኔ አይነት ሰው ምንም ይሁን ምን፣ አንተ ግን የሆነ ጥናት አጥንተህ በኔ ዙሪያ የሆነ መጽሐፍ ለመጻፍ ካልሆነ በስተቀር የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ አይደለህም” ብሎ ሞገተኝ። የመጣልኝ ዘዴ ሁሉ ተጠቅሜ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ መሆኔን ለማሳመን ጥረት አደረኩ። ያም ሆኖ ግን ከላይ የጠቀስኩትን አሳዛኝ ንገገር ተናግሮኝ በእንባ ተለየኝ። ወንድም አለሜ፣ እህቴ ሆይ ስሙኝ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ መሆን ከህይወት ክፍል አንዱ ብቻ ነው። ከሁሉ ነገር በላይ እኛ ሰው ነን። እንደማንኛዉም ግለሰብ መማር፣ መስራት፣ ሀብት ማካበት፣ ማመን፣ መታወቅና መከበር እንችላለን። እጅግ ብርቱ እና በዘመናቸው ድንቅ የሆኑ ሐኪሞች፣ ደራሲዎችና አርቲስቶች፣ አዋቂዎች እና ሃገር ወዳድ የሆኑ የሃገር መሪዎች በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪዎች ነበሩ። ዛሬም አሉ፣ አለን። ወደፊትም ይኖራሉ። እንኖራለን። ብዙ ርቀት ሳንጓዝ ዛሬ ዓለምን እጀብ ያሰኘዉንና የኑሯችንን ትልቁ የጀርባ አጥንት የሆነውን ኮምፒውተርን የሰራው የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ የሆኔ ግለሰብ እኮ ነው።

ታድያ ለምን የገዛ ሕይወታችንን ውሉን አጋጭተን ቅርፅ እናሳጣዋለን? ይህ ችግር ሁሉም ቦታ ያለ ቢሆንም በክፍለሃገር እና በገጠር አከባቢ ይብሳል። ብዙ መጓዝ የሚችሉ ሰዎች ለማንነታቸው ባላቸው አመለካከት እራሳቸዉን አጥረው ከመንገድ ቆመዋል። እንደ አንድ የማህበረሰብ አካል ከመተባበር ይልቅ በስሜት ተነድተው ከእንቅፋት ጋር እራሳቸዉን ድረዋል። ነገር ግን ይሄን የመገናኘት እድላችንን በተሻለ መንገድ ብንጠቀም ከትርፉ ብዙ ተጠቅመን እኛም ተለውጠንበት የዚህን ማህበረሰብ ምልከታም በለወጥን ነበር።

2ኛ. አንድ ቀን ሌላ ሰው ሆኖ ከእንቅልፉ ለመንቃት የህልም ዓለም ዉስጥ መኖር።
እስከዛሬ ካገኘኋዋቸው ጓደኞቼ ዉስጥ አብዛኞቹ በድንገት ሳይፈለጉት ወደዚህ ህይወት እንደገቡ ይተርኩልኛል። በዚህ ጉዳይ ምንም ማለት አልፈልግም። የሚገርመኝ ነገር ግን ይህ ማንነታቸው በእርግማን የመጣባቸው የሐጥያት ሁሉ ታላቅ፣ የሰይጣን መንፈስና የምዕራባውያን ወረራ ወይም የኢሉሚናቲ ሥራ ነው ብለው ማመናቸው ነው። በዝህ ላይ

ደግሞ “የሆነ ቀን የሆነ ኃይል መጥቶ ከዚህ ህይወት ያወጣኛል” ብለው ይመኛሉ። አንድ ታሪክ ልንገራችሁ። አንድ በህይወቱ ደስተኛ ያልሆነና ከዚህ ህይወት ለመውጣት የሚታገል ግን ደግሞ ሊሳካለት ያልቻለ ወዳጅ ገጠመኝ። ሁኔታው በጣም ስላሳሰበኝ የራሴን ህይወት በምሳሌነት አንስቼ የወንድማዊነት ምክሬን ለገስኩት፤፤ እናም እራስን የማጥፋት እቅዱን ትቶ ህይወቱን ማስተካከል ላይ እንዲያተኩርም ቃል አስገብቼው ተለያየን። ከወራቶች በኋላ ከዚህ ወዳጄ ጋር ዳግሞ ተገናኘንና ስለ ህይወቱ ጠየኩት። እሱም በንዴት ተሞልቶ “ተወኝ ባክህ! ይሄንን ልገላገለው ጫፍ የደርስኩትን ህይወት መክረህ እንድመለሰበት ያደረከኝ አንተ ነህ…” ብሎ ተቆጣ። ንግግሩ ቢያስኮርፈኝም እንዴት ማለት ጠሩ ነዉና “እንዴት?” ብዬ ጠየኩት።

“የሴት ጓደኛ ይዤ የፍቅር ህይወት ከሷ ጋር ጀምሬ ነበር። ግን ምን ያደርጋል? ካንተ ጋር ካወራሁ በኋላ፣ልቤ መልሶ መዋለል ጀመረ፤፤ ይባስ ብሎ ደግሞ አንድ ቀን ከዚች ፍቅረኛዬ ጋር ተገናኝተን ፍቅር እየሰራን ሳለ “ከተማህ መጥቼ እንትና የሚባል ሆቴል ነኝ ከፈለክ ና እንገናኝ” የሚል መልዕክት ስልኬ ላይ ተላከ። መልዕክቱን ባየሁበት ቅፅበት ፍቅረኛዬ ያልኳትን ልጅ እዛው አልጋ ላይ ትቻት እባብ እንዳየ ሰዉ ዘልዬ ወጣሁ፤፤ እናም ወደ ሆቴሉ አመራሁ…” ብሎ በቁጭት ተረከልኝ።
ይህ አብዛኞቻችን እየኖርን ያለነው አሳዛኝ ህይወት ነው። አብዛኞቻችን ሌላ ሰው መስለን መኖርን ስለምንመኝ ከገዛ ራሳችን ርቀናል። እራሱን የተወ ወይም ከራሱ የራቀ ደግሞ በማይገባው ጎዳና እየተጓዘ እራሱንም ሌሎችንም ይጎዳል እንጂ ሁኔታው አይቀየርም።
እውነት ነው ሃይማኖትና ባህላችን በዚህ ማንነታችን ላይ ትልቅ ተፅዕኖ አሳድረውብናል። ይህም የተሳሳተ አመለካከት እንዲስፋፋ ትልቅ አስተዋፆ አበርክቷል። ይህ ደግሞ ማንነታችንን ከመቀበል ይልቅ ከዛሬ ነገ ከዚህ ህይወት የሆነ ኃይል ያወጣኛል የሚል የሕልም ዓለም ጋር ተጣብቀን እንድንኖር አድርጎናል። በመልካም ጓደኝነት ሚዛኑን የጠበቀ ህይወት ከመኖር ይልቅ ተስፋ በመቁረጥ ከሴሰኝነት ባህር ጠልቀን እንድንዋኝ አድርጎናል።ከወገብ በታች ላለ ስሜታችን ተገዝተን ለወሲብ ብቻ የምንፈላለግ ሰዎች ሆነናል። መጎዳድት ባህላችን ሆነ። እስኪ ታሪክህን ተናገር ቢባል ከወሲብና መጎዳዳት ያለፈ የፍቅርና የመተጋገዝ ታሪክ የሚነግረን ከኛ መሀል ማነዉ
ትልቁ ህልማችንስ የሆነ ቀን ሌላ ሰው ሆነን ከእንቅልፍ መንቃት ነው ወይስ ከማንነታችን ጋር እርቅ ፈጥረን ከወንድሞቻችን ህብረት መሰርተን መኖር ነው? ዓለማችንን ከ ወሲብ አሻግረን አይተን መቀራረብ፣ መወያየት፣ መበረታታት፣ መመካከርና አንዳችን ከአንዳችን መማማር የለብንም ወይ?

እንግዲህ ይህንን ጽሑፍ የምታነብ ወዳጄ ሆይ ማንነት ቆሻሻ አይደለም ታጥበህ አታፀዳውም። ህይወትም ሕልም አይደለም ስትነቃ በኖ አይጠፋም። ወይም ነቅተህ ሌላ ህይወት አትኖርም። ስለዚህ ከማንነትህ ጋር ታረቅና ለህይወትህ

ትርጉም አበጅለት እልሃለዉ።

ከኔ ተማር። ለፈጠረኝ ምስጋና ይግባዉ! እኔ ከማንነቴ ጋር ከታረቅኩ ጀምሮ ትላንትና የጎዳውትን ሕይወቴን ለማስተካከል ብዙ ለፍቻለሁ። ዛሬ ከራሴ ተርፌ ለሃገር ለወገኑ የሚጠቅም ትልቅ ሰው ሆኛለሁ። ከራሴ ጋር መታረቄ ከፈጣሪዬ፣ ከቤተሰቤና ከዓለም ጋር አስታርቆኛል። ዛሬ ሰላም አለኝ። ትልቅ ዓላማን ሰንቄ ከግቤ ለመድረስ እየታተርኩ እገኛለሁ። እንተን/ቺንስ ምን አገዳቸሁ ታዲያ?!

ለጊዜው ጨረስኩ። ደህና ሁኑ!
ሌንጮ ሸገር የኩሽ ሀገር ሰው!

# Afterword X Preface

In a typical anthology series, this section would appear at the beginning of the book, serving as one of the first points of contact between the reader and the works enclosed within—an introductory essay that would outline the contents of the book in a careful methodological manner. But this e-book, much like any queer knowledge production, requires a certain degree of waywardness, a subversion of normative expectations of what a collection of personal stories should be, how it's structured, and the limits set by its mode of production. The result is this essay, which is in part an afterword and in part a preface. It is a deliberate choice, one that intends to foreground any form of discourse about queer Ethiopian culture from the mouth(s) where it flows. Thus, the book starts with a preface written in Amharic before opening into a collection of personal accounts and essays written in Afaan Oromo, Amharic, and English. It also ends in a translated version (from Afaan Oromo to Amharic) of the opening text, a story that serves as a guidepost from one end of the book to another.

The contents of the book are diverse reflections and responses to the question, "What does queer Ethiopian culture mean to you?" It's a daunting task entrusted both to our contributors and editors in an attempt to capture a nebulous concept such as culture into one collection. Even harder is the idea of "queer Ethiopian culture," as it contains three distinct terms that hold multiple meanings and implications. Although each of these terms requires careful deconstruction and analysis in relation to one another, this essay does not intend to do that, at least not directly. One main reason is that attempting to define what it is or means

to be “Ethiopian,” for example, is to invoke the same frameworks that are used to marginalize and silence us. The same can be said about “queer”, a word that, at first glance, can be libratory in its fluidity to encompass diverse identities but, at a much closer look, can feel exclusionary just as much. However, we borrow from American author, theorist, educator, and social critic bell hooks’ definition of queer in that “queer” to mean “not [just] who you’re having sex with, but about being at odds with everything around it, and that has to invent and create and find a place to speak, to thrive, and to live.” This definition somehow provides an expansive frame of thinking that grounds this exploration. And then there is culture, a much-written-about topic with disciplines solely dedicated to its study.

Anthropologists and sociologists define culture as the shared beliefs, values, and behaviors of a group of people. Culture is learned and passed down, shaping our thoughts, feelings, and actions while at the same time being influenced by geography, history, and religion. This results in it manifesting differently in different contexts across time. If there is one thing that is central to culture, it is language. The language we speak affects how we view the world, what we value, and the kinds of bonds we form with others. Language is a powerful tool that shapes our ways of communicating and thinking to the point that what we call something will affect our mental image of it. The role of language is also central to this book’s exploration, as we have tried to look at its function in relation to queer communities, meaning-making, and usage.

As queer Ethiopians, more often than not, our first contact with queerness is through insults directed towards us, admonishments that serve to police our

behaviors, or phrases that essentially tell us who we are and how we feel to be wrong from an early age. And as a consequence, these insults influence the relationships we have with others, going so far as to shape personality, subjectivity, and our being as individuals. It is when faced with these realities that marginalized communities either appropriate existing languages and words or create new ones all together. And through time, insults can become a marker of pride, while subtle coded language can turn into puns and vernacular. In volume 1 of N'or, we have attempted to illustrate this power of language through an article that examined the vernaculars and their usage by assigned male at birth (AMAB) sex worker communities in Addis Ababa. The article, for example, started as an attempt to trace the origins of the term Zega as a code name, but in the process opened up room for much more nuanced accounts of how queer communities have, through generations, employed language as identifiers, providing a window into their interactions (check out N'or Vol. I for more). In this volume, we try to show that in two articles. The first one is meant to provide a peek into online conversations and chatting culture, while the second one offers a witty take on "ፋጤ" a code word often used to refer to feminine gay men. It's a form of recognition, this act of speaking in the feminine, that both upends existing stereotypes as it perpetuates it.

While language is an important tool for expression, culture is reinforced through practices. Gatherings and festivities provide a sense of community and belonging, allowing a group of people to strengthen their identity and bond. One way that this manifests in the queer community is through private events that provide a relatively safe space for people to be and express themselves. These spaces exist as pockets of joy within

the city, fleeting clandestine meeting places undulating with what author Saidiya Hartman calls "rush and flight—the freedom to move, the want of liberty, the hunger for more, and the need of breathing room".

This dance between "rush and flight" could not be any more elucidated than in the excitement and anxiety that come with throwing private house parties or attending them. We have attempted to capture the former in a conversation with a party organizer who walks us through what goes on into throwing these underground events, from the lead-up to the event, the choices of music and set-up, to when the last person leaves the party and the clean-up ensues. Like any event, it has a number of moving parts and happens at great risk, but in the end, it is meant to serve as an enclave of happiness and a good time for communities that rarely get the chance to congregate en masse. Included in the book are also stories from partygoers, albeit two completely different takes, acting as a reminder that not all experiences are the same. While for some these parties are an exciting space to dance, drink, fuck, and let loose, for others they can be a point of discomfort and abuse. The stories serve as invitations to reflect on how these spaces, much needed and liberatory as they are, can at the same time encourage behaviors of physical, verbal, and sexual harassment.

No collection of stories about a community is complete without discussing relationships and the myriad ways they manifest. There are a number of stories in N'or Vol. 1 that broach the topics of romantic, platonic, and sexual relationships. This volume is no different in that there are submissions that also focus on the subject. What makes it slightly different from the preceding volume, however, is the fact that the stories

in this collection go a layer or more deeper in how they capture relationships. Normative social structures often set out rules and expectations for how relationships should be modeled. While our existence on its own challenges these expectations, we don't exist in a vacuum, and that oftentimes results in us succumbing to societal pressures in one form or another. This fact is expressed rather beautifully in a heartbreaking story of a relationship gone awry not for lack of love but because of societal and familial demands. In another story, a platonic relationship turns violent and dangerous upon our contributors coming out to their close friend. Somewhere else in the book, a group of friends decide to get married as a group, in a radical act of challenging set norms and dreaming of a different world, even if it's temporary.

There are several other topics that we wanted our contributors and readers to meditate on in this volume. However, to talk about all the stories here would take away from the pleasure and mystery of finding out the contents of this book in due course. There are a number of other stories that are meant to provide a glimpse into how our contributors have responded to our request for works focusing on queer Ethiopian culture. However, we want to stress that this book in no way attempts to be representational. First of all, anything that claims to represent a group of people, no matter how big or small, often ends up doing the exact opposite. The stories here are personal accounts of individuals' experiences with shared elements that can sometimes cut-across, as any human experience does. Secondly, a shortcoming of this volume in comparison to its predecessor is the lack of representation of LBQ, trans, and Gender Diverse stories. This is yet another reminder that, while there has been commendable effort and an increase in

content centered around LBQ, trans, and Gender Diverse people, there is yet more work that needs to be done in terms of inclusion and diversity of voices. And finally, this ebook is not meant to serve as a social commentary or critique of queer culture but rather as a repository of the different experiences of our contributing writers.

There is no specific map for the journey through this book, in so far as your experience is something that comes naturally to you. You can flip through (scroll might be the appropriate term here) from the first page and read each piece as it comes, or do a brief scan and start with where your eyes land, or even begin your journey from this piece and read it backwards. There is no right way to approach this, really. But we hope you accept our invitation and explore these topics with us.

N'or,

Anania T.

# ምስጋና፡-

ይህ የታሪክ ስብስብ ከኛ በፊት ለነበሩትና አሁንም በኛ መሃል ለሚገኙት በእውቀት ሳይሆን በየዋህነት ህይወታቸውን ለመሩት።

ከእኔ ይልቅ እኛን አሰበልጠው ቤተሰብ የገፋቸውን ታዳጊዎች ለሰበሰቡት።

ጓደኝነትን ወደ ምርጫ ቤተሰብ ለቀየሩት፣ መረዳዳትና መደጋገፍ ላሰተማሩን።

አጥንት የሚሰብር ሰድብን ጥርሰ በማያስከድን ቀልድ እንድንቀይር ላደረጉን ወግ አዋቂዎች ።

እንማርበት ዘንድ ታሪካችሁን ሳትሰሰቱ እውነታችሁን ሳትሸሽጉ አምናችሁን የላካችሁልንን እናመሰግናለን።

# ኖር

“ከዚህ ሌላ ደግሞ "የሆነ ቀን የሆነ ኃይል መጥቶ ከዚህ ህይወት ያወጣኛል" ብለው ይመኛሉ። አንድ ታሪክ ልንገራችሁ። አንድ በህይወቱ ደስተኛ ያልሆነና ከዚህ ህይወት ለመውጣት የሚታገል ግን ደግሞ ሊሳካለት ያልቻለ ወዳጅ ገጠመኝ። ሁኔታው በጣም ስላሳሰበኝ የራሴን ህይወት በምሳሌነት አንስቼ የወንድማዊነት ምክሬን ለገሰኩትና እራስን የማጥፋት እቅዱን ትቶ ህይወቱን ማስተካከል ላይ እንዲያተኩር ቃል አስገብቼው ተለያየን።

ከወራቶች በኋላ ከዚህ ወዳጄ ጋር ዳግም ተገናኘንና ስለ ህይወቱ ጠየኩት። እሱም በንዴት ተሞልቶ "ተወኝ ባክህ! ይሄንን ልገላገለው ጫፍ የደርሰኩትን ህይወት መክረህ እንድመለሰበት ያደረከኝ አንተ ነህ..."ብሎ ተቆጣ። ንግግሩ ቢያስኮርፈኝም "እንዴት?" ብዬ ጠየኩት።”

ከመጽሐፉ የተወሰደ።



N’or © 2024
Published by YEDI/የዲ
Addis Ababa, Ethiopia